# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሐሙስ

82ኛ ዓመት ቁጥር 201 መጋቢት 21 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ብዕራችን ስኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር

DERBA CEMENT

በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም

- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72

ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና 0111 26 23 18

ይዘዙን

ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።

ነገን ዛሬ እንሥራ


# «የዓባይ ግድብ ለተፋሰሱ አገራት ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ የሚያስገኝ ፕሮጀክት ነው»

- ዶክተር ኢንጂነር ጥላሁን ኤርዱኖ

በአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ መምህር

**ዘሳለም ግዛው**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ የዓባይ ግድብን በማልማት የያዘችው ተግባር ለተፋሰሱ አገራት የተሻለ የዝናብ መጠን እንዲያገኙ ከመርዳቱም በላይ ጎርፍ እንዳይከሰት በመቆጣጠርና ምንጮች እንዲጎለብቱ በማድረግ ዘርፈ-ብዙ ጥቅም የሚሰጥ ፕሮጀክት መሆኑን በአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ መምህር ዶክተር ኢንጂነር ጥላሁን ኤርዱኖ ገለጹ፡፡

ዶክተር ኢንጂነር ጥላሁን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገነባ ግድብ ለግብጽም ሆነ ለሱዳን በጣም ጠቃሚ ነው፡፡ የውሃ ችግር አያመጣም፤ ምንጮች እንዲጎለብቱ ያደርጋል፣ የጎርፍ ስጋትን ይቆጣጠራል፡፡

የግድቡ ግንባታና ተከትሎት እየተተገበረ ያለው ዛፎችን የመትከል ተግባር የኢትዮጵያን የአየር ሁኔታ የተሻለ፤ እንዲሆንና የወንዝ ውሃ መጠን እንዲጨምር በማድረግ ሱዳንና ግብጽ የበለጠ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደርጋልም ነው ያሉት ዶክተር ኢንጂነር ጥላሁን፡፡

ሆኖም አንዳንድ የታችኛው ተፋሰስ አገራት ለበርካታ ጊዜ ለብቻ መጠቀምን በመልመዳቸው የተለያዩ ምክንያቶችን በመፍጠር በጋራ ማልማትን አይፈልጉም፣ ሌላው ሲያለማም አይደግፉም፣ ‹‹እኛ ብቻ ያልነው ይሁን›› የሚል ሃሳብ ብቻ ነው የሚያነሱት ብለዋል፡፡

በወንዙ የሚመለከታቸው የተፋሰሱ አገራት ll ቢሆኑም በአብዛኛው ሱዳንና ግብጽ ውሃውን በሞኖፖል ይዘው ስለኖሩ ኢትዮጵያ ውስጥ ከውሃ ጋር የሚደረግን ልማት እንደ ስጋት እንደሚቆጥሩት ነው የተናገሩት፡፡

የላይኛው ተፋሰስ አገራት ጠንካራ የጋራ አንድነት


"የዓባይ ግድብ ... ወደ ገጽ 15 ዞሯል




ፎቶ - ገበዘ ገብሬ


eccs

የኢትዮጵያ የግንባታ ግብዓቶች አቅራቢ ኃ/የተ/የግል ማህበር

ETHIOPIAN CONSTRUCTION COMMODITIES SUPPLY PLC.

የአርማታ ብረት እና ሌሎች ብረታብረቶች አከፋፋይ

Mob. 0911 225057/ 0989 343434

አድራሻ: ከሜክሲኮ አደባባይ ወደ መርካቶ በሚወስደው መንገድ ከዲ-አፍሪክ ሆቴል ፊት ለፊት

ሲዳማ ባንክ

Sidama Bank

Bank for All!

ባንካችን የተሟላ የባንክ አገልግሎት መስጠት የሚያስችል ቅድመ-ሁኔታዎችን አጠናቅቆ በቅርቡ ሥራ ለመጀመር መዘጋጀቱን ስንገልፅ በታላቅ ደስታ ነው

አድራሻ

+25146 220 4704

+251944119303

565

+251462204704

info@sidamabanksc.com

www.sidamabanksc.com

ሲዳማ ባንክ አ.ማ.

Sidama Bank S.C.

የሁሉም ባንክ!


## ስምንት የ «ገበታ ለትውልድ» ፕሮጀክቶች በቅርቡ ይጀመራሉ

- የጎርጎራ ፕሮጀክት በአራት ወራት ውስጥ አገልግሎት መስጠት ይጀምራል


ገጽ 4


## ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች ለምግብ የሚመደበው በጀት ዝቅተኛ ነው

- ዩኒቨርሲቲዎች

## የሚመደበው በጀት እንዲሻሻል ጥናት ተሠርቶ ለገንዘብ ሚኒስቴር ቀርቧል

- ትምህርት ሚኒስቴር


ገጽ 15


# በኮንሶ ለድርቅ ለተጋለጡ ዜጎች ከ50 ሚሊዮን ብር በላይ ድጋፍ ተደረገ

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በኮንሶ ማህበረሰብ ላይ በተከሰተው የተፈጥሮ ድርቅ ምክንያት ጉዳት ለደረሰባቸው ዜጎች ከ50 ሚሊዮን ብር በላይ የሚያወጣ የተለያዩ የእህል ዓይነቶችን ድጋፍ አደረገ።

በድጋፍ ርክክብ ሥነሥርዓቱ ላይ ተገኝተው ንግግር ያደረጉት የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ አዳነች አቤቤ እንደገለፁት፤ በሌሎች አካባቢዎች እንደተደረገው ሁሉ የኮንሶ ዞን ሕዝብም በዝናብ እጥረት ሳቢያ የድርቅ ጉዳት እንደደረሰበት ከተሰማበት ወቅት አንስቶ ከተማ አስተዳደሩ ድጋፍ የማሰባሰብ ሥራ ሲሠራ ቆይቷል። በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ለሚደርሱ ተፈጥሮአዊ እና ሰው ሰራሽ ችግሮች ሁሌም ቀድሞ የሚደርሰው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርና ሕዝብ ዛሬም ለኮንሶ ሕዝብ


በኮንሶ ለድርቅ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




ፎቶ - ገበዘ ገብሬ


AMG STEEL FACTORY

ኤ.ኤም.ጂ ብረታ ብረት ፋብሪካ

Our Products

GI-Coil Color Coil Tiles

Ega Sky Tiles Corrugated Sheet Curving Ridge Sky Ridge V-Gutter Accessories

Tel: 0920 65 65 65 / 0940 60 60 60 / 0940 80 80 80/ 0940 81 81 81 / 0940 90 90 90 / 0979 06 06 06

AfriSky PLC ETHIOPIA

Our Products

Billet RHS Wire Rod Re-bar CZU H-BEAM Nail Streel Structure Tanker

Akaki, Gelan

0920 65 65 65 / 0940 60 60 60 / 0940 80 80 80

0940 81 81 81 / 0940 90 90 90 / 0979 06 06 06

ዜና

# አዋጁ ሲሻሻል አምራች ኢንዱስትሪው ያለበት ጫናና የተጋነነ ታክስ ይቀንሳል

**ልጅዓለም ፍቅሬ**



ፎቶ - ፀሐይ ንጉሤ

አዲስ አበባ፡- በሥራ ላይ የነበረው የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ሲሻሻል በአምራች ኢንዱስትሪው ላይ የነበረው ጫና እንዲሁም በአንዳንድ ምርቶች ላይ ተጥሎ የነበረው የተጋነነ የኤክሳይዝ ታክስ የሚቀንስ መሆኑ ተገለጸ፡፡

በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የፕላን፣ በጀትና ፋይናንስ ቋሚ ኮሚቴ ከገንዘብ ሚኒስቴርና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር እንዲሻሻል የቀረበው የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ላይ ውይይት አካሂዷል፡፡

የገንዘብ ሚኒስትር ዴኤታ እዮብ ተካልኝ (ዶክተር)፤ የገቢ አሰባሰቡን ለማሳደግ የተጣሉ የኤክሳይዝ ታክሶች እንደነበሩና የተጣለው ታክስ በጣም ከመጋነኑ የተነሳ ችግር ፈጥሮ እንደነበር አስታውሰዋል።

አሁን ላይ አዋጁን ለማሻሻል እንቅስቃሴ በመጀመሩ ማሻሻያ አዋጁ በአምራች ኢንዱስትሪው ላይ የነበረው ጫና እንዲሁም በአንዳንድ ምርቶች ላይ ተጥሎ የነበረውን የተጋነነ የኤክሳይዝ ታክስ ለመቀነስ እንደሚረዳ ተናግረዋል።

አገሪቱ አሁንም ለመኪና የምታስከፍለው ቀረጥ ከፍተኛ በመሆኑ አዲሱ የኤክሳይዝ ታክስ ማሻሻያ ይህንን ችግር ይቀርፋል ሲሉ አስታውቀዋል።

ዶክተር እዮብ እንደገለጹት፤ በሌላ በኩል ከዚህ በፊት የኤሌክትሪክ መኪናን በቋሚነት ያለምንም ኤክሳይዝ ታክስ እንዲገቡ ተፈቅዶ ነበር። በማሻሻያ አዋጁ መሠረት ደግሞ ለሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች ጭምር ተጠቃሚ የሚሆኑበት የታሪፍና የታክስ ቅናሽ እንዲኖራቸው ይደረጋል።

በጤና ላይ ጉዳት የሚያስከትሉ ምርቶች ላይ ሽመታ እንዲቀንስ፣ የቅንጦት ዕቃዎች ላይ የታክስ መጠኑ ለመቀነስ የሚረዳ የኤክሳይዝ ታክስ ትግበራ ባለፉት ሦስት ዓመታት መኖሩን ጠቁመዋል።

አዋጁ መሻሻሉ በፊት በሥራ ላይ በነበረው አዋጅ 1186/2012 አሠራር የታዩ ውጤቶች ለማሳደግና ከዚህ በፊት የኤክሳይዝ ታክስ ይጣልባቸው የነበሩ ምርቶች ላይ የታዩ ችግሮችን ለማስተካከል ይረዳል ብለዋል።

እንደ ዶክተር እዮብ ገለጻ፤ ከዚህ ቀደም በቪድዮ ካሜራ ላይ የተጣለው ኤክሳይዝ ታክስ ከ40 በመቶ ወደ 10 በመቶ ዝቅ የተደረገ ቢሆንም የፊልም ኢንዱስትሪው ባለበት የአቅም ውስንነትና የቅጂ መብት ያለመከበር የተነሳ እንዲሁም መንግሥት ኪነ-ጥበቡን ለማሳደግ ሲል በማሻሻያ አዋጁ መሠረት ሙሉ በሙሉ ታክሱን ያነሳል።

በተጨማሪ ቴሌቪዥን በዋናነት የመረጃና የእውቀት ማስራጫ በመሆኑ ኅብረተሰቡ ዝቅ ባለ ዋጋ የቴሌቪዥን ባለንብረት መሆን እንዲችል የኤክሳይዝ ታክስ እንዲነሳ ሀሳብ መቅረቡን ጠቁመዋል።

የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ አቶ ደሳለኝ ወዳጄ በበኩላቸው፤ የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ መሻሻል አስፈላጊ ነው፤ በጉዳዩ ላይ ሰፊ የውይይት መድረኮች መዘጋጀት አለባቸው ብለዋል።

የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ የማሻሻል ዓላማው የቅንጦት ዕቃዎች፣ አልኮል ነክ መጠጦች እና የሲጋራ ፍላጎትን ለመቀነስ፣ ወደ አገር የሚገቡ ያገለገሉ ተሽከርካሪዎች በነበረው የታክስ ሥርዓት እንዲቀጥሉ መደረጉ አዳዲስ ተሽከርካሪዎች በቅናሽ ዋጋ እንዲገቡ ለማድረግ መሆኑን ገልጸዋል።



ፎቶ - ፀሐይ ንጉሤ

አቶ አለማየሁ ባውዲ

# በክልሉ በሙስና የተጠረጠሩ 49 ሰዎች ላይ ክስ ተመሠረተ

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- ኮሚቴው ከሕዝቡና ከተቋማት ከደረሱት ጥቆማዎች ውስጥ በ78 ሚሊዮን ብር ምዝበራ የተጠረጠሩ 49 ሰዎች ላይ ክስ መመስረቱን የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል የፀረ ሙስና ኮሚቴ አስታወቀ፡፡

የክልሉ የሰላምና ፀጥታ ቢሮ ኃላፊና የክልሉ ፀረ ሙስና ኮሚቴ ሰብሳቢ አቶ አለማየሁ ባውዲ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ኮሚቴው ተቋቁሞ ወደ ሥራ ከገባበት ጊዜ ጀምሮ ከሕዝቡና ከተለያዩ ተቋማት ከአንድ መቶ በላይ ጥቆማዎችን ተቀብሏል፡፡

ከመጡት ጥቆማዎች መካከል ከ78 ሚሊዮን ብር በላይ የሕዝብና የመንግሥት ሀብት ምዝበራ በመፈፀም የተጠረጠሩ 49 ግለሰቦች ላይ መዝገብ ተደራጅቶ ክስ ተመስርቷል ብለዋል፡፡

ኮሚቴው ለሙስና ይበልጥ ተጋላጭ ዘርፎችን በመለየት እና እቅድ በማዘጋጀት ወደ ሥራ መግባቱን አንስተው፤ በእቅዱም ከዚህ በፊት በከባድ ሙስና ተጠርጥረው የነበሩ እና በተለያዩ ምክንያቶች ሂደታቸው ያላለቁ ጉዳዮች ቅድሚያ ተሰጥቶ እየተሠራ መሆኑንም አመላክተዋል፡፡

እንደ አቶ አለማየሁ ገለጻ፤ ሥራዎችን በተቀናጀ መልኩ መሥራት እንዲቻል ከክልሉ የተለያዩ አካባቢዎችና ከየተቋማቱ የሚመጡ ጥቆማዎችን እየሰበሰቡ የሚያደራጁና የጥቆማዎችን ትክክለኛነት እየፈተሹ መረጃዎችን በመሰብሰብ የምርመራ ሥራውን የሚመሩ ንዑስ ኮሚቴዎች ተቋቁመዋል፡፡

ይህን መነሻ በማድረግም ሕዝቡ ጥቆማ እንዲሰጥ ጥሪ ከቀረበበት ጊዜ አንስቶ በክልሉ በሁሉም አካባቢዎች ከተቋማት እና ግለሰቦች አዳዲስ የሙስና ጥቆማዎችን የመቀበል እና የማደራጀት ሥራ መሠራቱን ገልጸዋል፡፡

እስካሁን በተከናወነ የማጣራት ሥራም በሙስና የተጠረጠሩ 49 ግለሰቦችን ያካተቱ አራት መዝገቦችን በማደራጀት ለፍርድ ቤት ማቅረብ ተችሏል ያሉት ኃላፊው፤ መረጃዎችን ከማደራጀትና ከማጥራት ጎን ለጎን ተጠርጣሪዎችን በቁጥጥር ሥር የማዋል ሥራም ተጀምሯል ብለዋል፡፡

በቀሪ ግለሰቦች ላይ የቀረቡ ጥቆማዎችን በተቋቋሙት ንዑስ ኮሚቴዎች አማካኝነት የማደራጀትና የማጥራት ሥራ እየተሠራ ነው ያሉት አቶ አለማየሁ፤ ግለሰቦችን ተጠያቂ ከማድረግ ጎን ለጎን ምዝበራ የተፈፀመበትን ሀብት የማስመለስ ሥራም ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ገልጸዋል።

ሙስናን የመዋጋት ሥራው ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ያስታወቁት ሰብሳቢው፤ ሕዝቡ ከዚህ ቀደም ሲያደርግ እንደነበረው ጥቆማዎችን መስጠቱን መቀጠል አለበት ብለዋል፡፡

በተጨማሪም የሙስና ወንጀል ውስብስብ እንደመሆኑ ማህበረሰቡ ጥቆማ ከመስጠት ባለፈ ወንጀለኞችን በማጋለጥና አሳልፎ በመስጠት ለሥራው መሳካት የድርሻውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክት ጥሪ አቅርበዋል፡፡

# በፓርኩ ቀይ ቀበሮዎችን ለመከታተልና መረጃ ለመሰብሰብ የሚያግዝ «ፖላር» የተሰኘ ቴክኖሎጂ ጥቅም ላይ ዋለ



**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ጎንደር፡- በሰሜን ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ የቀይ ቀበሮዎችን ብዝሃ ሕይወት ለመጠበቅና ለመከታተል የሚያግዝ «ፖላር» የተሰኘ ቴክኖሎጂን ጥቅም ላይ ማዋል መጀመሩን የፓርኩ ጽሕፈት ቤት አስታወቀ፡፡

በጽሕፈት ቤቱ የቀይ ቀበሮዎች ጥበቃ ፕሮግራም አስተባባሪ አቶ ጌታቸው አሰፋ ለኢዜአ እንደተናገሩት፤ ቴክኖሎጂው በፓርኩ ያሉ ቀይ ቀበሮዎችን የአኗኗርና የጤና ሁኔታ እንዲሁም ሥነ-ተዋልዶና እንቅስቃሴያቸውን ለመከታተል የሚያግዝ ነው።

ቴክኖሎጂው ከዚህ ቀደም በፓርኩ ስለቀይ ቀበሮዎች መረጃ ለማሰባሰብ በባለሙያዎች ይካሄድ የነበረውን አድካሚ የእግር ጉዞ በማስቀረት በቴክኖሎጂ የታገዘ ሳይንሳዊ መረጃ ለማሰባሰብ እንደሚያስችል አስረድተዋል።

አቶ ጌታቸው እንዳሉት ቴክኖሎጂው በቀይ ቀበሮዎች አንገት ላይ የሚታሰር ሲሆን በሳተላይት አማካኝነት መረጃዎችን ለመሰብሰብ የሚያስችል ነው።

ባለፉት ሦስት ሳምንታት በተደረገ እንቅስቃሴ በአራት ቀይ ቀበሮዎች አንገት ላይ ቴክኖሎጂው ታስሮ ሥራው መጀመሩንም ተናግረዋል።

በቀይ ቀበሮዎቹ አንገት ላይ የተገጠመው ቴክኖሎጂ በአንድ ላይ የሚኖሩ እስከ 40 የሚደርሱ የቀይ ቀበሮ የቤተሰብ አባላትን ለመከታተል እንደሚረዳም ገልጸዋል።

ቴክኖሎጂው በፓርኩ ከተዘጋጀው የመረጃ ቋት ሥርዓት ጋር በመገናኘት የቀበሮዎቹን ደህንነትና ያሉበትን ቦታ ጭምር በየዕለቱ ለመከታተልና መረጃዎችን ለማደራጀት የሚያግዝ መሆኑንም አብራርተዋል።

እንደ አስተባባሪው ገለጻ ቴክኖሎጂው የተገጠመለት ቀይ ቀበሮ በቀን ምን ያህል ኪሎ ሜትር እንደተጓዘና የት ቦታ እንደሚገኝ እንዲሁም በሕይወት ስለመኖሩና ሲሞትም የት ቦታ ሞቶ እንዳለ መረጃ የሚጠቁም ነው።

በቀጣይ ሳምንታትም በተጨማሪ ሁለት ቀይ ቀበሮዎች ላይ ቴክኖሎጂው እንደሚገጠም ገልጸው፣ መሣሪያው ለተገጠመላቸው ቀይ ቀበሮዎች የእብድ ውሻ በሽታ መከላከያ ክትባት መሰጠቱንም አመልክተዋል።

አቶ ጌታቸው እንዳሉት አዲሱ ቴክኖሎጂ ከዚህ ቀደም በባሌ ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ በሚገኙ ቀይ ቀበሮዎች ላይ ተሞክሮ ባስገኘው ውጤት መነሻነት በሰሜን ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ ለመጀመሪያ ጊዜ ተግባራዊ ተደርጓል።

«ቴክኖሎጂው ቀይ ቀበሮዎቹ ያሉበትን ቦታ መጠቆሙ ከዚህ ቀደም ጎብኚዎች ቀበሮዎቹን ፈልጎ ለማየት የሚደርስባቸውን እንግልት ያስቀራል» ያሉት ደግሞ የፓርኩ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ አዛናው ከፍያለው ናቸው።

ባለፉት ዓመታት በፓርኩ ክልል ውስጥ ተግባራዊ የተደረገው የልቅ ግጦሽ ቅነሳ ስትራቴጂ በውሾች አማካኝነት ወደ ቀይ ቀበሮዎች ይተላለፍ የነበረውን የእብድ ውሻ በሽታ ስርጭት መቀነስ እንዳስቻለም ተናግረዋል።

ኃላፊው እንዳሉት በፓርኩ ክልል ዋነኛ የቀይ ቀበሮዎች መኖሪያና መገኛ ሥፍራዎች መካከል ግጭ፣ አይና ሜዳ፣ ጨነቅ፣ ሰባት ምንጭ እና ቧሂት ይጠቀሳሉ።

በአሁኑ ወቅት በፓርኩ ውስጥ ቁጥራቸው 90 የሚደርሱ ቀይ ቀበሮዎች የሚገኙ ሲሆን ከ20 ዓመት በፊት ቁጥራቸው 20 ብቻ እንደነበር አስታውሰዋል።

በአውሮፓውያኑ የዘመን ቀመር በ1978 በተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፣ የሳይንስ እና የባህል ድርጅት (ዩኔስኮ) በዓለም የተፈጥሮ ቅርስነት የተመዘገበው የሰሜን ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ 412 ስኩየር ኪሎ ሜትር ስፋት አለው።

የሰሜን ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙትን ዋልያ፣ ቀይ ቀበሮ እና ጭላዳ ዝንጀሮን ጨምሮ የሌሎች ብርቅዬ የዱር እንስሳትና አዕዋፋት መገኛ ስፍራ መሆኑ የሚታወቅ ነው።

ዜና

# በዞኑ የሚገኙ 68 ሺህ የሚጠጉ ተፈናቃዮች ትኩረት እንደሚሹ ተገለጸ

## - ክልሉ በበኩሉ በቅርቡ ድጋፍ እንደሚያደርግ አስታውቋል



**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- ከአበርገሌ እና ከፃግብጅ ወረዳ ተፈናቅለው በዋግኽምራ ለሚገኙ 67 ሺህ 961 ተፈናቃዮች ትኩረት እንዲደረግ ዞኑ አስታወቀ። የአማራ ክልል የቅድመ ማስጠንቀቂያና ምላሽ ዳይሬክቶሬት በበኩሉ ከዚህ ሳምንት ጀምሮ የምግብ ድጋፍ ለማድረግ እየሠራ መሆኑን አስታውቋል።

የዋግኽምራ ዞን አደጋ መከላከል እና ቅድመ ማስጠንቀቂያ ምላሽ ቡድን መሪ ወይዘሮ ዝናሽ ወርቁ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በጦርነቱ ወቅት ከአበርገሌ እና ከፃግብጅ ወረዳ የተፈናቀሉ 20 ሺህ የሚሆኑ ተፈናቃዮች በአራት መጠለያ ጣቢያዎች የሚገኙ ሲሆን የተቀሩት ከ47 ሺህ በላይ የሚሆኑ ተፈናቃዮች ግን በኅብረተሰቡ ውስጥ ተከራይተው የሚኖሩ ናቸው።

የሰላም ስምምነቱ ከተደረገ በኋላ ወደ ቦታቸው ይመለሳሉ የተባለ ቢሆንም እስካሁን ግን ምንም ተፈናቃይ ወደ መኖሪያ ቀዬው መመለስ አልቻለም ያሉት ወይዘሮ ዝናሽ ያሉበት ሁኔታም አሳሳቢ ነው ብለዋል።

ተፈናቃዮቹ ወደ ዋግኽምራ ዞን ከመጡ ሁለት ዓመት ከአምስት ወር የሆናቸው ሲሆን እርዳታ ማግኘት የቻሉት ግን ለተከታታይ አምስት ጊዜ ብቻ ነው ሲሉም ጠቅሰዋል።

እርዳታውንም ሊያገኙ የቻሉት ዞኑ በድርቅ የሚጠቃ አካባቢ በመሆኑ በድርቁ ለተጎዱ ሰዎች ተብሎ ከሚመጣ መደበኛ እርዳታ ላይ መሆኑን የጠቀሱት ወይዘሮ ዝናሽ፤ ለአንድ ሰው በወር 15 ኪሎግራም ስንዴ፣ አንድ ነጥብ አምስት ኪሎግራም ክክ እና ግማሽ ሊትር ዘይት በማቅረብ እንደሆነም ጠቁመዋል።

ወይዘሮ ዝናሽ እንዳሉት ለአዛውንት፣ ነፍሰ ጡሮች፣ ለሕፃናት እና ለበሽተኞች መቅረብ ያለበት ተጨማሪ ድጋፍም አልቀረበም።

ለተፈናቃዮቹ ትኩረት እንዲሰጥ በተደጋጋሚ ለሚመለከተው አካል ብናመለክትም ምንም ዓይነት ምላሽ ማግኘት አልቻልንም ያሉት ወይዘሮ ዝናሽ መንግሥት ተፈናቃዮቹን ወደ ቦታቸው እንዲመልሳቸው አልያም ባሉበት ሆነው የሚያስፈልጋቸውን የውሃ፣ የጤና፣ የመጠለያ እንዲሁም ሌሎች አገልግሎቶችን ማግኘት እንዲችሉ ማመቻቸት ይኖርበታል ብለዋል።

የአማራ ክልል የቅድመ ማስጠንቀቂያና ምላሽ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ብርሃኑ ዘውድነህ በበኩላቸው አጠቃላይ በዋግኽምራ ዞን ተፈናቃዮችን ጨምሮ ከ300 ሺህ በላይ ድጋፍ የሚፈልጉ ዜጎች ይገኛሉ። በዚህም በአሁኑ ሰዓት የልየታ ሥራ በመሥራት ላይ እንገኛለን። በዚህ ሳምንት መጨረሻም ልየታውን አጠናቀን የምግብ አቅርቦቱን እናደርሳለን ብለዋል።

እስካሁንም ለአምስት ዙር ድጋፍ አድርገናል ያሉት አቶ ብርሃኑ ነገር ግን የተደረገው ድጋፍ በቂ ነው ማለት አይደለም ብለዋል።

አቶ ብርሃኑ ጨምረውም ተፈናቃዮቹ ቀያቸውን ለቀው የመጡት በሰላም ማጣት ምክንያት ስለሆነ ወደ ቀያቸው የመመለሱ ተግባር ከእኛ ተቋም ውጪ የሆነ ነው። እስከሚመለሱ ድረስ ግን በእኛ በኩል የሚጠበቅብንን እናደርጋለን ብለዋል።

# ኅብረተሰቡ ከኮሌራ ወረርሽኝ ራሱን እንዲጠብቅ የኦሮሚያ ክልል ጥሪ አቀረበ

## -በሽታው በአምስት ዞኖችና አንድ የከተማ መስተዳድር ተከስቷል

## -ለ76ሺህ ዜጎች ክትባት ተሰጥቷል

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- ኅብረተሰቡ የግልና አካባቢ ንጽህናን በሚገባ በመጠበቅ ራሱን ከኮሌራ ወረርሽኝ እንዲከላከል የኦሮሚያ ክልል ጤና ቢሮ ጥሪ አቀረበ፡፡ በክልሉ በሽታው በተከሰተባቸው አካባቢዎች ለሚገኙ 76ሺህ ዜጎች ክትባት ተሰጥቷል፡፡


ፎቶ - ገባቦ ገብሬ
ዶክተር መንግሥቱ በቀለ

የኦሮሚያ ክልል ጤና ቢሮ ኃላፊ ዶክተር መንግሥቱ በቀለ ትናንት በሰጡት መግለጫ፣ በክልሉ በአምስት ዞኖች ውስጥ በሚገኙ 17 ወረዳዎችና አንድ የከተማ መስተዳድር የኮሌራ በሽታ ወረርሽኝ መከሰቱን አስታውቀዋል። በሽታውን ለመከላከል የግልና የአካባቢ ንጽህና ጨምሮ ሥራዎች በስፋት እየተሠሩ እንዳለ አመላክተዋል፡፡ ኅብረተሰቡም የግልና የአካባቢ ንጽህናን በመጠበቅ በራሱ ተሳትፎ ከበሽታው መጠበቅ አለበት ሲሉ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

የኮሌራ ወረርሽኝ በባሌ፣ ምሥራቅ ባሌ፣ ምዕራብ አርሲ፣ ምሥራቅ ቦረና፣ ጉጂ ዞኖች እንዲሁም በሞያሌ ከተማ መከሰቱን በመግለጽ፤ እንዳይስፋፋና የከፋ ጉዳት እንዳያስከትል የሕክምና አገልግሎትና የግንዛቤ ሥራዎች እየተከናወኑ እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡ እስካሁን ለ76ሺህ ዜጎች የኮሌራ ክትባት መሰጠቱንም ነው የተናገሩት፡፡ በሽታውን ለመከላከል ሁሉም ሰው የግሉንና የአካባቢውን ንፅህና መጠበቅ እንዳለበት የሕክምና ባለሙያዎችን ምክር ተግባር ላይ ማዋል እንደሚገባውም አክለው ተናግረዋል፡፡

እስካሁን የተናበበ አመራር የመስጠት፤ የአሰሳና የቅኝት ሥራ፤ የላብራቶሪ ሥራዎች፣ የግልና የአካባቢ ንጽህና አጠባበቅ ላይ ግንዛቤ የመስጠት፣ ሥልጠናና የአቅም ግንባታ ተግባራት፣ ከጤና ሚኒስቴርና አጋር አካላት ጋር ክትባት የመስጠት ሥራዎች መከናወናቸውን ዶክተር መንግሥቱ ተናግረዋል፡፡ በሽታው አዋሳኝ በሆኑ የኬንያ አካባቢዎች መከሰቱን ተከትሎ በሞያሌ ከተማ በስፋት እንዳይሰራጭ በትኩረት እየተሠራ እንዳለም ገልጸዋል፡፡

የከፋ ምልክት በታየባቸው ግለሰቦች የሕክምና ክትትልና መድኃኒት እየተሰጠ እንዳለም በመጥቀስ፤ ለዚህም የሚያስፈልጉ የሕክምና ግብዓቶች ዩኒሴፍና የዓለም ጤና ድርጅትን ጨምሮ የተለያዩ አጋር አካላት ድጋፍ ማድረጋቸውን አመላክተዋል፡፡

የጤና ምክር በሚፈለገው ደረጃ መተግበር አለመቻል፤ አንዳንድ አካባቢዎች በድርቅ የተጎዱ በመሆናቸው በሽታን የመቋቋም አቅሙም በዚያው የተዳከመ መሆኑና ግጭትና የጸጥታ ችግር የሚስተዋልባቸው አንዳንድ አካባቢዎች ላይም በሽታውን ለመቆጣጠር እንቅፋት ሆኖ መቆየቱን ገልጸዋል፡፡

የኅብረተሰቡን ተሳትፎ ማጠናከር ቀጣይ ሥራ መሆኑን የጠቆሙት የቢሮ ኃላፊው፤ እጅን በንጹህ ውሃና ሳሙና በመታጠብ ንጽህናን መጠበቅ፣ ምግብን አብስሎ መመገብ፣ የውሃ መገኛ ምንጮችን ማወቅ፤ በሽታውን ለመከላከል በጤና ሚኒስቴር አማካኝነት የሚወጡ ዓለም አቀፍ ደረጃቸውን የጠበቁ ፕሮቶኮሎችን መጠበቅና መተግበር ከኅብረተሰቡ የሚጠበቅ ትልቅ ሚና እንደሆነ አመላክተዋል፡፡

የኮሌራ በሽታ በባክቴሪያ አማካኝነት የሚከሰት ሲሆን፤ መንስኤውም የተበከለ ምግብና ውሃ ነው፡፡

# የእድገቱ ወጋገን የፈነጠቀበት የድሬዳዋው ኮሪደር

**ጌነትነት ምህረቴ**

በተለያዩ መኪና ፋብሪካዎች ውስጥ ለ6 ዓመታት ሠርቷል። ሊፋን ሞተር መኪና መገጣጠሚያ ሦስት ዓመት፤ ቢሾፍቱ አውቶሞቲቭ ኢንዱስትሪ ሁለት ዓመት ያህል አገልግሏል። በአሁኑ ጊዜ በድሬዳዋ ነፃ የንግድ ቀጣና ውስጥ በሚገኘው ኤልአውቶ ኢንጅነሪንግና ትሬዲንግ መኪና ማምረቻ ውስጥ እየሠራ ነው ያገኘነው። ወጣት አዳሙ ሞጁርን።

የመኪና ማምረቻ ፋብሪካዎች በአገራችን እየተስፋፉ ይገኛሉ የሚለው ወጣት አዳሙ ሞጁር፤ በአገራችን የመኪናና የሌሎች ማምረቻ ፋብሪካዎች እየተስፋፉ መምጣት ለኢትዮጵያ ዕድገትና ለዜጎቿ ሕይወት መለወጥ ትልቅ ድርሻ እንዳላቸው በተግባር አይቻለሁ ነው ያለው።

በተለይ መኪና ማምረቻዎች ሲስፋፉ መኪና እየረከሰ መሄዱ እንደማይቀር የሚገልጸው ወጣቱ፤ ምክንያቱም በአገር ውስጥ ብዙ መኪናዎች መመረት ሲጀምሩ አንደኛ ለብዙ ዜጎች የሥራ ዕድል ይፈጥራሉ፤ ሁለተኛ ከውጭ የሚገባውን መኪና በአገር ውስጥ በሚመረቱት ስለሚተካ የውጭ ምንዛሬን ማዳን ያስችላል። ሌላው የቴክኖሎጂ ሽግግሩ እየተስፋፋ ይሄዳል። እነዚህ ሁሉ ተደምረው የመኪና ዋጋ ወደፊት እየቀነሰ እንደሚሄድ ጥርጥር የለኝም ብሏል።

ከዚህ ቀደም መኪና መገጣጠሚያ ውስጥ የሚሠሩ የውጭ ዜጎች እንደነበሩ አስታውሶ፤ አሁን በአገር ባለሙያዎች ተተክቷል። ወደፊትም መኪና ለውጭ አገር ገበያ የምናቀርበት ጊዜ ሩቅ እንደማይሆን አመልክቷል።

መንግሥት ኢንዱስትሪዎችን ለማበረታታት የሚያደርገው ድጋፍ ይበል የሚያሰኝ ነው ያለው አዳሙ ሞጁር፤ በተለይ ፋብሪካዎች ለበርካታ ዜጎች የሥራ ዕድልን በመፍጠር የዜጎችን ሕይወት እየቀየሩ መሆኑን እኔና የሥራ ባልደረቦቼ ምስክር ነን ብሏል።



ነዲል ሙክታር በድሬዳዋ ከተማ መልካ 01ቀበሌ ነዋሪ ነው። እንደ ዕድል ሆኖ በቴክኒክና ሙያ በአውቶመካኒክ እንደተመረቀ እዚህ ፋብሪካ ሥራ አግኝቷል፤ በሙያዬ የሥራ ዕድል ወዲያው በማግኘቴ ደስተኛ ነኝ ብሏል።

በዘመናዊና ለሥራ ምቹ በሆነ ዘመናዊ ፋብሪካ ውስጥ መሥራት መታደል ነው የሚለው ወጣቱ፤ በድሬዳዋ ነፃ የንግድ ቀጣናን መንግሥት ከፍተኛ ገንዘብ አውጥቶ መገንባቱ ለኢንዱስትሪ መስፋፋትና ለንግድ መሳለጥ ያለውን ከፍተኛ ፍላጎት የሚሳይ ነው። ይህም ነገ ኢትዮጵያ ብሩህ ተስፋ እንዳላት አመላካች ነው። እኛ ዜጎቿም ጠንክረን በመሥራት ቤተሰባችንና አገራችንን ለመለወጥ መዘጋጀት ይኖርብናል ነው ያለው።

በድሬዳዋ ነጻ የንግድ ቀጣና ውስጥ ሁለት የመሥሪያ ሼዶችን ተከራይተው መኪናዎችን እያመረቱ እንደሆነ የገለጸው፤ ኤልአውቶ ኢንጅነሪንግና ትሬዲንግ ኩባንያ ኦፕሬሽን ሥራ አስኪያጅ ኤርሚያስ ኃይሉ፤ ፋብሪካቸው በቀን በአማካይ ከ22 እስከ 35 ዘመናዊ አውቶሞቢል መኪኖችን እንደሚያመርት ይናገራሉ።

እስካሁንም 44 መኪኖችን ለገበያ ማቅረባቸውንና 60 መኪኖች ደግሞ ተመረተው ለገበያ ዝግጁ መሆናቸውን ጠቁመው፤ በድሬዳዋ ነፃ የንግድ ቀጣና መሥራታቸው ትልቅ ዕድል መሆኑን ነው የተናገሩት።

በተለይ የአንድ ማዕከል አገልግሎት መኖሩ፤ ነፃ የንግድ ቀጣና ሥርዓት መዘርጋቱና ነፃ የንግድ ቀጣናው ለአማራጭ ወደቦች ቅርብ መሆኑ ፋብሪካው በአጭር ጊዜ ለማደግ ትልቅ ብሩህ ተስፋ እንዳለው ተናግረዋል።

ፋብሪካው በሙሉ አቅሙ ለመሥራትም በቅርቡም በአውቶ ሜካኒክ ዘርፍ የተመረቁ የቴክኒክና ሙያ ተመራቂዎችን ለመቅጠር በሂደት ላይ መሆናቸውን ገልጾልናል።

ከድሬዳዋ ነፃ የንግድ ቀጣና ቀጥታ ግንኙነት ያላቸው ኢንቨስትመንት ኮሚሽን፣ ኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል፣ ኢትዮ ቴሌኮምና ሌሎች አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ጭምር በአንድ መስኮት አገልግሎት የሚሰጡበትና የተቀላጠፈ ሎጂስቲክ አገልግሎት የሚያገኙበት መሆኑን የገለጹት የድሬዳዋ ነፃ የንግድ ቀጣና ምክትል ሥራ አስኪያጅ አቶ አህመድ ረሽድ፤ መንግሥት ከፍተኛ ኢንቨስትመን አድርጎ መሠረተ ልማቶችን ያሟላው ኢንዱስትሪዎች እንዲስፋፉና የሚያጋጥማቸውን ችግሮች በዘላቂነት ለመፍታት አቅዶ መሆኑን ነው ያስረዱት።

ነፃ የንግድ ቀጣናው በኢትዮጵያ የመጀመሪያው መሆኑን ገልጸው፤ አምራቾች ምርቱ አገር ውስጥ በሚሸጥበት ጊዜ ቀረጥ የሚከፍለው ገዥው ሲሆን ምርቱ ለውጭ ንግድ ሲላክ ደግሞ ምንም ዓይነት ቀረጥ የማይከፈልበትን ሥርዓት የተዘረጋ መሆኑን ተናግረዋል።

ከዚህ ቀደም ስድስት አምራች ኢንዱስትሪዎች እያመረቱ እንደሚገኙና ስምንት ባለሀብቶችም ወደ ነፃ ንግድ ቀጣናው ገብተው ለማልማትም በዝግጅት ላይ መሆናቸውን ገልጸው፤ ይህን አገራዊ ፋይዳ ያለው ነፃ የንግድ ቀጣና በፌዴራል መንግሥት ኮሙኒኬሽን አስተባባሪነት መገናኛ ብዙኃን መጎብኘታቸው ነፃ የንግድ ቀጣናውን ለማስተዋወቅና ባለሀብቱ እንዲሠራበት በማድረግ ረገድ ብዙ ፋይዳ ያለው መሆኑን ጠቁመዋል።

በመንግሥት ኮሚኒኬሽን አገልግሎት አስተባባሪነት የተለያዩ መገናኛ ብዙኃን የድሬዳዋን ነፃ የንግድ ቀጣናን ትናንት የጎበኙ ሲሆን፣ በቀጣይም የተለያዩ የልማት ሥራዎችን እንደሚጎበኙም ይጠበቃል።

ዜና

# ስምንት የ «ገበታ ለትውልድ» ፕሮጀክቶች በቅርቡ እንደሚጀመሩ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ገለጹ

## - የጎርጎራ ፕሮጀክት በአራት ወራት ውስጥ አገልግሎት መስጠት ይጀምራል

**ሞገስ ጸጋዬ**



ፎቶ ፦ ፀሐይ ንጉሤ

አዲስ አበባ፡- እንደ አገር ቱሪዝምን ለማስፋፋት በመላ አገሪቷ ስምንት የ«ገበታ ለትውልድ» አዳዲስ ፕሮጀክቶች ሊጀመሩ መሆኑን ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ገለጹ፡፡

በ6ኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 2ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 11ኛ መደበኛ ስብሰባ ላይ የምክር ቤቱ አባላት ላነሷቸው ጥያቄዎች ምላሽ የሰጡት ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ እንደገለጹት፤ የቱሪዝሙን ዘርፍ ለማስፋፋት እንደ አገር እየተከተልነው ያለውን መንገድ የምክር ቤት አባላት ሊደግፉ ይገባል ብለዋል፡፡

ኢትዮጵያ ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ ሊሸጥ የሚችል ታሪክ፣ መልክዓምድርና ባህል ቢኖርም የትራንስፖርት፤ የማረፊያና መዝናኛ ስፍራዎች ባለመዘጋጀታቸው ከቱሪዝም መጠቀም ያለብንን ያህል እየተጠቀምን አይደለም ብለዋል፡፡

‹‹ገበታ ለትውልድ›› ከወር በፊት መጀመሩን የገለጹት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ለግንባታው እስከ ሰባት ቢሊዮን ብር ለማግኘት አቅደናል ብለዋል፡፡ አንድ ወር ባልሞላ ጊዜም ከሕዝቡ ከአምስት ቢሊዮን ብር በላይ መሰብሰብ መቻሉን ጠቁመዋል፡፡

በዚህ ገንዘብ ስድስት የ‹‹ገበታ ለትውልድ›› እና ሁለት በግል የሚሠሩ በድምሩ ስምንት ፕሮጀክቶችን ለመሥራት መታቀዱን ገልጸዋል፡፡ ከሚሠሩት ፕሮጀክቶች ውስጥ በትግራይ ክልል በገራዓልታ አካባ የሚከናወነው አንዱ ሲሆን፣ አሁን የጀመርነው የሰላም ሂደትም ለግንባታው መፋጠን ጉልህ ሚና እንዳለው ገልጸዋል፡፡

ፕሮጀክቶቹ ከትግራይ በተጨማሪ በአማራ ክልል ሐይቅ፣ በኦሮሚያ ክልል በጅማ፣ በአፋር ክልል፣ በደቡብ ክልል አርባምንጭ፣ በሱማሌ ክልል እንደሚገኙ የጠቆሙት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ፤ ከፋሲካና ከረመዳን ጾም በኋላ ወደ ሥራ እንደሚገባ ገልጸዋል፡፡

በግል ከሚሠሩት ፕሮጀክቶች መካከል በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል በህዳሴ ግድብ አካባቢና ሚዛን አካባቢ የሚሠሩ ፕሮጀክቶቸ እንዳሉ የጠቀሱት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ለእነዚህም የዲዛይን ሥራ መጠናቀቁን አስረድተዋል፡፡ ስምንቱ ሲሠሩ እየተሠሩ ያሉት የመዝናኛ ቦታዎች ብዛት ከፍ የሚል በመሆኑ ለቱሪዝም እድገት ትልቅ አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡ በዚህ መንገድ ቱሪዝምን እያስፋፋን እንሄዳለን ብለዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሁሉም አካባቢ እንዲገነባ ጥያቄዎች አሉ፤ ነገር ግን የተጀመሩት ሊጠናቀቁ ይገባል፤ በጥቅሉ ቱሪዝም አካባቢ ተስፋ ሰጪ እንቅስቃሴዎች አሉ ብለዋል፡፡

እንደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ ለቱሪዝም እድገቱ ማነቆ የሆኑ ችግሮችን ለመቅረፍ በ ‹‹ገበታ ለሸገር›› ፕሮጀክት አዲስ አበባ ውስጥ ታሪካዊ ሥራ መሥራት ተችሏል፡፡ አዲስ አበባን እንደ ስሟ እናደርጋታለን ብለን ስንጀምር ብዙ ፈተና ይገጥሙናል ብለን ባናስብም እየሠራንና እየገነባን ስንሄድ ሊሠሩ የሚገባቸው ብዙ ሥራዎች እንዳሉ ተገንዝበናል፡፡ ወደፊትም በስፋት እንሄድበታለን ብለዋል፡፡

ከአዲስ አበባ አልፈን ኢትዮጵያን ለማዳረስ ባደረግነው ጥረት ‹‹ገበታ ለሀገር›› የጎርጎራ ፕሮጀክት በመጠናቀቅ ላይ ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ጎርጎራ አራት ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ አገልግሎት መስጠት ይጀምራል ሲሉም ተናግረዋል፡፡

የጎርጎራ ፕሮጀክት በአፍሪካ ከአንድ እስከ ሦስት ምርጥ ቦታዎች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ ለታሪክና ለትውልድ የሚተላለፍ ሥራ ተሠርቷል፡፡ ወንጪ፣ አላላ ኬላና ኮይሻ ላይ የተሠሩ ሥራዎች በጥራታቸውና በጊዜያቸው ተስፋ ሰጪ ናቸው፡፡ አሁንም ውስን በመሆናቸው እየተስፋፉ መሄድ አለባቸው ሲሉም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አብራርተዋል፡፡

# በኮንሶ ለድርቅ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

አለኝታነቱን አሳይቷል ብለዋል።

ከተማ አስተዳደሩ በሚችለው ሁሉ ድጋፍ ማድረጉን አጠናክሮ ይቀጥላል። ይህ በጎ ሃሳብ እንዲሳካ እጃቸቸውን ለዘረጉ ባለሀብቶች፣ ይህን ላስተባበሩ ኮሚቴዎች እና በማይመች ሁኔታ ውስጥ እየኖሩ ፈጣን ምላሽ ለሠጡት ለመዲናይቱ ነዋሪዎች ምስጋና አቅርበዋል።

የኮንሶ ዞን ሕዝብን በመወከል ድጋፉን የተረከቡት የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ዋና ዳይሬክተር አቶ ሰለሞን ሶካ፤ የኮንሶ ሕዝብ ሥራ ወዳድና ሠርቶ በመለወጥ የሚያምን ሕዝብ ነው። በተለይም በኮንሶ ልመናና ሌብነት ፀያፍ ነው፣ ያም ሆኖ ግን በተፈጥሮ ችግር ምክንያት ለተረጂነት ተዳርጓል፤ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርም ይህንን ከግምት ውስጥ በማስገባት ላደረገው ድጋፍ ምስጋና ይገባል ብለዋል።

የኮንሶ ሕዝብ የማይመች መልክዓ ምድርን በእርከን በማልማት ለኢትዮጵያም ምሳሌ የሆነ ታታሪ ሕዝብ መሆኑን ያስታወሱት አቶ ሰለሞን፤ ሆኖም ግን ባለፉት ተከታታይ አራት ዓመታት በዞኑ አካባቢ ባጋጠመው የዝናብ እጥረትና ከአጎራባች አካባቢዎች ጋር በነበረ ግጭት ከ10ሺህ በላይ ዜጎች ከመኖሪያ ቀያቸው እንደተፈናቀሉ ተናግረዋል።

አቶ ሰለሞን አክለውም ከ230ሺህ በላይ ዜጎች ለረሀብ በመጋለጣቸው አስቸኳይ ሰብዓዊ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው መሆኑን ገልፀው መንግሥትም ሆነ ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት ድጋፎችን እንዲያደርጉ ጥሪ አቅርቧል።

የዞኑ ሕዝብ ያቀረበውን የድረሱልኝ ጥሪ ተከትሎ የከተማ አስተዳደሩ ለሰጠው ፈጣን ምላሽ ምስጋና ያቀረቡት አቶ ሰለሞን፣ ድጋፉ ለተጎጂዎች በቀጥታ የሚደርስ መሆኑንም አረጋግጠዋል።

ድጋፉም ለሕፃናት የሚሆኑ አልሚ ምግቦች እንዲሁም ለአዋቂዎች የሚሆኑ የተለያዩ የእህል ዓይነቶች እንደሆኑ ተገልጿል።

በመርሃ ግብሩ ላይም ከንቲባ አዳነች አቤቤ፣ የከተማ አስተዳደሩ የብልጽግና ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ ሞገስ ባልቻ፣ የከተማ አስተዳደሩ የእሳትና አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን ኮሚሽነር ፍሰሀ ጋረደው፣ የተለያዩ አርቲስቶችና በመዲናይቱ የሚኖሩ የኮንሶ ተወላጆች ተገኝተዋል።


Ethiopian
የኢትዮጵያ
THE NEW SPIRIT OF AFRICA

# የቅጥር ማስታወቂያ

## የኢትዮጵያ አየር መንገድ ሰልጣኝ የመንገደኛ አገልግሎት ኤጀንት (Trainee Customer Service Agent)

አመልካቾችን አወዳድሮ ማሰልጠን ይፈልጋል፡፡

**የምዝገባ ጊዜ፡-**
**ከሚያዝያ 21 እስከ ሚያዝያ 24፣2015ዓ.ም**

- **የስልጠናው መጠሪያ**፡- ሰልጣኝ የመንገደኛ አገልግሎት ኤጀንት (Trainee Customer Service Agent)
- **ተፈላጊ መስፈርት**፡- በማንኛውም የትምህርት ዘርፍ በሌቭል 03 ወይም 10+3 ከታወቀ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም የትምህርት ማስረጃ ያላት/ያለው ወይም የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ፈተና የወሰደች/የወሰደ
- **እድሜ**፡ 18-35 ዓመት የሆነ/ች

* ከላይ የተጠቀሱትን መመዘኛዎች የሚያሟሉ አመልካቾች በድርጅቱ ድህረ ገፅ www.ethiopianairlines.com/AboutEthiopian/careers/vacancies በመግባት ኦንላየን መመዝገብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

bole International Airport, P.O.Box 1755 Addis Ababa. Ethiopia Tel:(251-011) 617 9900, Hotline Number 6787, Fax (251-001) 661 1474
www.ethiopianairlines.com

STAR ALLIANCE

Ethiopian
የኢትዮጵያ
THE NEW SPIRIT OF AFRICA

# ርዕሰ አንቀፅ

## ሰላማችንን በመጠበቅ ድህነትን ታሪክ ለማድረግ እንትጋ!

ለኢኮኖሚ እድገት/ብልጽግና ከሁሉም በላይ ሀገራዊ ሰላም እና መረጋጋት ወሳኝ ነው፤ ስለ ሰላም ሁለንተናዊ በሆነ መልኩ ከፍ ባለ የኃላፊነት መንፈስ መንቀሳቀስ ይጠይቃል። ይህ እውነታ በሌለበት ማኅበረሰባዊ ዐውድ ዘላቂ የኢኮኖሚ እድገት በማስመዝገብ ሕይወት ለመለወጥ የሚደረግ የትኛውም አይነት ጥረት ረጅም መንገድ የሚጓዝ አይሆንም ።

በተለይም ተፈጥሮ በብዙ በረከት ያደለቻቸው ፤ ይህንን በረከት በአግባቡ ተጠቅመው የሕዝቦቻቸውን ሕይወት በአጭር ጊዜ መለወጥ የሚችሉ እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ሀገራት ለሰላማቸው በቂ ጥበቃና ትኩረት መስጠት ከቻሉ ድህነትንና ኋላ ቀርነትን ታሪክ ማድረግ የሚችል አቅም እንዳላቸው ላለፉት አምስት ዓመታት እንደ ሃገር የሄድንባቸው የፈተና መንገዶች ተጨባጭ ማሳያ ናቸው ።

በሀገሪቱ የለውጥ ኃይሉ መንግሥት መሆኑን ተከትሎ ድህነትን ታሪክ ለማድረግ የጀመረው ሁለንተናዊ ጥረት ገና ከጅምሩ ብዙ ተግዳሮቶች አጋጥሞታል። በሃገር ውስጥ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ በተናበበ እና በተቀናጀ መልኩ ከጦርነት ጀምሮ በተለያዩ ግልጽና ስውር ደባዎች/ሴራዎች ተፈትኗል። ድህነትን መታገል የቱን ያህል ዋጋ ሊያስከፍል የሚችል አጀንዳ እንደሆነም በተጨባጭ ማረጋገጥ ችሏል።

በአንድ በኩል የሀገርን ስጋት ውስጥ የከተቱ ግጭቶችንና ጦርነቶችን በመመከት ፤በሌላ በኩል የተጀመረውን ድህነትን ታሪክ የማድረግ ትግል አጠናክሮ በመቀጠል፤ሀገራዊ ኢኮኖሚው ተከታታይ ዕድገት እንዲያስመዘግብ አድርጓል። ዓለም አቀፍ እውቅና ያገኘው ይህ እድገት ፤ለውጡ በተነሳበት መንፈስ በሀገራዊ ሰላም ቢታገዝ፣ እድገቱ በምን ደረጃ ሊሰላ እንደሚችል ማሰብ የሚከብድ አይሆንም።

ሀገራዊ ኢኮኖሚው በጦርነትና በግጭት ውስጥ ያስመዘገበው ዕድገት ፤ በሰከነ መንፈስና አእምሮ ማየት ለሚችል ሰብዓዊ ፍጡር ፣ እንደ ሀገር ያለንን የመልማት እድል በተጨባጭ የሚያመላክት ፤ድህነትን ታሪክ ለማድረግ የጀመርነው ትግል የዜጎች ቁርጠኝነት/ ሁለንተናዊ ድጋፍ ከታከለበት የሩቅ ጊዜ ተስፋ እንደማይሆን በተግባር የሚያሳይ ነው ።

በተለይም ሃገራዊ ኢኮኖሚው ላለፉት አስርና ከዛም በላይ ዓመታት በዘለቁ ችግሮች ሲፈተን የመጣ ከመሆኑ አንጻር ፤ባለፉት አምስት ዓመታት ያስመዘገባቸው ስኬቶች በተለያዩ ሴራዎች ምክንያት የሚገባቸውን ያህል ትርጉም ተሰጥቷቸው የአደባባይ ግዝፈት ባይሆኑም ፤የመጣንባቸው የፈተና መንገዶች የከፋ ዋጋ እንዳያስከፍሉን ታድገውናል።

በዚህም እንደሕዝብ/ሀገር ከዛሬ ተሞክሯችን በአግባቡ ልናጤነው፣ ትኩረት ልንሰጠው የሚገባው፤ ነገዎቻችንን ብሩህ ለማድረግና የተሻለች ሀገር ለመጪዎቹ ትውልዶች ለማስረከብ ከሁሉም በላይ የሰላም ጉዳይ ወሳኝ መሆኑን ነው። በተለይም ዘላቂ ልማት በማምጣት ከድህነት ለመውጣት እያደረግን ያለነው ብሔራዊ ጥረት ያለ ሰላም የተሟላ ትርጉም የሚኖረው አይደለም።

ለዚህም ከሁሉም በላይ የድህነት ገፈት ቀማሽ የሆነው ሕዝባችን ፤ ከዚህ አንገት አስደፊ ችግር ወጥቶ ቀና ብሎ መሄድ የሚያስችለውን ሁለንተናዊ አቅም ለመላበስ ሃገራዊ ሰላሙን ባለው አቅም ሁሉ መጠበቅ ፤ ለዚህ የሚሆን ዝግጁነትና ቁርጠኝነት መፍጠር ይኖርበታል።

አብረውት በኖሩት ሃይማኖታዊና ባሕላዊ የሰላም እሴቶቹ ራሱን የሰላም ሐዋሪያ በማድረግ ፤ለራሱ ፣ ለልጆቹና ለልጅ ልጆቹ የተመቸች ሰለማዊና የበለጸገች ሀገር መፍጠር ይጠበቅበታል ።

የሰላም ጠንቅ የሆኑ ጽንፈኛ ኃይሎች ለሚያዜሙት የጥፋት ዜማ ጆሮ በመከልከል፤በብሔራዊ ሰላሙ ለሚቆምሩ ግለሰቦችና ቡድኖች ዕድል ባለመስጠት ፤ እንደ ሃገር የተጀመረውን እና በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ ሳይቀር ውጤታማ እየሆነ ያለውን ድህነትን ታሪክ የማድረግ እልህ አስጨራሽ ትግል በንቃትና በባለቤትነት መንፈስ ሊሳተፍ ይገባል ።

እንደ ሕዝብ ይህን ማድረግ ከቻልን የአባቶቻችን የነጻነት የተጋድሎ ታሪክ በዓለም አቀፍ መድረኮች ያጎናጸፉንን ሞገስ ፤በተመሳሳይ መልኩ ከፍ ባለ ጽናት ድህነትን ታሪክ በማድረግ የተሟላ ማድረግ እንችላለን። ይህም እንደቀደመው ዘመን ከራሳችን አልፈን ለሌሎች አርአያ መሆን የሚያስችል ታሪክ ባለቤት እንድንሆን ዕድል ይፈጥርልናል!


## አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# «በጣም ብዙ ምርት ይዘን ሰዎች እንዲቸገሩ ማድረግ ተገቢ አይደለም»

**- የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር)**

**ካለፈው የቀጠለ....**

**በትናንትናው እትማችን«ሰላም እንደ ጦርነት ጀግንነት ይፈልጋል» በሚል ርዕስ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ፣ በ11ኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ስብሰባ ላይ ተገኝተው የስድስት ወራት የመንግስት አፈጻጸምን ሪፖርት አስመልክቶ የሰጡትን ምላሽና ማብራሪያ ማቅረባችን ይታወቃል፡፡ ዛሬም ከትናንቱ የቀጠለውን እና በተለያዩ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ዲፕሎማሲያዊና ሌሎችም አገራዊና ዓለማቀፋዊ ጉዳዮች ላይ ከምክር ቤቱ አባላት ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች የሰጡትን ምላሽና ማብራሪያ ቀጣይ ክፍል እንደሚከተለው ይዘን ቀርበናል፡፡**

ኢትዮጵያ ውስጥ ሕግ አስፈፃሚ አካላት መከላከያ፣ ደህንነት እና ፖሊስ የገነባንበት መንገድ ሀገርን ለማፅናት ያለንን ቁርጠኝነት የሚያሳይ ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ ሆነው በማያውቁት ልክ በቁጥርም፣በጥራትም፣ በቴክኖሎጂም ብዙ ከየአፍሪካ ሀገራት የሚቀኑባቸው ተቋማት ሆነዋል። ያን የምናደርገው ሀገራችን ኢትዮጵያ እንዳትፈርስ ስለምንፈልግ ነው። ማዘኗም መጎሳቆሏም ይጎዳናል ብለን ስለምናስብ ነው። ከዚያ የሚገኝ ጥቅም የለም።

የኢትዮጵያ የመፍረስ ስጋት አልፏል። ከእንግዲህ በኋላ እንደዚህ አይነት ስጋት እኛ የለንም። ኢትዮጵያን ለማፍረስ የሚነሳ ኃይል ካለ ኢትዮጵያን ለማጽናት የሚያስችል የተሻለ ኃይል ስለገነባን ስጋት የለንም። ከዚህ ቀደም ነበረን ፤ ኃይል ስላልገነባን። አሁን ግን ለማፍረስ የሚችል ኃይል እንኳን በኢትዮጵያ ውስጥ ከሌላም ቦታ አለ ብለን አናስብም። በዚህ ብዙ ስጋት አያስፈልግም።

ነገር ግን ኢትዮጵያ ልትፈርስ ነው፤ እየፈረሰች ነው ባሉ ሰዎች ጭንቅላት ውስጥ ፈርሳለች። ጭንቅላት ውስጥ ቀድሞ የፈረሰን ሀገር መገንባት አይቻልም ። እኛ ጋር ያለው ሃሳብ የምትበለፅግ፣ የምትፀና፣ በከፍተኛ ችግር ውስጥ የምታልፍ፣ ይበልጥ የምትቀራረብ ኢትዮጵያ ትፈጠራለች የሚል ነው ። ለሱ ነው የምንሠራው። እኔ ካልመራሁ ትፈርሳለች ብሎ ለሚያስብ ኃይል እየፈረሰች ናት። ችግር ውስጥ የምታልፍ የበለጠ የምትቀራረብ ኢትዮጵያ ትፈጠራለች። ለእሱ ነው የምንሠራው።

እኔ ካልመራኋት ትፈርሳለች ብሎ ለሚያስብ ኃይል የፈረሰች ናት። ለእኛ ግን በኋላም በዳታ/በመረጃ እንደማሳየው እጅግ ብዙ ድንቅ ድንቅ ሥራ እየሠራች ያለች ፤አሁንም ብዙ ፈተና ያለባት ፤ ተደምራ የምትወጣ ትልቅ ሀገር እንደሆነች ነው የምናምነው። ወደ ሳር ቤት ከዚህ ቀደም ስትነዱ ከኤዩ /AU/ በኋላ ያለው ድልድይ ጋር መኪና ውስጥ ሆናችሁ መስኮት ዝቅ ያለ እንደሆነ ከየት እንደመጣ የማታውቁት አፍንጫ የሚሰነፍጥ ሽታ አለ።

መኪና ውስጥ አይደለም ከአስፋልት ነው፤ ከድልድዩ ማዶ እየመጣ ይረብሻል። በባሕርይው አፍንጫን የሚሰነፍጥ ፤ በጣም በርቀት ሄዶ መረበሽ የሚችል ነው። መልካም መዓዛ ግን ቀረብ ካላሉት በስተቀር አይሸትም። አሁን የምትሰሙት አፍንጫ የሚሰነፍጥ ጩኸት ከዛ ከፀለምተኝነት የመጣ ሀሳብ ነው። እንጂ ቀረብ ብሎ ሲታይ በእያንዳንዱ እንቅስቃሴ ኢትዮጵያ ተስፋ በሚሰጥ ጉዞ ላይ ነው ያለችው። በጣም የሚገርመኝ በቀደም ኤዩ/ AU/ ስብሰባ ላይ ከመጡ ሰዎች ካገኘኋቸው 100 ፐርሰንት የሚሆኑት የነገሩኝ አንድ ነገር ነው።

ኢትዮጵያ በውጊያ ውስጥ ፣ በኮሮና ውስጥ በዚህ ሁሉ ችግር ውስጥ እንዴት መለወጥ ቻለች ፤ ህዳሴ እንዴት ይገነባል የሚሉ ናቸው ። እንዴት ነው እዚህ ያለን ሰዎች ይሄንን ለማየት የምንቸገረው። ፈተና አለ፤ችግር አለ፤ እውነት ነው። ነገር ግን ከድህነት ውጪ መበልፀጊያ መንገድ፤ አንድ መሆኛ ፤ሰላም መሆኛ መንገድ የማይታያቸው ኃይሎች ሁልጊዜ መከራ ያወራሉ። ይሄ ብርጭቆ ባዶ አይደለም። በውስጡ አየር አለ በውስጡ አየር ያለው ብርጭቆ ልክ ውሃ ሲጨመርበት በምታውቁት ሕግ ሥፍራ ይለቃል።

አሁን አየር የት እንደገባ ባናውቅም ሥፍራ ይለቃል ምክንያቱም በሲምፐል ማቲማቲክስ ማስ ማለት ዴንሲቲ ታይምስ ቮልዩም ስለሆነ ይሄን ውሃ የሞላውን ብርጭቆ ዝም ብለን ፍሰስ ብንለው አየር የሞላውን ብርጭቆ አየር ውሃን ሊያስወጣ አይችልም። የሚያስወጣው ከበድ ያለ ማስ ነው ድንጋይ ነው። ከበድ ያለ ነገር ሲመጣ ነው የሚወጣው። አሁን ያለውን መንግሥት መቀየር የሚቻለው ሻል ያለ ሀሳብ ሲመጣ ነው፤ አየር ጨብጦ ልቀቁ አይሆን ማለት ነው። የተሻለ ሀሳብ ሲመጣ ውሃው ቢፈልግም ባይፈልግም ሥፍራውን ለቅቆ ይሄዳል። ዝም ብሎ ግን ከሆነ አይሆንም።

እባካችሁ መስከንና ነገር በማስተዋል ማየት ብንችል ጥሩ ነው። ከአንደኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ጀርመን ሀገር ወይማ ሪፐብሊክ የሚባል መንግሥት ተቋቁሞ ነበር። ይሄ መንግሥት ይሄኛው መንግሥት አንደኛው የዓለም ጦርነት አልፎ ሁለተኛው ሳይፈጠር የነበረ መንግሥት ነው። ሦስት ከባድ ከባድ ኃይሎች ያስቸግሩት ነበር። አንደኛ የንጉሡ ሥርዓት መመለስ አለበት የሚሉ። በቅርቡም ጀርመን ታይቷል እንደዚህ ዓይነት ሰምታችሁ ይሆናል።

የንጉሡ ሥርዓት መመለስ አለበት ብለው የጠፋውን የንጉሥ ሥርዓት የሚናፍቁ ኃይሎች ነበሩ። ሁለተኛው ለጀርመን የሚያስፈልጋት ኮሚኒስት መንግሥት ነው። እና ኮሚኒዝም መቋቋም አለበት የሚሉ ኃይሎች ነበሩ። ሦስተኛው ሊብራል መንግሥት ወይም ሶሻል ዴሞክራት መንግሥት ያስፈልጋታል ብለው የሚያስቡ ኃይሎች ትጥቅም ያላቸው የሚረብሹ ኃይሎች ነበሩ። እነዚህ ሦስት ኃይሎች ለመገዳደርና ጀርመንን ለማጥፋት የተፈጠረው መንግሥት ጀርመንን ለሁለት ከፈለ፣ አውሮፓን ናጠ፤ ዓለምን ናጠ፡ ሁለተኛው የዓለም ጦርነትን ቀሰቀሰ፣በሚሊዮን ሰዎች አለቁ እንደምታውቁት እኔ የሚያሳስበኝና ምክር ቤት እንዲገነዘብ የምፈልገው ዴሞክራሲን ለመገንባት ጥረት እያደረግን ነው።

ነፃ ሚዲያ፤ነፃ ሀሳብ፤ነፃ ምርጫ ሙከራ የተደረገበት ጥረት ነው። ይሄ ዴሞክራሲን ለመገንባት የምናደርገውን ጥረት በቀና መንገድ አስበን በነፃ ገበያ ተወዳድረን ሰላማዊ በሆነ መንገድ ለመተካካት የማንሠራ ከሆነ የመንግሥቱ መንገድ የሚሆነው ዲክታተርሽፕ ነው። ዴሞክራሲን ካልገነባን ዴክታተርሽፕ ነው የሚገነባው። ዴክታተርሽፕ ደግሞ ሞክረን፤ሞክረን ኢትዮጵያ ውስጥ ሞክረን ሞክረን አልተሳካልንም። ብንገባበት ቀጥሎ የመጣው ዲሴንትግሪዴሽን ነው።

እንደምንም ብለን ለኢትዮጵያ ለሕዝቧ ጥቅም ሲባል ዴሞክራሲን ከነ እንከኑም ቢሆን እንኳን ማስቀጠል ማሰብ ነው እንጂ ያለብን ከዛ ውጭ በኃይል ፤በሴራ፤በምናምን ማሰብ የለብንም ፤ እንደዛም ከሆነ ያው የተሻለ ጉልበት ያለው መንግሥት ስለሆነ ወደ ጉልበት ይሄዳል። ወደ ጉልበት ደግሞ ከሄደ የነበረውን ጥፋት ይደግማል። ያጥፋት ደግሞ ይበትነናል። ወደዛ እንዳንሄድ የበለጠውን ነገር ማሰብ ጠቃሚ ይመስለኛል። የጀርመን መንግሥትን የገጠመው እኛንም እንዳይገጥመንና ለሌሎች እዳ እንዳንሆን በተቻለ መጠን ነገርን በማስተዋልና በዘላቂ ጥቅም አንፃር ብናይ ጥሩ ይሆናል።

ስልጣን ብትለቅ የተባለው በጣም ጥሩ ጥያቄ ነው። ግን ጥሩ የሚሆነው ሥልጣን ብንለቅ ቢባል ነበር። ምክንያቱም ሥልጣን ፤ መንግሥት ማለት አስፈፃሚ ማለት አይደለም። ሕግ አውጪ መንግሥት ነው፤ ሕግ ተርጓሚ መንግሥት ነው። አስፈፃሚ መንግሥት ነው። እኛ እዚህ ያለን ሰዎች የመንግሥት ባለስልጣኖች ነን። ይልቁኑ የተከበሩ አቶ ክርስቲያን ደግሞ ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ናቸው፤የአንድ ሚኒስቴር አለቃ ናቸው። እና በጋራ ብንለቅ ቢሆን የበለጠ ጥሩ ነበር። ምክንያቱም እርሶ እንደሚገነዘቡት የሁሉ ችግር ምንጭ እኔ ብቻ ነኝ ማለት አልችልም። ኃላፊነት ከወሰድንም በጋራ ቢሆን ጥሩ ይሆናል ብየ አስባለሁ።

ነገር ግን ይሄ ጥያቄ እሳቸው ቢያነሱትም እሳቸው ላይም ይነሳ ነበር። በውጭ ያሉ በፓርላማ እንደሳቸው አሸንፈው መግባት ያልቻሉ ሰዎች ለምንድነው እኚህ ሰው የቋሚ ኮሚቴ ኃላፊ ሆነው የተቀመጡት? አይለቁም እንዴ እያሉ ከዚህ ቀደም በሚዲያ እንደምትሰሙት ብዙ ይተቻሉ። እርሶ ምርጫ አሸንፈው ነው የገቡት። እዚህ

ወቅታዊና ልዩ ልዩ

# ወቅታዊ

# «በጣም ብዙ ምርት ይዘን ሰዎች እንዲቸገሩ...

ተቀምጠው የሕዝቡን ጥያቄ ማንሳትዎት ተገቢ ነው ብዬ ነው የማስበው። ለመቆጣጠሩም የሚያደርጉት ጥረት ተገቢ ነው ።

ከሥልጣን ጋር ተያይዞ ያለው ጉዳይ በአንድ ቀላል ምሳሌ ለማስረዳት በደቡብ ሕንድ ሞንኪታ የሚባል ጦጣን የማጥመድ ቴክኒክ አለ። ጦጣ እንደምታውቁት ቁንጥንጥ ናት፤ቅብዝብዝ ናት። ለአደን አትመችም እና በደቡብ ሕንድ ያሉ አዳኞች ጦጣን ለማጥመድ ቅል የሚመስለውን የኮኮናት ፍሬ በጦጣ እጅ ልክ በቀጭኑ ይቀዱና ሲቀዱት የጦጣ እጅ ቀጭን ስለሆነ በዛ ልክ ይቀዱትና ወደ ውስጥ ሰፋ አድርገው ሩዝ ያስቀምጣሉ። ሊይዟት ስለማይችሉ ነው። ጦጣ ሩዝ አየሁ ብላ በዛ ልክ እጇን ሰዳ ልውጣ ስትል የተሠራው ለቀጭኑ ስለሆነ ከጨበጠች በኋላ አይለቃትም።

ይህች ጦጣ የሰው ሩዝ ነው የያዝኩት፤የማይገባኝ ሩዝ ነው የያዝኩት፤ይገቼው ከቆየሁ ልያዝ እችላለሁ በትኼው ልሂድ አትልም። እንደጨበጠች ትታገላለች። በዚህ ጊዜ ያን የኮኮናት ፍሬ መውሰድ ስለማትችል አዳኝ መጥቶ ይወስዳታል። ጦጣዋን ያደናት፤የያዛት ምንድነው ያላችሁ እንደሆነ ሀሳቧ ነው እንጂ ወጥመዱ አይደለም። እዛው በትና ብትለቅ ትወጣለች። በሀሳብ ግን ሩዝ አፍሼ ካልወጣሁ ካለች ሀሳቧ እዛው አጥምዶ ያስቀራታል።

እዛው በትና ብትለቅ ትወጣለች። በሀሳብ ግን ሩዝ አፍሼ ካልወጣሁ ስላለች ሀሳቧ አጥምዶ ያስቀራታል እዛው ማለት ነው። ‹‹ዶሮ ብታልም ጥሬዋን›› ነው የሚባለው ቁጭ ብለው የሚያልሙ ሰዎች አሉ። ሁልጊዜ። በዚያ መንገድ ጥሩ አይሆንም። ሁለተኛው ቢጨበጥ ጥሩ የሚሆነው ሥልጣንን በሚመለከት በእኔና በተከበሩ አቶ ብናልፍ መካከል የሚደረግ ድርድር የለም።

የሥልጣን ባለቤት ሕዝብ ነው። ሥልጣን ሰጪም ነፋጊም ሕዝብ ነው። እኔና አቶ ብናልፍ ማድረግ ያለብን የተሻለ ሀሳብ ይዘን ሕዝባችን ጋር መቅረብና የኔን ሀሳብ ምረጥልን ብለን በሰጪው ነው የምንመረጠው እንጂ በምክር ቤት ውስጥ ስጠኝ፣ልቀቀኝ በሚል አይሆንም ማለት ነው። ሰጪው ጋ ሀሳብ የተሻለ ይዞ መቅረብ ያስፈልጋል። ለዚሁ ሥልጣን ‹‹በኮሮጆ እንጂ በመናጆ አይያዝም›› ነው መልሱ።

ለምርጫ ሦስት ዓመት ይቀራል ያኔ፤ በውጭም ‹‹የኦሮሞ መንግሥት፣የኦሮሞ መንግሥት›› እያሉ የሚዘፍኑ አሉ ብዙ ዘፋኞች አሉ ፤ እነሱን ጨምሮ ሰብሰብ ብሎ ሀሳብ አጠናክሮ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ማቅረብ ነው። እኛ ለኢትዮጵያ ሕዝብ እንደተባለው የገባነውን ቃል ካልፈጸምን ፣የኢትዮጵያ ሕዝብ በእኛ አስተዳደር ካልረካ ፣በምርጫ ከጣለን በተደጋጋሚ እንደምንለው ስልጣናችንን በደስታ እናስረክባለን። ፓርቲዎች መዘጋጀት ያለባቸው ሀሳብ ይዞ መምጣት ነው። አሁን ሀሳብ የለም ውሀውን በአየር ላውጣ ነው።

ሰብሰብ ብሎ ሀሳብ ይዞ፣ ያን ወደሕዝብ አቅርቦ፣ለመመረጥና ለማሸነፍ የሚደረግ ጥረት ለሁላችን የሚጠቅመን ይሆናል። ለሁላችን በዚህ አግባብ ቢታይ ጥሩ ይመስለኛል። ከዚሁ ጋር ተያይዞ የእኛን መንግሥት በሚመለከት በሰሜን ጦርነት፣ በምዕራብ፣ከሸኔ ጋር በምሥራቅ እንደዚህ ተብሎ ብዙ ፈተናዎች ስላሉ ‹‹አሁን ነው ጊዜው፣ አሁን ነው የሚዳከሙት ፣ አሁን ነው የሚወድቁት›› የሚል ሀሳብ በስፋት ይሰማል።

የተከበረው ምክር ቤት እንዲገነዘብ የምፈልገው፣በዓለም ላይ ፈተና አልቦ፣ ችግር አልቦ ሀገር የለም። የችግራችን ባሕርይ ይለያያል እንጂ አሜሪካን በጣም ብዙ ችግር አለባት። ተማሪዎች ይሞታሉ ፣ሰዎች ይሞታሉ፣ሥቃይ አለ እዛም። አውሮፓም እንደምትሰሙት ነው ፤ ሰሞኑን ሥቃይ አለ ችግር አለ ፣ ይቃጠላል››። የእነሱ ችግር ‹‹ዲሽ ወሸር›› ይባላል። የእኛ ‹‹ላውንደሪ›› ነው። ዲሽ ወሸር ዕቃ የሚያጥብ ማሽን ነው ዕቃ ሲያጥብ ብርጭቆውን አይሰብረውም፣ ድስቱን አይሰብረውም ፣አይጨምቀውም። በፕሬዥር ብቻ ውሀ እየረጨ ያጥበዋል። ከውጭ ሲታይ ብርጭቆውም እንዳለ ነው፣ ድስቱም እንዳለ ነው።

የእኛ ግን ላውንደሪ ነው። ሸሚዝ ሲገባበት ይጨምቀዋል፣ያሸዋል። እስኪተኮስ ድረስ ያ ሸሚዝ ተለብሶ ልብስ የሚሆን አይመስልም ያለቀለት ነው የሚመስለው እኛ የሚያጥበን ላውንደሪ የሚያሸን ቢሆንም ተተኩሰን አዲስ ስለምንሆን ፣ፈተናዎች ይበልጥ ስለሚያጠናክሩን፣ ይበልጥ ስለሚያስተምሩን በቀለለ መንገድ የሚሆን አይመስለኝም። ጠንከር ያለ ዝግጅትና ሥራ ቢኖር ጥሩ ነው ብዬ አስባለሁ ፤ በድምሩ ኢትዮጵያ ውስጥ ከባለፈው የተሻለ ሰላም አለ። አበክረን ልንሠራበት የሚገባን ነገር አለ።

በሀገሪቱ እጅግ የሚያስደምሙ ውጤቶች አሉ። የሚያሳዝኑም ጉዳዮች አሉ። በሁለት ሕዝቦች መካከል፣ ኃላፊዎች መካከል የማይገቡ ነገሮች አሉ። እነሱን ደግሞ በሽግግር ፍትሕ ማረጋገጥ አስፈላጊ ይሆናል። የሽግግር ፍትሕ ያልነው በነበረው ሂደት ውስጥ ተበዳይና በዳይ ስላለ ፣የጉማ ባሕል ስላለን ፣በይቅርታ በሕግ አግባብ ያለፈውን ታሪክ እየዘጋን ብናልፍ ጥሩ ነው ከሚል እሳቤ ነው። ምክንያቱም ጦርነት ሁለት ኃይሎችን ተሸናፊ ነው የሚያደርገው፤ሰላም ግን ሁለቱን ኃይሎች አሸናፊ ያደርጋል።

ቢያንስ ልጆቻችን ሻል ያለ ነገር እንዲያገኙ ያደርጋል። እና ለሰላሙ አብዝተን እንሥራ ፤ለሰላሙ አብዝተን እንቁም። ከትግራይ ጋር የተጀመረውም ይሁን ፤ከሸኔም ጋር ፤ከቤኒሻንጉል ይሁን፤ከአገው ሸንጎ ይሁን ፤ከቅማንትም ጋር ይሁን፤ ከየትኛውም ፎርስ/ኃይል ጋር ያለውን ጉዳይ በሰላም ለመጨረስ የሚደረግ ጥረት የሚበረታታ ሊሆን ይገባል።

ሱዳንን በሚመለከት በኢትዮጵያና በሱዳን መካከል ላለፉት ስልሳ ሰባ ዓመታት በታሪክ በትንሹ (በታሪክ ታይቶ የማይታወቅ የሚለው ስህተት ነው) ከኃይለሥላሴ ዘመን ጀምሮ ጭቅጭቆች አሉ። የኮሎኒ ኃይል ሲሄድ ዲማርኬሽ ስላልተሠራ የይገባኛል ጥያቄዎች ሁልጊዜ አለ። እኔ እንኳን እዚህ ምክር ቤት አባል እያለሁ ሁልጊዜ ጥያቄው ይነሳ ነበር። አዲስ ጉዳይ አይደለም።

ነገር ግን ወደ ውጊያ ስንሄድ ተጨማሪ ያጋጠሙን ፈተናዎች የነበሩ ቢሆንም ከሱዳን መንግሥት ጋር ተነጋግረን በሰላማዊ መንገድ ጉዳዩን ለመፍታት የጋራ የሚኒስትሮች ኮሚሽን አቋቁመናል። ያን ያደረግነበት ዋና ምክንያት ችግሩ በዘላቂነት የሚፈታው ዲማርኬሽን ሲደረግ ነው። እስከዚያ ግለሰቦችና አርሶ አደሮች በሁለቱም እንዳይጉላሉ የሚል የጋራ ስምምነት ቢኖርም በአፈጻጸም ደረጃ ያሉ ስህተቶች ይኖራሉ። ጉዳዩን የምንፈታው ግን በውይይትና በንግግር ቢሆን የበለጠ ጠቃሚ ይሆናል። በዚህ አግባብ እየተኬደ መሆኑን የተከበረው ምክር ቤትም እንዲገነዘብ ነው።

ደቡብ ሱዳንን በሚመለከት በምዕራብ ኢትዮጵያ አካባቢ ወረራ እያካሄዱ ነው ለሚለው ፤ደቡብ ሱዳን የሰው ሀገር ለመውረር የሚያስችል ቁመናም ፍላጎትም የላትም። ስለዚህ በወረራ መንገድ ባይገለጽ ጥሩ ነው። ወደ 20 ሺ ገደማ የሚጠጉ አርብቶ አደሮች፤ ችግር ገጥሞናል፤ድርቅ ገጥሞናል እናንተ ጋር እንቆይ የሚል ጥያቄ አቅርበዋል። ለማነጋገርም ሙከራ ተደርጓል።

ዞሮ ዞሮ በድንበር አካባቢ የሚያሰጋ ነገር አይፈጠርም። በአርብቶ አደር ደረጃ ፤ ከኬንያም፤ ከደቡብ ሱዳንም አልፎ አልፎ የሚያጋጥሙ ችግሮች አሉ፤ አሁን ቅድም ባነሳሁት አሰፋፈር አንዱ ትኩረት የተሰጠው የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ አካባቢ በመሆኑ በኮንትሮባንዱም በዚህም ጉዳይ ያሉ ችግሮች እየተፈቱ ይሄዳሉ። ከደቡብ ሱዳን መንግሥት ጋር በጋራ ልንፈታው የተግባባንበት ጉዳይ ነው።

ሸኔን በተመለከተ ጠያቂው እንዳነሱት ወለጋ አካባቢ ላለፉት አራት አምስት ዓመታት ልማት እንዳይሠራ ፤ሰዎች እንዲፈናቀሉ፤ እንዲገደሉ ብዙ መጎሳቆል ያመጣ ግጭት ነው። ይህ ግጭት በሰላም እንዲፈታ መንግሥት ከፍተኛ ፍላጎት አለው። ከፍተኛ ፍላጎት አለውም ብቻ ሳይሆን በባለፈው ሥራ አስፈጻሚ ተወያይቶ ሥራ አስፈጻሚ አይደለም በማዕከላዊ ኮሚቴ ተወያይቶ ፓርቲያችን ምክትል ፕሬዚዳንት የሚመራ ኮሚቴ አቋቁሟል።

የሰላም ውይይቱን የሚመራ። ከቤኒሻንጉል ጋር የተሻለ ውጤት ተገኝቷል፤ ከጋምቤላ ጋር የተሻለ ውጤት ተገኝቷል፤ ከቅማንት ጋር እንዲሁ የሚቀሩ ጉዳዮች ቢኖሩም። ሸኔን በተመለከተ ባለፉት አንድ ሁለት ወር ገደማ ከአስር በላይ ሙከራዎች ተደርገዋል። ያስቸገረው ነገር አንድ የተሰባሰበ ፎርስ/ኃይል ባለመሆኑ የምንነጋገርባቸው ኃይሎች የተለያየ ሀሳብ እና አቋም ይዘው ስለሚመጡ ነው።

የሆኖ ሆኖ በእኛ በኩል የኦሮሚያ መንግሥት ያቀረበው ሀሳብ ሳይሆን እንደ ፓርቲ ተወያይተን ወስነን ፤በምክትል ፕሬዚዳንት የሚመራ ኮሚቴ አቋቁመን የዛን ተቀጥያ ነው የኦሮሚያ መንግሥት የገለጸው ወይም ያብራራው። እናም ሰላሙን የሚጠላ ኃይል አይኖርም ብዬ አስባለሁ፤ጤነኛ ሰው እና ኢትዮጵያዊ እስከ ሆነ ድረስ። ምክንያቱም ብዙ ሰው እየሞተ እየተፈናቀለ ስለሆነ። ሰላሙን ሁሉም ይፈልገዋል የሚል እምነት አለኝ። በእኛ በኩል ግን ጉዳዩ በሰላም እንዲፈታ አበክረን እንሠራለን።

ጉዳዩ በሰላም እንዲፈታ አበክረን እየሠራን ተጨማሪ መፈናቀልና መግደል እንዳይኖር ኃይሎቻችን እዚያ አካባቢ በስፋት ጠንከር ያለ ሥራ እየሠሩ ይገኛሉ። ለሰላሙ ግን ጥርጣሬ መኖር የሌለበት ለሸኔም፤ ለቅማንትም፤ ለአገው ሸንጎም ፤ለቲፒኤልኤፍም ፤ለአነግም ለሁሉም የታጠቁ ኃይሎች የኢትዮጵያ መንግሥት መግለጽ የሚፈልገው ጉዳዩን በንግግርና በምክክር መፍታት ነው። መገዳደል አይጠቅምም የሚል የጸና አቋም አለን። የሚያዋጣንም እሱ ይመስለኛል። የሸኔ ጉዳይ። በዚህ አግባብ ቢታይ በጥቅሉ ለተከበረው ምክር ቤት ወደ ኢኮኖሚ ጉዳይ ከመሄዴ በፊት ላስገነዝብ፤አደራ ልል የምፈልገው ነገር የዓለም ጉዳይ በፍጥነት እየተቀያየረ ነው፤የእኛም ቀጠና ሁኔታ በጣም በፍጥነት እየተቀያየረ ነው። በእኔ ግምት በሚቀጥሉት ስድስት ሰባት ዓመታት ቢበዛ እስከ 2030 ድረስ የዓለምን አምሳ፤ ስድሳና ሰባ ዓመታት የሚወስኑ ጉዳዮች ይፈጠራሉ ብዬ አስባለሁ። የሚቀጥሉት አምስት፤ስድስት ዓመታት በጣም ወሳኝ ጊዜዎች ናቸው።

በርካታ ነገሮች የሚቀያየሩበት ጊዜ ነው። የኢኮኖሚው፤ የሰላሙ፤አጠቃላይ የመንግሥታት ግንኙነት፤የሚሳየው ነገር በዓለም ላይ አዲስ ኩነት ሊፈጠር ይችላል። በእንደዚህ ጊዜ ሰብሰብ ያሉ አርቀው ያሰቡ ሀገራት ይሻገራሉ፤ወለም ዘለም ያሉ ሀገራት ይበተናሉ። ይህቺ አምስት ስድስት ዓመታት በከፍተኛ ጥንቃቄ እንደ ሀገር የምንቀጥልባት ጊዜ መሆኑን የተከበረው ምክር ቤት እንዲገነዘብ በአንክሮ እጠይቃለሁ። ዓለም ላይ የተፈጠረው አጠቃላይ ሾክ እንደ እኛ ያሉ ሀገራትን በጎናቸውም ካለፈ ያንሸራትታቸዋል። በኢኮኖሚውም፤በዲፕሎማሲውም በሌላውም ዘርፍ።

እና ሰብሰብ ብለን በአዲስ እይታ እና አስተሳሰብ ነገሮችን መፍታት ብንለምድ ጥሩ ነው። በሳይኮሎጂ(በስነ ልቦና ) ኢንስቴሊንግ የሚባል ኢፌክት አለ። ይህ ኢፌክት ችግሮችን በቀደመው መንገድ ፤በቀደመ እይታ ለመፍታት መሞከር ነው። ይህ አሁን አያዋጣንም ፤አዲስ እይታ ፤አዲስ መንገድ ያስፈልገናል። በዛ መንገድ ብንሄድ ተባብረን ችግሮችን ለመፍታት፤ ሕዝቦችን ለማቀራረብ ያስችለናል። ወደ ልማት ለመሄድ ያግዘናል። ነገሮችን በሃሳብና በአስተውሎት ብንመራ የሚሻል ይመስለኛል።

ለምሳሌ መንግሥት ኢትዮጵያን ሊበትን ይፈልጋል፤ ወይም አንዳንዴም ይገነጥላል የሚባለው ሃሳብ አለ በመደመር መንገድ ላይ እንዳስቀመጥኩት እኛ የምንፈልገው ከኢትዮጵያ አልፎ ሚና የሚጫወት ትውልድ ማፍራት ነው። ሃሳባችን በንግግር ብቻ ሳይሆን በጽሑፍም የሰፈረ ነው። ለዛ ጊዜ አናባክን። በግድ ኦሮሞዎች ኢትዮጵያን ትገነጥላላችሁ የሚለውን አስተሳሰብ እንተወው። እኛ ኢትዮጵያን ስለምንፈልጋት አንገነጥልም። ለእኔ ከወላይታው፤ከጉራጌው ከሌላውም ተነጥሎ መኖር ያዋጣል የሚል እምነት የለኝም። ይህንን ሃሳብ ትተን ዘኒው ኖርማል የሚለው አስተሳሰብ ተቀብለን ፤ተግባብተን መኖር እንደምንችል ብንወያይ ጥሩ ነው። ይህንን ዘፈን ብንተወው ጥሩ ነው። አይጠቅመንም።

አሁን ኢትዮጵያ የምትገነጠልበት ታሪክ አልፏል። አሁን እንዴት ነው በዴሞክራሲያዊ መንገድ ተከባብረን የምንኖረው፤ ሳንገዳደል፤ ሳንገፋፋ፤ ተከባብረን የሚለውን ጉዳይ ብንመክርበት ፤ብንወያይ፤ ችግር ካለ በጋራ ብንፈታ፤ አማራጭ ሃሳብ ካለ ብናይ የሚሻል ይመስለኛል። እንጂ ለኢትዮጵያን ከበቂ በላይ የሆነችና አቅምም ያላት ሀገር መሆኗን መረዳት ይገባል። ከዛ ያነሰውን ነገር እምብዛም የሚፈልግ መንግሥት ይኖራል ብዬ አልገምትም።

በድምሩ የሚታይ ለውጥን ሳንክድ፤ የሚታይ፤ የሚጨበጥ ውጤትን ስናክድ፤የጎደለውን ነገር ካለ በልኩ ሳናጋንን በልኩ እያነሳን እያረምን ብንሄድ ለጋራ ሀገራችን ይጠቅማል የሚል ሃሳብ ነው ያለኝ።

**የተከበራችሁ የምክር ቤት አባላት፤**

ከሰላምና ደህንነት እንዲሁም ማህበራዊ ጥያቄዎች በተጨማሪ ኢኮኖሚን በሚመለከት በርከት ያሉ ጉዳዮች ተነስተዋል። አይቲንክ/በኛ እይታ ዋናውን በደንብ ልናየውና ልንነጋገርበት የሚገባው ጉዳይ የዚህ የኢኮኖሚ ጉዳይ ይመስለኛል። የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በጥቅሉ በአኃዝም በመስተጋብርም እያደገ መጥቷል። እራሱ በጂዲፒ ብቻ ሳይሆን ከዓለም ጋር ያለው መስተጋብር እያደገ እየሰፋ መጥቷል።

ከዓለም ጋር ያለው መስተጋብር እየሰፋ ሲሄድ በዛው ልክ ዓለም ላይ ያለው ሾክ/የኢኮኖሚ መንገጫገጭ በጥሩም በመጥፎም ይጎዳዋል ማለት ነው። ከዚህ ቀደም የነበረን ከአለም ጋር ትስስር እያደገ እየሰፋ በሚሄድበት ሰዓት ሌላ ቦታ የሚፈጠር ችግር በቀጥታ የኛን ኢኮኖሚ የሚጎዳ ይሆናል።

ላለፉት መቶ ዓመታት የዓለም ኢኮኖሚ አራት ፈተናዎች የአለምን ኢኮኖሚ የዓለም ፈተናዎች / ጋሬጣዎች ገጥመውታል። አምስተኛው አሁን ዓለምን እያንገዳገደ ይገኛል። አንደኛው በ1929 የተከሰተው፤ ዘግሬት ዲፕሪሼሽን የሚባለው ነው። ይሄ በወቅቱ የነበረውን የዓለምን ሁኔታ አናግቶ በጣም ከፍተኛ የሆነ የሰልፍ ለውጥ አስከትሏል። ሁለተኛው 1987 የነበረው ፤ዘብላክ ማንዴይ ክራሽ የሚባለው ነው። እሱም እንደዚሁ ከፍተኛ ዓኢኮኖሚ መናጋት ፈጥሯል። ሶስተኛው በ2000 የነበረው ዘዶት ኮም ክራሽ የሚባለው ነው።

አራተኛው የቅርብ ጊዜ ትውስታችን የሆነው የ2008



ፎቶ - ፀሐይ ንጉሤ

ወቅታዊና ልዩ ልዩ

# ወቅታዊ



የፋይናንሻል ክራይስስ ነው። እነዚህ አራት ዋና ዋና ኩነቶች መነሻቸው ከአንድ አካባቢ ቢሆንም መዳረሻቸውን ግን ሁሉንም አገር በመስተጋብሩ ልክ ጎድተዋል። አሁን እያጋጠመን ከ2008ቱ የሚለየው የ2008 የፋይናንሻል ክራይስስ ያጋጠመው ዋናው ኤርያ/አካባቢ የንብረት ዋጋ በተለይ ሪልስቴት መመታቱ ነው። እዛ ሞርጌጅ ጋር ብድር ጋር ተያይዞ ያሉ ባንኮችንም በከፍተኛ ደረጃ ያዳከመና በኋላ መንግሥታት የታደጓቸው ቢሆንም ከፍተኛ የፋይናንሻል ክራይስስ/ውድቀት ፈጥሯል።

አሁን እያጋጠመን ያለው ችግር ለመረዳት የእነዚህ የቀደሙ አራት ችግሮች መነሿቸው ምን ነበረ፣ እንዴት ተፈጠሩ አሁን ቢፈጠሩ እንዴት መከላከል እንችላለን የሚለውን ነገር ለማወቅ እንደ ባክግራውንድ ያግዛሉ። የኢኮኖሚ ዲፕሪሼሽን የሚያጋጥመው በመሠረታዊነት ሶስት ነገር ሲጋጥም ነው። አንደኛው ከፍተኛ እዳ ነው። እንደ አገር መክፈል ወደማይቻል ደረጃ ውስጥ የሚያስገባ እዳ ሲኖር ፤ይህ ለየትኛማውም አገር የሚሠራ ፎርሙላ ነው።

ሁለተኛው የአሴት ዋጋ መውረድ ነው። አንድ ሰው አንድ ሚሊዮን ብር ያወጣል ብሎ የሚያስበው ቤቱ በሳምንት በወር ጊዜ ውስጥ ሰባት መቶ ሺ እና ከዛም በታች እየወረደ ሲሄድ ያለው የሀብት ዋጋ/ ቫሊው እየቀነሰ ሲሄድ ነው። ሶስተኛው ደግሞ ገቢ/ ኢንካም ሲቀንስ ነው። እዚህ ላይ ኢንፍሌሽን በከፍተኝ ሁኔታ ሲጨምር ፤ ኢኮኖሚን ማናጋቱ ለቁጥጥር በማይመች ደረጃ ሲደርስ ነው።

አሁን በዓለም ላይ ያለው አምስተኛው እየተፈራ ያለው የኢኮኖሚ ችግር ኤግዛክትሊ 2008 ካጋጠመው ፋይናንሻል ክራይስስ አንድ አድርገን ምናየው አደለም። በሂደቱም በውጤቱም በሚያመጣው ውጤት አንድ አድርገን የምናየው አደለም። ነገር ግን ምልክቶቹ ፤አንደኛ ሠራተኛ ቅነሳ ፤በሺ የሚቆጠሩ የአይቲ ኩባንያዎች ዋና ዋናዎቹን ጨምሮ በመቶ ሺ የሚገመት ሠራተኛ እየቀነሱ ነው።

በዓለም ላይ ሠራተኛ ቅነሳ እየሰፋ መጥቷል። ሁለተኛ የባንክ ውድቀት ነው። በአሜሪካ በዌስት ኮስትና በኢስት ኮስት ሁለት ትላልቅ ባንኮች በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ ወድቀዋል። በዌስት ኮስት የወደቀው ሲሊሊ የሚባለው ባንክ ለቴክኖሎጂ የቀረበ ስታርት አፕ የሚያግዝ ፤ በ2020 ትርፋማ የሚባል ትልቅ ባንክ ነው። ከካሊፎርኒያ አልፎ በእንግሊዝ ሀገርም ቅርንጫፍ (branch) አለው። ትልቅ ባንክ ነው። በአጭር ጊዜ ውስጥ ወድቆ አሁን አሴቱን በከፍተኛ ደረጃ ዝቅ አድርጎ እየሸጠ ይገኛል። ሁለተኛው በካሊፎርኒያ በስፋት የሚታወቀው የሲግኒቸር ባንክ ፤በኒውዮርክ አካባቢም በስፋት የሚንቀሳቀስ ባንክ ነው። ትልልቅ ከሚባሉ ባንኮች አንዱ ነው። እሱም እንደዚሁ ተመቷል። ችግሩ በአሜሪካ አልቆመም። በስዊዝም ባንኮች መሸጥ ጀምረዋል።

አሁን በቅርቡ ደግሞ በተለይ ትናንት ትልቁ የደች ባንክ ከፍተኛ አደጋ ሊያጋጥም የሚችል ስጋቶች በደንበኞች፣ በገንዘብ አስቀማጮች ምልክቶች ታይተዋል። ይህ ባንክ በዓለም ትላልቅ ከሚባሉ ባንኮች አንዱ ነው። በርግጥ ስጋት መጠኑ ዝቅተኛ እንደሆነ ባንኮቹ እየተናገሩ ቢሆንም በከፍተኛ ደረጃ ግን ያለው አሴት እየቀነሰ መጥቷል። የነዚህ ባንኮች መንኮታኮት ፤ዋና ዋና ባንኮች፣ ትላልቅ ባንኮች ሲጎዱ ፤ችግሩ በቀጥታ እኛን ያደቀናል።

ሦስተኛው እዳ መክፈል ነው። እዳ መክፈል ድሮ ለአፍሪካ ሀገራት፣ ለእኛ በማደግ ላይ ላለን ሀገራት ነበር እንደጉዳይ የሚነሳው። አሁን ግን የዓለም ኢኮኖሚ አንደኛ፣ ሁለተኛ፣ ሶስተኛ... የሚባሉትም ጭምር በከፍተኛ ደረጃ እየተፈተኑ ነው። ሎካል ገቨርመንቶቻቸው/የአከባቢ አስተዳደሮች የተበደሯቸውን ትላልቅ ብድሮች መክፈል ችግር እየገጠማቸው ነው። እነሱ መክፈል ሲቸገሩ ወደኛ የሚፈሰው ሀብት በመጠኑ ይቀንሳል ማለት ነው።

አራተኛ ኢንፍሌንሽን ነው። እናንተም አንስታችሁታል ኢትዮጵያን ጨምሮ በርካታ ሀገራት ላይ ኢንፍሌንሽን ስጋት ነው። በኢንፍሌንሽን ደግሞ በጣም የተጋነነ ወደ ሀይፐር ኢንፍሌንሽን የገባባቸው ሀገራት ደግሞ አሉ። ለምሳሌ አርጀንቲና መቶ ፐርሰንት (በመቶ) ኢንፍሌንሽን ጨምሯል። በጣም በርካታ ሀገር ውስጥ በዚህ አደጋ ኢኮኖሚያቸው ብቻ ሳይሆን መኖር (survival) በራሱ ችግር እየሆነ መጥቷል።

ለምሳሌ በቅርቡ በሊባኖስ (መካከለኛው ምስራቅ ያለች ሀገር ነች) ያጋጠመውን ሰምታችሁ ከሆነ 100 ሺ የሊባኖስን ገንዘብ በአንድ ዶላር ተመንዝሯል። አንድ ሚሊዮን የሊባኖስን ብር ይዞ ሂዶ ሰው በ10 ዶላር ይመነዝራል። መካከለኛው ምስራቅ የምትገኝ ሀገር ናት። እዚህ 70 እና 75 በመቶ ወይም ፐርሰንት የሀገሪቱ ሕዝብ በከፍተኛ ችግር ውስጥ እንዳለ ይነገራል።

እነዚህ ሁሉ ጉዳዮች በሠራተኛ፣ በኢንፍሌንሽን፣ በባንኮች መውደቅ፣ እዳ መክፈል አደጋ መሆን፣ የውጭ ምንዛሪ ፍላጎት ከፍተኛ በመሆኑ የሎካል ከረንሲ ዋጋ በከፍተኛ ደረጃ ማሽቆልቆል፤ እኛ ልክ ከ20-30 ወደ 50-60 ገባ መቶ ሊገባ ነው የነበረው አይነት ጥያቄ አሁን 100 ሺ ብር በአንድ ዶላር መመንዘር ያህል አደገኛ ነገር ማለት ነው።

እነዚህ ምልክቶች በዓለም ላይ በስፋት ታይተዋል። በቅርቡ አይኤምኤፍ ያወጣውን የዓለም ኢኮኖሚ እይታ (IMF world economic outlook) አይታችሁ ከሆነ በጣም የሚያስፈሩ ዳታዎች / ወይም መረጃዎች በውስጡ ይታያሉ። እንደምክንያት ያስቀመጠው አንደኛ የሩሲያና የዩክሬን ውጊያ የብዙ ሀገራትን ኢኮኖሚ ጎድቷል። የንግድ ሥርዓት ሠንሰለት በጣጥሷል። ችግር አስከትሏል የሚል ነው።

ሁለተኛው ኮቪድ 19 ለሁለተኛ ጊዜ ስላገረሸ በተለይ ቻይና አካባቢ ያለውን የጥሬ እቃ አቅርቦት ጎድቶታል፤ እንቅስቃሴ ጎድቷል። በዚያ ምክንያት ከፍተኛ ኢንፍሌንሽን አጋጥሟል። ኢንፍሌንሽን አጋጠመ ብሎ አይኤምኤፍ ባወጣው የworld economic outlook (የዓለም ኢኮኖሚ እይታ) ላይ በአሁኑ ጊዜ 184 ሀገራት በኢንፍሌንሽን ችግር ውስጥ ነው ያሉት። ከነዚህ ውስጥ 110 ሀገራት ከደብል ዲጂት በላይ ወይም ከ10 ፐርሰንት በላይ ኢንፍሌንሽናቸው አድጓል። 110 ሀገራት። ለዚህ ነው መስተጋብሩ ምን ያህል ጉዳት እንዳለው ቀድሜ ለማንሳት የሞከርሁት።

በተለይ በዚህ ውስጥ ኢትዮጵያውያን ብንማር ጥሩ የሚሆነው ከ1 ነጥብ 5 ሚሊዮን ሕዝብ በታች ያላቸው 37 ሀገራት በዚህ ኢንፍሌንሽን ሕልውናቸውን አደጋ ውስጥ የሚያስገባ ችግር አጋጥሟቸዋል። ምን ማለት ነው? ይሄ የሀገር ቁጥር በከፍተኛ ደረጃ ያነሰ ሲሆን፣ የሀገር market (ገበያ) የጠበበ ሲሆን ጎጂ ስለሆነ።

ወደ ቅድሙ ጥያቄ ልመለስና መገንጠል፣ መገንጠል፣ መገንጠል የምንል ሰዎች ጉዳት እንጂ ጥቅም የለውም። ሰፋ ያለ ማርኬት ነው የሚያዋጣን። አሁን በተጨባጭ ዓለም ላይ እያጋጠመ ያለው ችግር እሱ ስለሆነ። በእርግጥ በቁጥር ብቻ ሳይሆን ሰው ፕሮዳክቲቭ መሆን አለበት። በቁጥር በጣም እያነሱ መሄድም በእንደዚህ አይነት አደጋ ጊዜ በከፍተኛ ደረጃ ሕልውናን ይገዳደራል። ያደጉ ሀገራት አሁን ያለውን እየመጣ ያለውን ችግር ሊፈቱ እየሞከሩ ያለበት መንገድ ምንድ ነው? ከእነርሱ ምን እንማራለን ምንስ ማድረግ እንችላለን የሚለው ለማየት ለምሳሌ የአውሮፓ ኅብረት ለአባል ሀገራቱ 190 ቢሊዮን ዶላር ገደማ ወደ ኢኮኖሚ እንዲገባ አድርጓል ችግር አጋጥሟል ብሎ።

የጀርመን መንግሥት ከ200 ቢሊዮን ዶላር በላይ ኢኮኖሚ ውስጥ ጨምሮ ያለውን ችግር ለመፍታትና ለማስተካከል ሞክሯል። የእንግሊዝ መንግሥት አሁን ከሰሞኑ 130 ቢሊዮን ዶላር ወደ ኢኮኖሚ እንዲገባ ወስኗል። የአሜሪካ ለባንኮቹ ብቻ ከሁለቱ ባንኮች መውደቅ በኋላ ከ30 ቢሊዮን ዶላር በላይ ኢኮኖሚ ውስጥ ለማስገባት ሞክረዋል።

በአንድ በኩል ከሪዘርቭ ወይንም ከሌላ ምንጭ ገንዘብ ኢኮኖሚው ውስጥ ያስገባሉ። በኩል ደግሞ ኢንፍሌሽን እየበዛ ስለሆነ ብር ለመሰብሰብ ኢንተረስትሬት /የወለድ ምጣኔን/ እንጨምራለን ይላሉ። እነዚህን ባንኮች አንደኛ የጣላቸው ጉዳይ ረዘም ላለ ጊዜ በአነስተኛ ወለድ ቦንድ ገዝተዋል ወለድ ምጣኔ ሲጨምር በከፍተኛ ደረጃ ሃብታቸው ይወርዳል። ይወድቃሉ።

የአሜሪካን ብሔራዊ ባንክ ሪዘርቭን ጨምሮ ሌሎቹም ኢንፍሌሽን ከመከላከል ያለው መፍትሔ የወለድ ምጣኔ መጨመር ነው የሚል አቋም ይዘዋል። እነርሱ የወለድ ምጣኔ ሲጨምሩ በፍጥነት ኢንቨስትመንት ይቀንሳል ማለት ነው። አብዛኛው ሃብት ያለው እዛ ስለሆነ። ይህ ነገር የ 2008 ባይመስልም እኛን በከፍተኛ ደረጃ ይፈትነናል። የተከበረው ምክር ቤት አሁን ካለው ላይ መዘጋጀት አለበት። እየመጣ ያለው ጎርፍ ኃይለኛ ነው።

ዝም ብለን ጤፍ ጨመረ ስንዴ ጨመረ ብቻ ሳይሆን ዓለም ላይ እየመጣ ያለው እንደ ኮሮና አደገኛ ጉዳይ ነው። ኢትዮጵያውያን ማምለጥ ከፈለግን/ መፍትሔው የጀመርናቸውን ኢንሺየቲቮች በተሟላ መልኩ መሥራት ብቻ ነው ፤። የዓለም ኢኮኖሚ በ 2021 እድገቱ ስድስት ነጥብ አንድ በመቶ ነው። በዓመቱ በ 2022 እድገቱ ሦስት ነጥብ አራት በመቶ ነው። በዚህ ዓመት ሁለት ነጥብ ዘጠኝ ነው የሚገመተው። አጠቃላይ የዓለም እድገት በሦስት ዓመት ውስጥ እያሽቆለቆለ ነው የመጣው።

ከዚህ ውስጥ ያደጉ አገራትን ብቻ ነጥለን ብንወስድ በ2022 ሁለት ነጥብ ሰባት በመቶ ያደጉ አሁን አንድ ነጥብ ሰባት በመቶ እድገት ሊመጣ እንደሚችል ነው አይ ኤም ኤፍ ያስቀመጠው። ይህ ማለት እንደ እኛ አይነት ኢኮኖሚ ሳይሆን ግዙፍ ኢኮኖሚ ስለሆነ አንድ በመቶ ሲቀንስ በከፍተኛ ደረጃ የዓለም እድገት ይቀንሳል ማለት ነው። አውሮፓን ብቻ ነጥለን ብንወስድ በ 2022 ሶስት ነጥብ አምስት በመቶ ነው ያደጉት። ዘንድሮ ግን ዜሮ ነጥብ ሰባት በመቶ ነው የሚጠበቀው። ምን ያህል እንደቀነሰ ማሰብ ይቻላል።

የአውሮፓ እድገት ሲቀንስ እዛው የሚቀር ሳይሆን ባለን መስተጋብር ምክንያት እኛም ላይ ከፍተኛ ጫና ያሳድራል። በአይ ኤም ኤፍ የዓለም ኢኮኖሚ ምልከታ መሠረት ከሰሃራ በታች ያሉ ሀገራት ከሶስት ነጥብ ስምንት በመቶ ያላነሰ እድገት ያመጣሉ ብሏል። ለኢትዮጵያ ሁላችሁም እንደሰማችሁት አምስት ነጥብ ሰባት በመቶ እድገት እንደሚኖር ገምቷል። ሰምታችሁታል ብዬ ነው ግምቱን።

ነገር ግን የእኛን እድገት የሚፈታተኑ ችግሮች ምንድ ናቸው ያላችሁ እንደሆነ አንደኛው እዳ ነው። ይህ መንግሥት 59 በመቶ የጂዲፒ እዳ ነው የተቀበለው የፖለቲካ ፣የመገንጠልና የዘር እዳ ብቻ ሳይሆን የብድር እዳም ተቀብሏል። ባለፉት አምስት ዓመታት እኛ አንድ ዶላር ኮሜርሻል ብድር አልወሰድንም። ይህን ሳንወስድ ቀድሞ የነበረው እዳ የክፍያ ጊዜው ደርሶ ባለፈው ዓመት ብቻ አንድ ነጥብ ሰባት ቢሊዮን ዶላር ከፍለናል። እኛ የተበደርነው ሳይሆን እንደ አገር የወሰድነው ስለሆነ ወደ ዲፎልት ውስጥ እንዳንገባ በሚል እዳን በአግባቡ ለማስተዳደር ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል። የእዳ ክፍያ ደርሶ በርካታ ሃብት ለዚሁ ሲውል የሚፈለገው ልማት እንዳናመጣ ያስቸግራል። ሁለተኛው የዋጋ ንረት ነው። ሦስተኛ የመሠረተ ልማት ክፍተት ነው።

የሎጀስቲክስ አለመያያዝ ችግር ኢኮኖሚያችንን በከፍተኛ ደረጃ ጎድቶታል። አንድ ቦታ ምርት አለ ሌላ ቦታ ፍላጎት አለ ይሄንን አለማገናኘት የሚያስከትለው ፈተና ነው። አራተኛውና ዋነኛው ልንሠራበት የሚገባ በፍላጎትና በአቅርቦት መካከል ያለው ልዩነት ነው። ጎን ለጎን ነው የምንሠራው ያልንበት ዋናው ምክንያት ምርትን በማብዛትና በማበራከት ከፍላጎት ጋር ያለውን እጥረትና ሽሚያ መቀነስ እንችላለን በሚል ነው።

እነዚህ ጉዳዮች በከፍተኛ ደረጃ ከዓለም ቀጥሎ የእኛን ኢኮኖሚ ይገዳደራሉ። የዋጋ ንረትን በሚመለከት በመጀመሪያ የእኛ ኢትዮጵያ ውስጥ ያጋጠመው የዋጋ ንረት ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን እንደሚጎዳ እየጎዳም እንዳለ በጽኑ እንገነዘባለን። የማንገነዘበው ጉዳይ አይደለም። ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ሰዎች በብዛት ይጎዳሉ። ምን አመጣው ይሄ ጉዳይ ከተባለ ከዚህ በፊት እንደተነሳው ላለፉት ሃያ ዓመታት በተከታታይ የኢትዮጵያ የዋጋ ግሽበት እያደገ ነበር። ከእድገቱ ጋር በተወሰነ ደረጃ አብሮ የሚያድግ የዋጋ ግሽበት ነበር ይህንን ልንገታ አልቻልንም።

ሁለተኛ አምራችና ሸማች መካከል ያለውን የፍላጎትና የአቅርቦት ርቀት ማስተካከል አልቻልንም። አምራች እያለ ሸማች ለብቻ የሚቸገርበት ሁኔታ ተፈጥሯል። ሦስተኛ ከውጪ የምናስገባቸው የዋጋ ግሽበቶች አሉ። የእኛ ያልሆኑ ውጪ ባለው ሁኔታ አንዳሉ የምናስገባቸው የዋጋ ግሽበቶች። ከዚህ ውጪ ጦርነት ነበር ፤ድርቅ አለ ጦርነትና ድርቅ እያሉብን ደግሞ የአለም እርዳታ ሰጪ ሀይሎች ለኢትዮጵያ ድሮ ከሚያደርጉት እርዳታ በእጅጉ ቀንሰዋል። ምክንያቱ ብዙ ቢሆንም።

የከተማ ፍልሰትም እንደዚሁ ወደ ከተማ የሚደረግ ፍልሰት በጣም በዝቷል። ከተሞች አካባቢ የሚኖረው ህዝብ ቁጥር እያደገ በመምጣቱ ፍላጎቱ እያደገ መጥቷል። እነዚህ ጉዳዮች ያመጡት የዋጋ ግሽበት ዝቅተኛ ኑሮ ያላቸውን የህብረተሰብ ክፍሎች ኑሮ በከፍተኛ ደረጃ ስላነሳቀለ እንደ መፍትሄ የወሰድነው አንደኛ አቅርቦቱን መጨመር ሁለተኛ በጀት ስንበጅት እንደሚታወቀው ሀምሳ ዘጠኝ በመቶ በጀቱ ለድህነት ቅነሳ የሚውል ነው።

ወቅታዊና ልዩ ልዩ

# ወቅታዊ



ከዚህ ውጪ በከተሞች በተለይ በአዲስ አበባ መመገቢያ ቦታዎች በማዘጋጀት ለተወሰኑ ምግብ ለሌላቸው ዜጎች ቢያንስ በቀን አንድ ጊዜ ምግብ ማብላት የሚቻልበትን ሥርዓት፤ በዓመት አንዴ ሁለቴ ደግሞ ምግብ በማጋራት ያለንን በመስጠት የማጋራት ሥርዓት ላይ እንገኛለን። በዚሁ እግረ መንገድ ለማንሳት የረመዳንና የፋሲካ ወር ስለሆነና አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ እነዚህን ሁለት ጾሞች እየጾመ ያለ ስለሆነ በሚቀጥለው ሳምንት መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ካለው ምግብ በማጋራት ያነሳቸውን ሰዎች የሚያስብበት ጊዜ እንዲሆን፤ ሙስሊሙም ክርስቲያኑም ተባባሪ እንዲሆን እዚህም ያላችሁት ባላችሁ አቅም በጎረቤት አንድ ምግብ ለሚቸገር ሰው በማጋራት በኑሮ ውድነት ያለውን ስቃይ በአብሮነት ለመከላከል ጥረት እንድናደርግ ጥሪ አቀርባለሁ።

እኛ ከምግብ ማጋራት በተጨማሪ ከፍተኛ ድጎማዎችን እያደረግን ነው። ለነዳጅ ባለፉት ስምንት ወራት ከሀምሳ ቢሊዮን ብር በላይ የኢትዮጵያ መንግስት ደጉሟል። የአሰራር ችግር ያለበት ቢሆንም 173 ሺ ገደማ ተሽከርካሪዎች ድጎማ ይጠቀማሉ። ማዳበሪያ አምና 15 ቢሊዮን ብር የደጎምን ሲሆን ዘንድሮ 21 ቢሊዮን ብር እየደጎምን እንገኛለን። ይህ ሁሉ የሚደረገው ምርት በማብዛት አነስተኛ ገቢ ያላቸውን ዜጎች ተጎጂነት ለመቀነስ የሚደረግ ጥረት ነው።

በፍራንኮ ቫሉታ ያስገባናቸው ዘይት ስኳር የመሳሰሉ ጉዳዮች ከአስር ቢሊዮን ብር በላይ ገቢ ልናገኝ የሚገባንን አሳጥተውናል። እነዚህ ሁላ ጥረቶች የደሀ ቤት አፍርሶ መገንባት፣ ዳቦ ፋብሪካ በየቦታው መገንባት የመሳሰሉት ጉዳዮች የሚደረጉት ቢያንስ ዳቦ መብላት የሚችሉ ዜጎች ለመፍጠር የሚደረግ ጥረት ነው። ይሄ ጥረት ካለው ችግር አንጻር ውስን ስለሆነ በስፋት ሊሠራ ስለሚገባ ውጤቱ እምብዛም አይደለም።

ታስታውሱ ከሆነ ባለፈው ዓመት ዘመን መለወጫ የአዲስ ዓመትን አስታኮ ዋጋ ሊንር ስለሚችል እንደመንግሥት እቅድ ወጥቶ ኮሚቴ ተቋቁሞ ሰፊ ምርት ካለበት ገዝተን ከተማ ውስጥ ለማቅረብ በመቻላችን ዋጋ ልናረጋጋ ሞክረን ነበር። አሁን ግን ሰፊ ምርት ስላለ እንደዚህ አይነት ዝግጅት ስላላደረግን በሰሞኑ አዲስ አበባ ላይ የምታውቁት ከፍተኛ የዋጋ ንረት አጋጥሟል። ከፍተኛ!

ይሄን ለመፍታት ልክ እንደ ዘመን መለወጫው ምርት እያስገባን ነው ያለነው። ትናንትናም በርከት ያሉ ምርቶች እየገቡ ነበረ። በሚቀጥለው ሳምንትም ይጠናከራል ይሄ። የተከበረው ምክር ቤት ግን መገንዘብ ያለበት ኢትዮጵያ ውስጥ የምርት እጥረት ስላለ አይደለም ዋጋ የጨመረው፤ አስጠንተን ነበር ባለፉት ሁለት ሳምንታት። ከአዲስ አበባ በቅርብ ርቀት ባሉ የአርሶ አደር ቤቶች እስከ አንድ ሺ ኩንታል በቤቱ ያስቀመጠ አርሶ አደር አለ። ይሰማሉ አሁን ስናገር፤ በመቶዎች ኩንታል ሆልድ ያደረጉ አሉ። ዋጋ ሊጨምር ይችላል ብለው ያቆዩ ሰዎች በጣም በስፋት አሉ።

ስንዴ ካሰብነው በላይ ነው ያመረትነው የስንዴ ችግር ኢትዮጵያ ውስጥ የለም፤ በቂ ምርት ነው ያለው። በዚሁ አጋጣሚ የኢትዮጵያን አርሶአደር ማሳሰብ የምፈልገው ነገር መንግሥት ማሽነሪ ቢያመጣ፤ ማዳበሪያ ቢደጉም፤ በሙያ ቢያግዝ፤ የኢሪጌሽን ሥርዓት ቢያበጅ እና አርሶ አደሩ እንዲያመርት በጣም ብዙ ግብዓቶች የሚደግፍ ቢሆንም በአርሶ አደር ጥረት የሚገኘው ምርት ምርታማ የሚሆነው የኢትዮጵያ አርሶ አደር ፈርነስም ሲኖረው ነው። ከተሜ ያለው ሸማች እንዲራብ ከፈቀደ ያው በሚቀጥለው ዓመት ዝናብም ሊቀር ይችላል ማለት ነው። መጠንቀቅ ያስፈልጋል፤ በጣም ብዙ ምርት ይዘን ሰዎች እንዲቸገሩ ማድረግ ተገቢ አይደለም።

ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የስንዴ ዋጋ ነግሬያችኋለሁ ኢትዮጵያ ኤክስፖርት አደርጋለሁ ስትል አካባቢ ሀገራት ላይ ይፈሳል ብያችሁ ነበር። የሆነው እንደሱ ነው፤ አፍስሰውታል አካባቢ ላይ። የእኛ የስንዴ ዋጋ ኤክስፖርት እንኳን ያደረግንበት ዋጋ ኬንያ ሱዳን ካለው ይበልጣል። በውድ ዋጋ ነው የሸጥነው። እና አርሶ አደሩ የክረምቱ በጣም በርካታ ምርት አግኝተናል። አሁን በጋ ከአንድ ሚሊዮን ሄክታር በላይ ነው ያረስነው፤ ሀርቨስት እያደረግን ነው። በኋላ ማስቀመጫም እንቸገራለን።

ከስር ስር ወደ ውጭም ሀገር ውስጥም የሚሸጥበትን መንገድ መፍጠር ያስፈልጋል። ምክር ቤት አባላት በየወረዳችሁ ነበራችሁ። አይታችኋል ምርት ምን እንደሚመስል፤ ይሄ እንደድሮው የሪፖርት ጉዳይ ሳይሆን ፕራክቲካሊ መሬት ላይ ያለ ነገር ነው። ይሄ ገበያ እንዲወጣ በመንግሥት በኩልም በሕዝብ በኩልም ሰፊ ሥራ ይጠበቃል።

ምርት አምጥተን ሰንደይ ማርኬት አስፋፍተን አርሶ አደርና ሸማች መካከል ያለውን ሰንሰለት ቀንሰን በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ገቢያቸው ያነሰ ሰዎችን ማገዝ ያስፈልጋል። ግን ምርት ስለሌለ ነው የሚባለው ነገር ትክክል አይደለም። እና ተረቱም ትክክል አይደለም። የሌላትን አላበደረችም ያላትን ነው የሸጠችው፤ ይልቁንስ የተከበረው ምክር ቤት ምናልባት በደንብ ቢያስብ ጥሩ የሚሆነው ባለፉት ሀምሳ ስልሳ ዓመታት ስንዴ በማስገባት የምትታወቅ ሀገር ለመጀመሪያ ጊዜ ከለውጡ በኋላ ለስንዴ ዶላር ያላወጣነው ዘንድሮ ነው። አምና እና አቻምና እንኳን ብር አውጥተናል። ይሄን ልንኮራበት የሚገባ ይመስለኛል።

የታሪክ እጥፋት የምንለው ስንዴ ለማኝ ሳይሆን ስንዴ አምራች መሆናችንን ማሳያ መንገድ ነው። እንግዲህ ስንዴ አምራች መሆናችንን ያው በሚዲያ እንደምትሰሙት ብዙ ሀገራት እየመሰከሩ ነው። የእኛ ነገር ሥራው ሲጀመር ምን ያደርጋል፤ ስንዴ አሁን ምን ያደርጋል ውጊያ ላይ እያለን አያስፈልግም ማለት፤ ምርቱ ደግሞ ሲመጣ የሌላትን አበደረች ማለት ነው የሚመጣው። እንደዛ አይደለም ስንዴ ላይ ትልቅ ድል ነው የሠራነው የሚያኮራ፤ የሚቀር ነገር አለ። በንግድ ሥርዓቱ ይስተካከላል።

ራሽያ ስንዴ ኤክስፖርት ስትጀምር ከፍተኛ ፍላጎት ነበራት በሀገሯ፤ ኢምፖርት ታደርግ ነበር፤ ልክ ታሪኩ እንደኛ ነው። ኢምፖርት ታደርግ ነበር፤ ኤክስፖርት ማድረግ ስትጀምር ፍላጎት ነበር። አሁን ግን እንደምታውቁት ነው ታሪኩ፤ ሁለት ሦስት ዓመት ውስጥ ታያላችሁ የስንዴ ምርት ቨርቲካሊ /vertically/ አስተማማኝ በሆነ መንገድ ለእኛ ፍላጎት ብቻ ሳይሆን ለሸያጭም በቂ የሆነ ምርት እናመርታለን።

ሥራውን እየተላመድነው፣ ማሽን እየሰፋ ነው። በክላስተር ከምናርሰው መሬት የሚገኘው ምርት እያደገ መጥቷል። ይሄን ልንኮራበት ይገባል። ይሄ የሚያኮራ ምርት ግን ለምን ደሃው ዘንድ አልደረሰም ፤ ደሃው እየተቸገረ ነው የሚለው ትክክል ነው። ተረባርበን ኢንፍሌሽኑን/ ግሽበቱን/ እንዳለ ባናስቀረውም ያለውን ነገር ለመቀነስ መጣር አለብን። ሰሞኑን እንደምታዩት ጀምረናል፤ ይህም ይጠናከራል። ችግሩ ግን የሚታወቅና የሚገባን መሆኑን ለመግለፅ ነው።

ምርት ስለሌለ፣ ኤክስፖርት ስለሌለ የሚባለውና የሚነገረው ወሬ ስህተት ነው። ከፍተኛ ምርት በእያንዳንዱ አርሶ አደር ጓሮ ውስጥ አለ። ሰሞኑን ጊዜ ካላችሁ ከፍተኛ ምርት ተከማችቶ ስለመገኘቱ አርሲ፣ ባሌ፤ ጎጃም ብትሄዱ ታገኙታላችሁ። እኛ የምንፈጥረው አርቴፊሻል/ ሰው ሰራሽ/ ችግር አለ። ኬላ እየዘጋን፣ መንገድ ላይ ፍተሻ እያበዛን በጣም የምንፈጥራቸው ችግሮች አሉ። ዋጋ ይጨምራል በሚል አሰምሽን /እሳቤ/ ደግሞ ምርት የሚይዙ ሰዎች አሉ። ለምሳሌ ቡናን ብትወስዱ በዚህ ዓመት መጀመሪያ አካባቢ ዋጋው ጥሩ ነበር።

ዋጋ ሊጨምር ይችላል ብለው ቡና የያዙ አሉ፤ ከአንድ ወርና አንድ ወር ተኩል እንዲሁም ሁለት ወር በኋላ ግን ዓለም ላይ ዋጋው ቀነሰ። ያ ቡና የያዘው ሰው በሙሉ አሁን እንደምታዩት በረከሰው ዋጋ ለመሸጥ ተገደደ። አሁን ስንዴ ተይዟል። የዘንድሮው በጋ ስንዴ ከአንድ ሚሊዮን ሄክታር በላይ ምርት ሲሰበሰብ ከ40 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ይጨመራል። የት እናስቀምጠዋለን። ከስር ስር ሰው እንዳይቸገር አድርጎ መሸጥን ታሳቢ አድርገን ብንሠራ እናንተም ብታግዙ በማስተማር ጥሩ የሚሆን ይመስለኛል። ችግሩ አለ። ግን በተቻለ መጠን ተረባርበን ለመቀነስ ጥረት እናደርጋለን።

አጠቃላይ ኢንፍሌሽን ግን ቅድም ያነሳሁት እንደተጠበቀ ሆኖ የኢትዮጵያ የሁለት ሶስት ወራት ኢንፍሌሽን ገታ ያለ እንጂ እንደሚባለው አይደለም። የጤፍ ዋጋ ጨምሯል፤ የስንዴ ዋጋ ጨምሯል፣ የአንዳንድ የምግብ ሸቀጦች ዋጋ ጨምሯል። ሰሞኑን እሱን አምጥተን ስናበራክት የሚረጋጋ እንደሚሆን ተስፋ ይደረጋል። እና ኢንፍሌሽኑ ችግር ነው፤ ተረባርበን የምንፈታበትን መንገድ ማየት ይጠቅማል።

የመንግስት ገቢና ወጪን በሚመለከት እስከ አሁን ያስገባነው የተጣራ ታክስ 210 ቢሊዮን ብር ነው። ይሄ በአሃዝ ደረጃ ሲታይ በ28 በመቶ አድጓል። ነገር ግን ታክስ ጂዲፒ /አጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት/ ሬሾ በሚባለው አሁንም በጣም ዝቅተኛ ነው። በቁጥር እያደገ መጥቷል፤ ጂዲፒውም እያደገ ስለሆነ የምንሰበስበው በቂ ስላልሆነ ተጨማሪ ስራ ይጠበቅብናል።

የሰባት ወሩ ወጪያችን ግን 376 ቢሊዮን ብር ነው፤ ይህም ከገቢያችን ብዙ ይበልጣል። ከገቢያችን ብቻ ሳይሆን ወጪው ብቻውን 31 በመቶ አድጓል። ይሄን ያመጣው ሰው ሰራሹም የተፈጥሮ አደጋውም ነው። ቅድም ሲነሳ የነበረው ተጨማሪ ገንዘብ ለማፍሰስ ስለሚያስገድድ በብድርና ርዳታ ካልተሞላ በስተቀር በገቢ ካስገባነው ባሻገር ያለውን ፍላጎት እንደ መንግሥት ለማሟላት ያስቸግረናል። ወጪና ገቢያችን ተጨማሪ ሥራ የሚጠይቅና ገቢ ማሳደግ እንዳለብን ያመላክታል።

ኤክስፖርትን በሚመለከት ባለፈው ዓመት የተሻለ መመዝገቡ ይታወቃል። ዘንድሮ እስካሁን ያለው ኤክስፖርት ከምናስበው እቅድ በሪፖርቱ እንደተመላከተው ትንሽ ዝቅ ያለ ነው። ዝቅ ያለበት ዋናው ምክንያት በኮንትሮባንድ ምክንያት ወርቅና ጫት አምና ከሸጥነው በጣም በጣም ባነሰ ዝቅ ስላለ ነው። ለምሳሌ ወርቅን ብቻ ብንወስድ አሶሳ ላይ አምና ወደ ማዕከላዊ ገበያ 20 ኩንታል ወርቅ ቀርቦ ነበር፤ ዘንድሮ ግን ሦስት ኩንታል ነው የቀረበው። አብዛኛው ወደ ጎረቤት አገር ሄዷል ማለት ነው። ወርቅ እያመረትን ወደ ማዕከላዊ ገበያ ከማምጣት ይልቅ በአሻጥርና ከንትሮባንድ ወደ ጎረቤት ሀገራት በስፋት ይሄዳል።

ታንታለም ጉጂ ይመረታል፤ ኢትዮጵያ ኤክስፖርት ከምታደርገው በላይ የማያመርቱ ጎረቤት አገሮች ኤክስፖርት ያደርጋሉ። ይህንን ኮንትሮባንድ ለመከላከል፤ እያጋጠመ ያለውን ፈተና ለመከላከል አብዛኛው ኃይላችን አሁን ሃብት ባለባቸውና ሽፍታ በበዛባቸው አካባቢዎች እንዲሰፍር ተደርጓል። የአገር መከላከያ ሚኒስቴር፣ የፌዴራል ፖሊስ ቀዳሚ ተግባር ኮንትሮባንድን መዋጋት፣ በኮንትሮባንድ የሚመዘበረውን የኢትዮጵያን ሃብት መከላከል ይሆናል፤ በየአካባቢው ታጥቆ ለዘረፋ የተሰማራ ኃይልን ሕግ እንዲያስከብሩ በሚል ሥራ ተሰጥቷቸዋል። ቦታ ቦታቸውን እየያዙ በሚቀጥሉት ጥቂት ወራት ውስጥ ከፍተኛ ለውጥ እንጠብቃለን።

ሰርቪስን/ አገልግሎትን/ በሚመለከት ከጉድስ ኤክስፖርቱ የተሻለ ነው። አራት ነጥብ ሦስት ቢሊዮን ዶላር ገደማ ነው የሚደርሰው። ግን ኔት (የተጣራ) ኤክስፖርትን በሚመለከት ያለው እድገት ከአምናው 25በመቶ ነው። ኤክስፖርት ሲባል የማኑፋክቸሪንግ፣ የአግሪካልቸራል ጉድስ /የግብርና ሸቀጦች/፣ የሰርቪስ ፣ በተለያየ መንገድ ነው የውጭ ምንዛሪ አቅም የሚመጣው። ከዚህ ውስጥ የሰርቪሱ ኔቱ/ የተጣራው/ ትንሽ ሻል ያለ ይመስላል።

የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት (FDI) በሚመለከት፣ ባለፉት ስምንት ወራት ሁለት ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ዶላር ገደማ ገብቷል። ይህም ከአምናው በጣም ከፍ ያለ ነው። ከዚህ ውስጥ ከ90 በላይ ፕሮጀክቶች የተግባር ሥራ ውስጥ ገብተዋል። ከኤፍዲአይ አንፃርም ምንም እንኳ ችግር ያለ ቢሆንም፣ ተጨማሪ ሥራ የሚጠበቅብን ቢሆንም፣ ተስፋ ሰጪ ምልክቶች ግን አሉ።

ከገቢ ንግድ አንፃር ዘጠኝ ነጥብ አንድ ቢሊዮን ዶላር ነው ያስገባነው። ይህ ከአምናው ስድስት ነጥብ ሰባት በመቶ እድገት አለው። ካስገባናቸው ነገሮች ውስጥ አንደኛው ነዳጅ ነው 49 በመቶ የሚይዘው። ብዙዎቻችሁ ለዚህ ከተማ እንግዳ አይደላችሁም። ይህ ከተማ የዛሬ አምስትና 10 ዓመት የነበረውን የትራፊክ እንቅስቃሴ ታውቃላችሁ፤አሁን መንቀሳቀስ በማይቻልበት ደረጃ ከፍተኛ የሆነ የትራፊክ መጨናነቅ አለ።

በአሜሪካ ሀገር አንድ ጥሩ ባሕል አለ፤ሦስትና አራት መኪና የሚያሻግሩ መስመሮች /ሌኖች/ ካሉ፣ አንደኛውን ሌን/ መስመር /ከአንድ ሰው በላይ የያዘ ሰው ብቻ ይሄድበታል። ሾፌር ብቻ የያዘው መኪና ከሆነ አይፈቀድለትም። ልክ እንደ ቪአይፒ /VIP/ ሁለት ወይም ሦስት ሰው ከያዘ፣ ፈጣን መንገድ ይፈቀድለታል። በዚህ ምክንያት በዚያ ፈጣን ሌን /መስመር/ ለመጠቀም የማያውቁትን ሰው ቆመው እየጫኑ ይሄዳሉ።

ይህ በጣም ጥሩ ልምድ ነው። አባትም፣ ሚስትም፣ ልጅም ሁሉም መኪና ይዞ ከሚወጣ ትንሽ የቁጠባን እሳቤ ማሰብ ጥሩ ነው። አንዳንዶቻችን ገንዘብ ስላለን ነዳጅ ለመግዛት አንቸገርም፤ነገር ግን በድምሩ ኢትዮጵያን ስለሚጎዳ የቁጠባው እሳቤ በሁላችን ውስጥ ቢሆን ጥሩ ነው። አንድ ሰው ይዞት የሚሄደው መኪና አለ፤መኪና አጥተው የሚሰለፉ ሰዎች አሉ። ይህን በተቻለ መጠን እያስታረቁ መሄድ ያስፈልጋል፣ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ እየፈለገ ስለሆነ።

ሁለተኛ የካፒታል እቃዎች ናቸው። እነዚህ 27 በመቶ ይሸፍናሉ። ጥሬ እቃ ወደ 11 ፐርሰንት ገደማ ይሸፍናል። በነገራችን ላይ የፍጆታ እቃዎች ባለፈው እዚህ ምክር ቤት ቀርቤ ቢቆዩ ያልናቸው የፍጆታ እቃዎች 18 በመቶ ቅናሽ አላቸው። ምንም እንኳ ከዘጠኝ ቢሊዮን ዶላር በላይ ብናወጣም የፍጆታ እቃ ግን 18 በመቶ ቀንሷል። ይህ ማለት ለኢኮኖሚ እድገት በጣም ጠቃሚ ነው ማለት ነው። ዱሮ የምናወጣቸው አንዳንድ እምብዛም አስፈላጊ ያልሆኑ ቁሳቁሶች ቀንሰዋል። ይህ ከኢምፖርት አንፃር በጣም ጥሩ ነው። ይን እያጠኑና እያጠናከሩ መሄድ ያስፈልጋል። የፍጆታ እቃዎችን እየቀነሱና ጥሬ እቃ ግብዓትና አጠቃላይ የንግድ ሥርዓቱን የሚያሳልጡ ጉዳዮች ግን የግድ መግባት ያለባቸው ላይ ብቻ ብንወሰን ለኢኮኖሚያችን ጠቃሚ ይሆናል።

ብድርን በሚመለከት ለውጡ አካባቢ በተደጋጋሚ እንዳነሳሁት 59 በመቶ ነው የኢትዮጵያ ጂዲፒ /GDP/ እዳ የነበረው። ወደ 52 በመቶ ዝቅ ብሏል። በተለይ የውጭ ከ30 ነጥብ ስድስት በመቶ ወደ 24 ነጥብ አራት ፐርሰንት በመቶ ለማውረድ ተችሏል። አሁንም ሰፊ ሥራ የሚጠበቅብን እዳ ቅነሳ ላይ ነው። እዳ ቅነሳ ሰፊ ሥራ ያስፈልጋል ብለን ስንናገር የኢትዮጵያ እዳ በጣም ብዙ ስለሆነ አይደለም።

እኛ የምናመነጨው ዶላር እዳ ለመክፈል የምናደርገው ጥረት ሌሎች ልማቶችን ስለሚያደናቅፍብን ነው። ለምሳሌ፣ አሜሪካን ብንወስድ ባለፉት 100 ዓመታት 20 ትሪሊዮን ዶላር እዳ ነበረባት። ባለፉት ሰባትና ስምንት ዓመታት ግን ከ50 ፐርሰንት በላይ ጨምራ ዛሬ 31 ትሪሊዮን ዶላር እዳ አለባት። የእኛ 30 ቢሊዮን አይሞላም፤ እንኳን ትሪሊየን። ልዩነቱ ያለው እነሱ መክፈል ስለሚችሉ፣

# ወቅታዊ

የሚገበያዩበት ዶላር ስለሆነ የውጭ ምንዛሪ አይቸገሩም። እኛ ግን ለመክፈል የግድ ዶላር ማመንጨት አለብን።

እዳን በከፍተኛ ደረጃ ቀንሰን አብዛኛው የእኛ የእዳ ክፍያ ወደ ኮንሴሽናል ካልተቀየረ በስተቀር በኮሜርሻል ሎን/ ብድር/ ሬት የምናመጣውን የውጭ ምንዛሪ በሙሉ እዚያ ላይ ካዋልን ለልማት እንቸገራለን። የብዙ ሀገራት እዳን መዘርዘር ይቻላል፣ በእኛ በኩል ግን ጥሩ ጅማሮዎች አሉ፤እነሱን አጠናክረን በመቀጠል በሚቀጥሉት ስድስትና ሰባት ወራት ተስፋ የምናደርጋቸው መሻሻሎች አሉ፤በዚያ እየቀነስን እንደምንሄድ ተስፋ ይደረጋል።

በሴክተር ደረጃ ሲታይ ግብርና በኩታገጠም ማሳ ስድስት ሚሊዮን ሄክታር ደርሰናል። ይሄ በጣም ተስፋ ሰጪ ውጤት ነው፤ ግን ብዙ ይቀራል። የዚህን እጥፍ ማደግ ብንችል በምርታማነት ላይም ከፍተኛ ለውጥ ያመጣል። የበጋ ስንዴ አንድ ሚሊዮን ደርሰናል፤ ማሽነሪዎችና ፓምፖች አድገዋል። አጠቃላይ ምርት አድጓል። ኢትዮጵያ ውስጥ የቡና ምርት በስፋት አድጓል። ስንዴ አድጓል። የሩዝ ምርት አድጓል። ሻይና አንዳንድ አካባቢዎች ላይ ተጨማሪ ሥራ ያስፈልጋል። ፍሩት / ፍራፍሬ/ በጣም ተስፋ የሚሰጡ ጅማሮዎች አሉ።

ግብርና አጠቃላይ ጥሩ ነገር ያለ ቢሆንም ዋጋው ላይ ግን አሁንም ችግር አለ። ዋጋው ላይ ችግር የሆነው አንደኛ የነዳጅ ዋጋ እየጨመረ ስለሄደ፣ማሽነሪ መጠቀሙ፣ ትራንስፖርት መኖሩ በአርሶ አደሩ ወጭ ላይ ተጨማሪ ሀብት ዲማንድ ያደርጋል/ ፍላጎት አምጥቷል። ሁለተኛ የማዳበሪያና የምርጥ ዘር ዋጋ በአጠቃላይ የግብዓት ዋጋ እየጨመረ ስለመጣ ከዚያም በላይ የሌበር ፎርስም / የጉልበት/ ወጭ እያደገ ስለመጣ በሚፈለገው ደረጃ ገበያው የሚያመጣጥን አልሆነም።

ቅድም እንዳነሳሁት ሆርዲንግን /ማቆየትን/ጨምሮ ማለት ነው፤ ይሄ ስፔኩሌሽን የሚያመጣውን ሆርዲንግ አስተካክለን ሎጂስቲክስ ላይ የሚያስፈልግ ሥራ ከሠራን ምርት እያደገ ሲሄድ በተቻለ መጠን ቢያንስ በልተን ለማደርና እንደሀገር ሰርቫይቭ ለማድረግ የሚያስችል ነገር ይፈጠራል የሚል ሀሳብ ነው ያለው። ማኑፋክቸሪንግ ላይ 55 ፐርሰንት መድረስ ነበር እቅዳችን፤ 52 ደርሰናል። ኢትዮጵያ ታምርት የሚለው እንቅስቃሴ በጣም ተስፋ የሚሰጥ ውጤት እያመጣ ነው።

በተለይ የተከበረው ምክርቤት ጊዜ ሲኖረው እንዲያይ የምፈልገው በኮምቦልቻ፣ በደብረብርሃን፣ በዱከምና አዲስ አበባ መካከል እስከ አዳማ ባለው አካባቢ፣ቁጥራቸው አነስተኛም ቢሆን አንዳንድ ፕራይቬት ኢንቨስተርስ / የግል ባለሀብቶች/ እጅግ ተስፋ የሚሰጥ አስደማሚ የኢንዱስትሪ ሥራ እየሠሩ ነው። አንዳንዶቹን የማየት እድል አግኝቻለሁ፤ በሳይዝ ስፋት ሳይሆን በጥራት ደረጃ እኛ ኢንዱስትሪ ፓርክ ካልናቸው የሚሻሉ። ይሄን ጅማሮ ማስፋት ያስፈልጋል።

ግብርና እንደምታውቁት አዳጊና ሟች ነው። በቀጣይነት የሚያድግ አይደለም። አድጎ አድጎ ይሞታል ይቆማል። ኢንዱስትሪ ለረጅም ጊዜ የሚያድግ ስለሆነ ፕራይቬት ሴክተሩ/የግሉ ዘርፍ/ ታግዞ በዚያ ሴክተር ኢንቨስት እንዲያደርግ ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል። ጅማሮዎቹ የሚደነቁ ናቸው። ጥቂትም ቢሆኑ በከፍተኛ ደረጃ በጥራት የሚሠሩ ባለሀብቶች መታየት ጀምረዋል፤ ይሄንን ማጠናከር ያስፈልጋል።

ሰርቪስን በሚመለከት የኢትዮጵያ አየር መንገድ፣ ቴሌኮሙኒኬሽን፣ ሁለቱም በጣም በጣም ተስፋ ሰጪ ውጤት አምጥተዋል። በእቅዳቸውና ከእቅዳቸውም በላይ አሳክተዋል። ቱሪዝምን በሚመለከት ቅድም እንደተነሳው፤ሀመር አካባቢ የተደረገልኝን ግብዣ መቼ እንደሆነ ባላውቅም መጥቼ ለማየት በጣም እጓጓለሁ። ደስ ይለኛል። መታየት የሚገባው ሕዝብ ነው። ግን ቱሪዝምን በሚመለከት በአጠቃላይ እንደሀገር እየተከተልን ያለነው መንገድ፣የተከበረው ምክር ቤት በደንብ እንዲገነዘብና እንዲደግፍ ያስፈልጋል።

እንደምታስታውሱት ኢትዮጵያ ውስጥ ታሪክም፣ መልክዓ ምድርም፣ ባሕልም በከፍተኛ ደረጃ ሊታይም ሊሸጥም የሚችል ነገር አለ። ይሄን ለማሳየት ግን ምቹ ነገር የለም። ለምሳሌ ታሪክ አለ፤ ነገር ግን ማረፊያ ቦታ የለም። ታሪክ አለ፤ ትራንስፖርት ምቹ አይደለም። ብለን በገበታ ለሸገር ምን ሥራ አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ እንደተሠራ ታውቃላችሁ።

አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ አዲስ አበባን እንደስሟ እናደርጋታለን ብለን ስንጀምር ይሄ ሁሉ ቻሌንጂንግ / ፈታኝ/ ነገር ይገጥመናል ብለን አላሰብንም። እየገነባንና እየሠራን ስንሄድ ግን ገና ሊፈርስ ሊሠራ የሚገባው ስንት ጉድ እንዳለ እያየን ነው የሄድነው።



ከአዲስ አበባ አልፈን ኢትዮጵያን ለማዳረስ ባደረግነው ጥረት ገበታ ለሀገር ላይ እየሠራን ነው፤ ለምሳሌ፣ ጎርጎራ ፕሮጀክት አሁን በመጠናቀቅ ላይ ነው ያለው፤ ምናልባት ሶስት ወር ወይንም አራት ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ሰርቪስ መሥጠት ይጀምራል። ጎርጎራ ፕሮጀክት ሲባል አሁን ዝም ብለን እንደምንናገረው ሳይሆን በአፍሪካ ምናልባት አንድ ሦስት ቤስት ሪዞርቶች ካሉ አንዱ ጎርጎራ ነው።

ምርጥ ሥራ ነው የተሠራው። ምንም አያጠራጥርም። ለታሪክና ለትውልድ የሚሆን ሥራ ተሰርቷል። ወንጪ ብትሄዱ፣ ሳይዙ የሚለያይ ቢሆንም ሃላላ ኬላ፣ ኮይሻ ብትሄዱ የሠራናቸው ሥራዎች በጥራታቸውም ሆነ በጊዜያቸው በጣም በጣም ተስፋ የሚሰጡ ናቸው። ግን ውስን ናቸው አሁንም፣፤ሶስትና አራት ናቸው። በመንግሥት በጀት አይቻልም ታውቃላችሁ።

በቅርቡ የዛሬ ወር ገደማ ገበታ ለትውልድ አልን፤ ገበታ ለሸገር፣ ገበታ ለሀገር ብለን ገበታ ለትውልድ የሚል አዲስ ፕሮጀክት ጀምረናል። በዚህ እስከ ሰባት ቢሊዮን ብር እናገኛለን ብለን ነው የዛሬ ወር እቅድ ያወጣነው። ይገርማችኋል! የኢትዮጵያ ሕዝብ ደግ ነው። አሁን አንድ ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ከአምስት ቢሊዮን አልፈናል። እስካሁን በሚዲያ አልተናገርንም፤ አዋጅ አልታወጀም። ምክንያቱም ይሄ ፕሌጅ ተደርጎ የማይሰጥ ሳይሆን ወደኛ አካውንት መግባቱ እስኪረጋገጥ ለሕዝብ አንናገርም በሚል ማለት ነው።

በዚህ ገንዘብ ስድስት የገበታ ለትውልድና ሁለት በግል የሚሠሩ ፤ በአጠቃላይ ስምንት ፕሮጀክቶች ለመሥራት ታቅደዋል። በሰሜን ትግራይ ገራልታ ላይ የሚሠራ መሰል ሪዞርት አለ። አሁን የጀመርነውን የሰላም ጉዳይንም የሚያጠናክር ማለት ነው። በወሎ ሐይቅ ዳርቻ አካበቢ የሚሠራ ሁለተኛ ሪዞርት አለ። አንድ ሰው ከዚህ እየነዳ ሐይቅን አይቶ ከዚያ ወደሰሜን ሄዶ መስመሩን ቀስ ቀስ እያልን እየሞላን ለመሄድ በቅርብ ርቀት የታሰበ ነው፤ በዚያ ደረጃ ያለውን ቱሪስት ለመሳብ ያስችላል።

ወደ ኦሮሚያ ሲኬድ ጅማ ላይ ነው የታሰበው። ጅማ በጣም ከፍተኛ የሆነ የልማት ጥያቄዎች አሉ። ቅድምም ከጌራ በተነሳው አይነት መንገድ በገበታ ለሀገር ብዙ የሚታይ ታሪክ ስላለ። ሦስተኛው ጅማ ላይ ይሆናል።

አራተኛው በአፋር ክልል ፓል በሚባል አካባቢ ምናልባት ከመረጥናቸው ቦታዎች ሁሉ በጣም በጣም ምርጡ በአፋር ክልል ያገኘነው ቦታ ነው። እዚያ ቦታ የሚሠራ ይሆናል። አምስተኛው የደቡብ ፈርጥ የሆነችው እና በጣም በጣም ብዙ ሊሠራበት የሚገባው ከዚህ ቀደም ያነሳኋት ከተማ አርባምንጭ ላይ የሚሠራ ይሆናል። ስድስተኛው በሶማሌ ክልል ሁለት ምርጫ ቀርቧል። ከሁለቱ በአንድ ቦታ የሚሠራ ይሆናል። ይሄ በገበታ ለትውልድ ምናልባት ፆም ረመዳንና ፋሲካ ሲፈታ የሚታወጅ (የሚሠራ )ነገር ይሆናል።

በግል ደግሞ በቤኒሻንጉል ክልል ሕዳሴ ግድብ አካባቢ አንድና በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሚዛን አካባቢ ሌላ አንድ ዲዛይን አልቋል። ግለሰብ ለምነን በቀጥታ በገበታ ለትውልድ ውስጥ የሚገባ። ስምንት ሲሠራ አሁን ከምንሠራቸው አራት አምስት ውስጥ ከሚጠጉት ጋር ተያይዞ አስራ ምናምን ይሆናል ማለት ነው። ይሄ በጀት አይደለም። ሰው አዋጥቶ ተለምኖ የሚሠራ ሥራ ነው። ሲሠራ ግን የመዋጮ ሥራ አይደለም። ለታሪክ የሚሸጋገር ሥራ ነው።

ከእናንተ መካከል ጎርጎራን ማየት ያልቻለ ሰው፣ ኮይሻን ማየት ያልቻለ ሰው ካለ ያልታደለ ብቻ ነው። ማየት አለባችሁ፤ በባስም ቢሆን ሄዳችሁ። ምክንያቱም ጎርጎራ ወደፊት በጣም ብዙ ሰው እየመጣ ስለሚያይ ዋጋ እየጨመረ ስለሚሄድ እንዳሁኑ አይረክስም። ቶሎ ቶሎ አሁን ካላያችሁ በኋላ ሸሚያው ከባድ ነው። በዚህ መንገድ ቱሪዝምን እያስፋፋን እንሄዳለን። አሁን ያለው ችግር እኔም ጋ ይሠራ፤ እኔም ጋ ይሠራ የሚል በጣም ጥሩ የሆነ ቀና እሳቤ ቢሆንም ሁሉም ጋ ከመሄድ በፊት ቃል የገባነውን መጨረስ ፤የምንጀምረውን መጨረስ በጥራት መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። ልክ ፍሬንድሽፕ እንደሠራነው፤ ልክ እንጦጦ እንደሠራነው፤ ልክ ፓርኪንጎች እንደሠራነው ጽድት ያለ እና ለልጆች የሚሸጋገር መሆን አለበት የምንሠራው ሥራ። እንደዚያ ካልሆነ ዘላቂ ውጤት አያመጣምና። ቱሪዝም አካባቢ በጥቅሉ በጣም ተስፋ ሰጪ ጅማሮች አሉ። እነዚህን ለማጠናከር የተከበረው ምክር ቤት ከጎናችን እንዲሆን እንዲያግዝና እንዲያስፋፋ አደራ እላለሁ።

ፋይናንሻል ሴክተር ልክ እንደአምናው ዘንድሮ በጣም ጥሩ ውጤት የተገኘበት ነው። ካበደሩት ውስጥ ወደ 172 ቢሊዮን ገድማ ብድር ሰብስበዋል። 311 ቢሊዮን ብር አበድረዋል። ዘንድሮ የሰጡት ብድር አምና ከሰጡት ብድር ከመቶ ፐርሰንት በላይ ያደገ ነው። ባንኮች ማበደራቸው ብቻ ሳይሆን 93 በመቶ ያበደሩት ለግሉ ሴክተር ነው። ይሄ የጀመርነውን ልማት ለማፋጠን በጣም ተስፋ ይሰጣል። ስለግብርና ሴክተር ባለፈው አንስቼ ነበር ትዝ ይላችኋል፣ አሁን ለግብርና 92 ቢሊዮን ብር የተሰጠ ሲሆን፤ ይህ ከአምናው በ29 በመቶ አድጓል።

በጣም ተስፋ ሰጪ ነው ማደግ አለበት፣ የተሠራው ሥራ በጣም ጥሩ ነው። አነስተኛና ጥቃቅን 30 ቢሊዮን ከአምናው 36 በመቶ ጭማሪ አለው። ምን ማለት ነው ይሄ በርከት ያሉ ሰዎች የሥራ እድል እንዲያገኙ ዕድል ይሰጣል ማለት ነው። ፋይናንሻል ሴክተር አጠቃላይ ጤናማ ነው፤ እድገቱም ጥሩ ነው የሚል ድምዳሜ የሚያሰጥ ቢሆንም ግን መጠንቀቅ ያስፈልጋል።

ፋይናንሻል ሴክተሮች አሉ ሲባሉ ሳታወቅ እየወደቁ ስለሆነ በ2020 ከፍተኛ ትርፍ ያገኘ ባንክ በ2023 ስለወደቀ የእኛም ባንኮች ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርባቸዋል። ኢኮኖሚ በጣም በሚዋዥቅበት ሰዓት ፋይናንሻል ሴክተሩ ከተመታ አደጋ ስለሆነ ናሽናል ባንክና ገንዘብ ሚኒስትር በቅርብ ቁጥጥር ማድረግ አለባቸው። ሃብቶቻቸው ትክክለኛ ቦታ እየዋለ መሆኑን ማወቅ ያስፈልጋል። ዕዳው የእኛው ስለሆነ። አሁን ያለው ተስፋ ሰጪ ነው፤ ነገር ግን ጥንቃቄ ያስፈልጋል።

መሠረተ ልማትን በሚመለከት፣ መንገድን በሚመለከት በርካታ ጥያቄ ተነስቷል። ጥያቄው ሦስት መልክ አለው፣ አንደኛው በጣም ለመልማት ካለ ፍላጎት የሚነሳ ነው፣ ሁለተኛው ከፌዴራል መንግሥት ስልጣን ውጪ የሚሄድ ነው፣ ሦስተኛው ደግሞ የሚጓተቱና ተጀምረው መልስም ያልሆኑ ለጥያቄም የማይመቹ ፕሮጀክቶች የሚመራበትን መንገድ ታሳቢ ያላደረገ ነው። የተከበረው ምክር ቤት ባለፈው ስመጣ 22ሺ ኪሎ ሜትር ገደማ አስፓልት ኮንክሪት እየተገነባ ነው ብያችሁ ነበር። አሁን ዛሬ ባለኝ ዳታ ከዚያ ይበልጣል። ቁጥሩን አልናገርም ስለምታውቁት፣ ከ22ሺ ኪሎ ሜትር በላይ አስፓልት ኮንክሪት ኢትዮጵያ ውስጥ ይሠራል።

ዛሬ በእጃችን ያሉ ፕሮጀክቶችን ብቻ ለማስጨረስ አንድ ትሪሊየን ዶላር ያስፈልገናል። 320 ፕሮጀክቶች በመንገድ አሉ፣ ዛሬ(320 ፕሮጀክቶች ኢትዮጵያ ውስጥ)። አንድ ትሪሊየን ብር ይጠይቃሉ፤ እኛ እነዚህን ፕሮጀክቶች ስንጨርስ እስካሁን ኢትዮጵያ ከተፈጠረች ከሠራችው መንገድ በአስፓልት የዛሬ አምስት ዓመት ውስጥ የጀመርናቸው ይበልጣሉ ስንጨርሳቸው። ሰፊ ሥራ ነው፤ በእርግጥ ያ ሥራ ነው ዲማንድ የፈጠረው ፤ ተጨማሪ ሥራ እያመጣ ያለው ያ ሥራ ነው። እዛ ሥራ ውስጥ ውስንነት ቢኖርም። በቅርቡ አንድ ሃገር ሄጄ ነበረ እና ይሄ ሃገር ከሞላ ጎደል ከኛ ጋር ይቀራረባል። ባለፉት አራት ዓመታት አንድ ኪሎ ሜትር አስፓልት መንገድ አልጠገኑም። አንድ ኪሎ ሜትር ያልጠገነም መንግሥት አለ፣ 20ሺ ኪሎ ሜትር የሠራ መንግሥት አለ፤ ሁለቱም በጋራ ይወቀሳሉ።

መንገድ ላይ ሰፊ ሥራ እየሠራን መሆኑን በሄዳችሁበት በእያንዳንዱ ዞን መንገድ የማይቆፈርበት አንድ ዞን መናገር አትችሉም። አንዳንዱ በጥሩ የሚሄድ አንዳንዱ የሚያዘግም ሊሆን ይችላል። እንደየአካባቢው ሁኔታ፤ ግን ሰፊ ሥራ አለ። ይህንን ስራ አድሚት ካደረግን በኋላ በውስጡ ያሉ እንከኖች በበጀት፣ በዲዛይን፣ በካሣ እንዲሁም እንዴት እያረምን እናፋጥናቸው ብለን መነጋገር ደግሞ አስፈላጊ ይሆናል።

ለምሳሌ፣ ባህርዳር ላይ የጀመርነው ድልድይ ኢትዮጵያ ውስጥ የለም። ሠርተንም አናውቅም እንዲህ ዓይነት ድልድይ ኢትዮጵያ ውስጥ በዋጋውም በዲዛይኑም፤ እያለቀ ነው ያለው። በርካታ መንገዶች በእጅጉ ሊያግዙ የሚችሉ ፕሮጀክቶች አጀማመራቸውና ሂደታቸው ጥሩ ሊባል የሚችል ነው። እዚህ ውስጥ ግን ውስንነቶች አሉ፤ ለምሳሌ ሮቤ ጋሰራ ከለውጥ በፊት የነበረ ፕሮጀክት ነው፣ ኮንትራክተሩ ከሰረ ሥራውን ጥሎት ሄደ፤ ሁለት ሎት ነው አንደኛውን ሎት ለማሠራት ሙከራ ተደርጓል፣ አንደኛው ሎት ግን ችግር አለበት። መፍታት አለብን ጥያቄ የለውም፣ ግን መቼ ተጀመረ እንዴት ተቋረጠ የሚለውን ማወቅ አስፈላጊ ነው።

ይሄ ለውጥ ከመምጣቱ በፊት የተጀመረ፤ ለውጡ ከመምጣቱ በኋላ ኮንትራክተሩ ሙሉ ለሙሉ ሥራውን ጥሎት የሄደ ጉዳይ መሆኑ መታወቅ አለበት። ያም ሆኖ ለማረም ጥረት ይደረጋል፣ አርባ ምንጭ ሳውላ ከዛ የመጣችሁ እንደምታውቁት በጣም አደገኛ መሬት ነው፣ የሚንሸራተት መሬት ነው ቦታው፣ አስፋልት ከተሠራ በኋላ መሬት ተንሸራቶ አስፋልቶች ይወስዳል ሦስት አደገኛ ድልድዮች ተጠግነዋል ሌላውን መንገድ ክረምት ሳይመጣ ለመጠገን እዚያ አካባቢ ያሉ ዲስክሪክቶች ተንቀሳቅሰዋል። ሥራው በጣም አስፈላጊ ነው እንደተባለው የችግሩ መንስኤ ግን ይታወቃል አካባቢው ላይ ያላችሁ ሰዎች እንደምታውቁት በመሬት መንሸራተት ያጋጠመ ችግር ነው፣ ያን በጥገና ለመፍታት ጥረት ይደረጋል።

የወልድያ ጋሸና ከግጭት በፊት ለአማራ ክልል የመንገድ ስራ ተቋራጭ የተሰጠ ፕሮጀክት ነበረ፣ ግጭቱ ሲያጋጥም አደጋ ደርሶበታል ሥራው አጠቃላይ በዚያ ምክንያት ተጓቷል፣ አሁን ኮምቦልቻና የጎንደር ዲስትሪክት ለጥገና ተሰማርተዋል፣ እንዴት አድርገን ወደ ነበረው ቁመና ፕሮጀክቱን እንደምንመልሰው ሥራ ይፈልጋል። ያው የምታውቁት ጉዳይ ስለሆነ ብዬ ነው።

ወቅታዊና ልዩ ልዩ

# ወቅታዊ

የመጣውን እዳ እና ገፈት እንዳለ ወደ ጎን አድርጎ መሄድ አይቻልም፡፡ አንዳንዱን እያስቀመጡ እየጠገኑ መሄድ ነው የሚያስፈልገው፡፡

የአማራ ክልል የመንግስት ስራ ተቋራጭ ጅማሮው ቆንጆ ነበር፣ በነበረው ግጭት ግን ብዙ ሀብት ወድሟል፡፡ እና እሱን እንዴት አድርገን ወደ ነበረው እንደምንመልስ ሥራ ይፈልጋል፡፡ ምስራቅ ሐራርጌ የተባለው ነገር ትክክል ነው፡፡ ግን ያ ስፔስፊክ መንገድ መንግሥት የሚሰጥ ነው የሚለውን ማየት ጠቃሚ ነው፡፡እያንዳንዱ ወረዳ የሚያገናኘውን መንገድ ኪሎ ሜትር ዘጠኝም ይሁን አሥር የፌደራል መንግሥት ሊመልሰው አይችልም፣ የፌደራል መንግሥት ግዴታ ዋና ዋና መንገዶች ናቸው፡፡ እና የክልል መንግሥታት አንዳንዱን ነገር እንዲያግዙ ማድረግ ጠቃሚ ይመስለኛል፡፡

ከዚሁ ጋር ተያይዞ የተነሱ ከመንገድ ጋር የተያያዙ ጥያቄዎች መንገድን ሥራ የሚያጓትቱ በርካታ ምክንያቶች አሉ፡፡ አንደኛው የቅድመ ግንባታ ሥራ፣ እናንተ ትሄዳላችሁ ሕዝብ ይጠይቃል፣ እናንተ ትጠይቃላችሁ ወዲያው እሺ ይባላል፣ ፕሮፐር ዲዛይን ሳይሠራ ሥራ ይጀመራል በአንድ ቢሊዮን ብር ሥራ ይጀመራል እየተገባ ሲሄድ ሶስት አምስት አስር ይባላል፡፡ የቅድመ ግንባታ ሥራ የዲዛይን ለውጥ የጨረታ ሂደት የማቴሪያል ዋጋ በየጊዜው መጨመር ሁሉ መንገዶች ላይ እንቅፋት ይፈጥራል፡፡ ስንጀምር የነበረውና አሁን ያለው አንድ አይደለም፡፡ ከሁሉ በላይ ግን የተከበረው ምክር ቤትና መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲያደምጠኝና እንዲደግፈን የምንፈልገው ነገር የካሣ ጉዳይ ነው፡፡ ካሣ የአደገኛ ግብር የማይከፈልበት ሕገወጥ ንግድ ሆኗል፡፡ አደገኛ አንድ ከተማ ውስጥ ውሃ የለንም ውሃ አምጡልን ይባላል ለውሃ ተብሎ ፌደራል መንግሥት በጀት ሲይዝ ለከተማው እርዳታ የሚሠራ ፕሮጀክት መሆኑ ቀርቶ ልክ እንደ ኢንቨስትመንት ይታሰብና የፕሮጀክቱን ዋጋ ያክል የካሣ ጥያቄ ይቀርባል፡፡

ይሄ ትክክል አይደለም፡፡ ሕግ እናወጣለን ከእንግዲህ በኋላ የፌደራል መንግሥት ካሣ የሚከፍልባቸው ለምሳሌ የባቡር መንገድ አልፎ ባቡሩ ገቢ የሚያገኝበት ከሆነ የቴሌኮሙኒኬሽን አልፎ ቴሌኮሙኒኬሽኑ ገቢ የሚያገኝበት ከሆነ፣ ለሰፈር የምንሠራውን ውሃ ለሰፈር የምንሠራቸውን ማንኛውም ጉዳዮች ክልሎች ከካሣ ውጪ ማዘጋጀት አለባቸው፡፡ ሌላ ሪሶርስ የለም አሁን ዝም ብሎ ወረዳ የተባለው፣ ወረዳዎች ገና መንገድ ይሠራል ሲባል ጌሾ እያስተከሉ ተመን እያስፋፉ ልማት እንዳይሠራ እያደረጉ ነው፡፡

ይሄን ደግሞ ታውቃላችሁ፣ ዘንድሮ እኮ ለመንገድ 20 ቢሊዮን ብር ጠይቋል ካሣ ብቻ፣ ካሣ እንክፈል ወይስ መንገድ እንሥራ?፤ በአንድ በኩል ኢንፌሌሽን ተብሎ በሌላ በኩል ስንትና ስንት ጣጣ ያለበት ሀገር ልማት ስንፈልግ ተረባርበን ማገዝ ሲገባን ዩኒቨርሲቲ ይባልና የሚጠየቀው ዩኒቨርሲቲ እንኳን እኛ አንሠራም በጥቅሉ ግን የሚጠየቀው ካሣ ሃብት በጣም ከፍተኛ ነው፡፡ በዚህ ልምምድ ልማት ልናመጣ አንችልም፡፡

ካሣ መጠየቅ ያለበት አቶ ታገሰ ፎቅ ሠርቶ ሆቴል ሠርቶ ለራሱ ትርፍ የሚያተርፍ ከሆነ እዚያ ቦታ ያለን ሰው ወይም ሼር ማስገባት አለበት ሰውየውን በሚጠቅም መንገድ ኢንቨስትመንት መካሄድ አለበት ትክክል ነው ይሄ፡፡ ለሰፈሩ ለመንደሩ ውሃ እየቀረበ ለውሃ ካሣ ተብሎ ፕሮጀክት ማዘግየት ግን ትክክል አይደለም፡፡ ያ ውሃ የሚጠቅመው ለእነርሱ ነው ንግድ አይደለም፡፡ የጋራ ሀብት ነው መሬት የመንግሥትና የሣዝብ የተባለው ለዚህ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ልምምድ ግን እንደዛ አይመስልም፡፡ እና ሣሳን በሚመለከት ብታግዙን ጥሩ ነው፡፡

በእርግጥ ገንዘቡ በሙሉ ለአርሶ አደሮች እየገባ ነው ወይ እርግጠኛ አይደለሁም፡፡ ግን ከፍተኛ አሻጥር ስላለ እንደ ወርቅ ኮንትሮባንድ የተከበረው ምክር ቤት ቢያግዘን ጥሩ ነው፡፡ ከዚህ የተነሳ ልማት እያደናቀፈ መሆኑን ከግምት ብታስገቡ ይሻላልና እና መንገድ በሚመለከት በጣም ሰፊ ሥራ እየሠራ ያለ መንግሥት እኔ በሰብ ሰሐራን ሀገራት የኢትዮጵያን ያክል በመንገድ ላይ ልማት ገንዘብ የሚያወጣ መንግሥት ያለ መሆኑን እርግጠኛ አይደለሁም፡፡ አይመስለኝም፡፡ ሰፊ ሥራ እየሠራን ነው ያለነው፡፡

ችግሮች አሉት እሱን እያረምን ብንሄድ መልካም ይሆናል ብዬ አስባለሁ፡፡ ኢነርጂ በሚመለከት የኤሌክትሪክ ኃይልና የኤሌክትሪክ አገልግሎት የሚባል ሁለት ተቋም አለ፡፡ በመጀመሪያ ሁለቱም ተቋም የበጀት ተቋም ስላልሆኑ በጀት አነሳቸው ወይም በጀት ይመደብላቸው የሚለው በበጀት አይተዳደሩም፡፡ ሁለቱም የልማት ድርጅቶች ናቸው፡፡

**ይሄን አስበን እንሂድ፤ ሥልጣን በምርጫ እናድርግ፡፡ውይይት እንመን፤ በሀሳብ እንመን፤ ያለውን ጥላቻና ውጥረት እንቀንስ፤ በዚህ አግባብ የተጠናከረች ኢትዮጵያን ለመፍጠር አበክረን እንሥራ**

የኤሌክትሪክ ኃይል በሚሠራው ሥራ ኢነርጂ ለማመንጨት በአማካኝ 85 በመቶ የውጭ ምንዛሪ ያስፈልገዋል፡፡ አሁን ዘንድሮ 66 ቢሊዮን ብር ነው በጀቱ፡፡ በአፍሪካ ካሉ አምስት ትላልቅ ግድቦች ሁለቱን የምትሠራ ናት ኢትዮጵያ፡፡ ህዳሴና ኮይሻ፡፡ በኃይል ማመንጨት የጀመርነውን ሥራ እንፈጽም እንጂ በጣም ትልቅ ነው፡፡

ሁለቱ እኮ ሲያልቁ አሁን ያለውን ሁለት እጥፍ ይጨምራል፡፡ እና እንደቀላል ኢንቨስትመንት የሚታይ አይደለም፡፡ ይሄ ሁሉ ውጊያ ይሄ ሁሉ ጣጣ እያለ አንድ ቀን እንዳይቋረጥ ተደርጎ የሚሰራው ኢነርጂ ያስፈልጋል ተብሎ ስለሚታመን እና ጥቅሙ የሚታወቅ ስለሆነ ነው፡፡ ልክ እንደመንገድ ሁሉ ሀይል ለማመንጨት የኢትዮጵያ መንግስት የሚያደርገው ኢንቨስትመንት በብዙ ሀገራት የሚታይ አይደለም፡፡ በጣም በጣም ግዙፍ ነው፡፡ ህዳሴ ብቻውን በቂ ነው እኮ ኮይሻ አያስፈልግም፡፡ ግን እዛ አልቆመም እኮ ሶላሮች አሉ፡፡ ዘወትር የሚሰሩ ስራዎች በጣም በጣም ብዙ ናቸው በየክልሉ፡፡ ካለን ዲማንድ አንጻር እሩቅ ቢሆንም፡፡

ጌራ ላይ የተነሳው የኃይል ጉዳይ ያው ጌራ በጣም ሀብታም፣ በጣም ለም አካባቢ ነው፡፡ ግን ጌራ መንገድም መብራትም እንደዚህ አይነት ነገሮች ላይ ብዙም አይታወቅም፡፡ ራቅ ያለ ቦታ ስለሆነ፡፡ አሁን ቢያንስ መንገድ እየተሠራለት ነው፡፡ በጣም ብዙ ቡናና ማር ያለው ሀብታም ሀገር ነው፡፡ ያን ሀብት እንዲያመጣ ኢነርጂም ደረጃ በደረጃ እየተሻሻለ እንደሚሄድ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡

እስካሁን በነበረው ግን እንደምታውቁት ጥያቄውንም እንዳነሱት ትንሽ እራቅ ያለ ቦታ ስለሆነ ከጅማ መቶ ኪ.ሜ ገደማ የጅማ ጫፍ ላይ ያለ አካባቢ ነው፡፡ በዚህ ምክንያት መሠረተ ልማት በቂ አይደለም፡፡ ግን በሀገር ደረጃ ሲታይ በጣም ተስፋ ሰጪ የኃይል ማመንጨት ተግባር እየተካሄደ ነው ተብሎ ቢወሰድ ጥሩ ይሆናል፡፡

እንግዲህ የፓርላማ አባላት ሁለት ገጽታ አላችሁ፡፡ አንደኛው ገጽታ እንደ ሀገር ነው የምናየው፡፡ ሌላው ደግሞ የሰፈራችን ይሆናል፡፡ ሁሉ ጉዳይ የሰፈር ከሆነ አስቸጋሪ ነው የሚሆነው፡፡ እንደ ሀገር ያለውን አይተን ከዚያ ውስጥ ሰፈር ጋር ባላንስ ካላደረግን በስተቀረ የየቀበሌያችንን ካነሳን ትንሽ ያስቸግራል፡፡ ደግሞ እንደምታውቁት ምክር ቤት እዛም ስላለ ይሄኛው ምክር ቤት በሀገር ደረጃ ስላሉ ጉዳዮች ቢነጋገር የበለጠ ጥሩ ይሆናል፡፡

ሰርቪስን በሚመለከት የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት በሚመለከት በሪፎርሙ የጀመራቸው ውጤቶች አሉ፡፡ ለምሳሌ ፈረቃ ቀርቷል፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ፈረቃ ነበር ቀንሷል፡፡ ጥሩ ነገር ነው፡፡ ማሰራጫዎች ሊያስፋፉ ሞክረዋል፡፡ ጥሩ ነገር ነው ነገር ግን አሁንም ብዙ ሪፎርም ያስፈልጋል፡፡ የመብራት መጥፋት ሰፊ ነው፡፡ ሰርቪስ ላይ እርካታ የለም፡፡ የሪፎርም ሥራዎች ያስፈልጋሉ እዛም ቢሆን ግን ሪፖርት እንደቀረበላችሁ አውቃለሁ፡፡

እዛ ቢሆን ግን በተሠራው ሪፎርም በጣም በርካታ ውጤቶች እየመጡ ነው፡፡ የነበረው ማሰራጫ አሮጌ ስለሆነ ብዙ ጥገና ስለሚፈልግ አዳዲስ ኃይል ሲጨመር ብናመነጭም ማመንጨትና ማድረስ ለየቅል ስለሆነ ይፈተናሉ፡፡ በሪፎርሙ ሰፋፊ ሥራ ከሚያስፈልጋቸው ተቋማት አንዱ እሱ ነው፡፡

ለምሳሌ፣ ቀደም ሲል አላነሳሁላችሁም እንጂ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣የኢትዮጵያ ልማት ባንክ፣የማኅበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ፣ እነዚህ ሦስቱ ላይ የሠራናቸው ሪፎርሞች የዛሬ ሁለት ዓመት ገደማ ባንሠራ ኖሮ አሁን አሜሪካ ላይ የሰማነው ዜና ኢትዮጵያ ላይ ይሰማ ነበር፡፡ ባንኮች ይወድቁ ነበር፣ልማት ባንክ ከትልቅ ኪሳራ ወጥቶ አትራፊ የሆነው አሁን ነው፣ ንግድ ባንክ በጣም በጣም አደገኛ ኮንዲሽን ወስጥ ከነበረበት ወጥቶ አትራፊ የሆነው አሁን ነው፣ በተለይ በተለይ የማኅበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ አስተዳደር የሚባለው ተቀም እስከዚህ ዓመት ድረስ ከትርፍ ጋር አይተዋወቁም፡፡

በዚህ ዓመት በጣም ከፍተኛ ትርፍ አግኝተዋል፡፡ ሪፖርት ሰምታችሁ ይሆናል፡፡ እነዛን ሪፎርሞች በቴሌኮም ያመጣነው ሪፎርም፣ በንግድ ባንክ ያመጣነው ሪፎርም ወደ ኤሌክትሪክ አገልግሎት መውሰድ ያስፈልጋል፡፡ ሰፋፊ ሥራ ያስፈልጋል፡፡ እናንተም ደግፋችሁ ማሻሻል አለብን፡፡ እኛም ይሄን እናምናለን፡፡ ግን አጠቃላይ ውጤቱን በሚያሳንስ መንገድ ባይታይ፡፡

ድርቅን በሚመለከት ኢትዮጵያ ውስጥ ድርቅ አጋጥሞ በእንስሳት ላይ ብዙ ጉዳት አድርሷል፡፡ ያ ድርቅ ወደ ረሃብ እንዳይሸጋገር እንደ 77ቱ በጣም ብዙ ዜጎች እንዳይረግፉ መንግሥትም አጋር ድርጅቶችም የኢትዮጵያ ደጋግ ሕዝብም በትብብር ሰፊ ሥራ ተሠርቷል፡፡ ለዚህ ምስጋና ነው ያለን፡፡ በመጣው ድርቅ ልክ በቂ ሥራ ባይሠራ በርካታ ዜጎች ይጎዱብን ነበር፡፡ በርብርብ የሰዎች ሞት እንዳይኖር ጥረት ተደርጓል፡፡

በመንግሥት በኩል የቅድሚያ ቅድሚያ የሚሹ ወደ 3 ነጥብ6 ሚሊዮን ገደማ የሚጠጉ ከዛም በላይ የሆኑ ሕዝቦች በሦስት ክልል በአስር ዞኖች በ61 ወረዳዎች የቅድሚያ ቅድሚያ ያስፈልጋቸዋል ተብሎ እርዳታ ቀርቦላቸዋል፡፡ ቅድሚያ ደግሞ የሚሹ 6 ሚሊዮን ገደማ የሚጠጉ ሰዎች በ8 ክልል በ32 ዞን በ40 ወረዳዎች እንዲሁ እርዳታ ቀርቦላቸዋል፡፡ ነገር ግን የተከበረው ምክር ቤት ቢያግዝ ጥሩ የሚሆነው፤ እርዳታን በሚመለከት አደገኛ የሆነ ልምምድ እየተፈጠረ ነው ያለው፡፡

10 ሰው ሲራብ መቶ ሰው ነው፤ 50 ሲጠማ 1 ሺህ ነው እያሉ እርዳታን በተቸገረ ሰው ስም የመወሰድና የመነገድ ልምምድ እየሰፋ ነው ያለው፡፡ ይሄን የተከበረው ምክር ቤትም ባለው አክሰስ ቁጥጥር ቢያደርግበት ጥሩ ነው፡፡ እርዳታ ችግር የምንሻገርበት እንጂ የምንኖርበት ጉዳይ መሆን የለበትም፡፡ ባንድ ወቅት የምንሻገርበት እንጂ ልክ በዘላቂ ልክ እንደ የወር ሬሽን የሚታሰብ መሆን የለበትም፡፡ ልማት ነው ያንን የሚቀይረው፡፡ ያንን በናንተ በኩል ድጋፍ ብታደርጉ ጥሩ ነው፡፡

ደቡብ ኦሞን በሚመለከት 6 ወረዳ ውስጥ 300 ሺህ የሚጠጉ ዜጎች ከአጠቃላይ ከደቡብ ኦሞ 37 በመቶ የሚጠጋውን ሕዝብ ረድተናል፡፡ እና ርዳታ ደርሷል፡፡ የሚቀር ነገር እና መጨመርም ያለበት ነገር ካለ አሁንም እንሠራለን፡፡ ነገር ግን ደቡብ ኦሞ በጣም በጣም ሀብታም መልማት የሚችል አካባቢ ነው፡፡ ክረምት ከበጋ የሚፈስ ውሃ ያለው፣ ሰፊ ያልታረሰ መሬት ያለው አካባቢ ነው፡፡

አሁን ከዚያ የመጡት ጠያቂ እንደሚያውቁት አንዱ ከስኳር ጋር ተያይዞ ባለው ካናል በጣም በርካታ ኪሎ ሜትር የኢሪጌሽን ካናል እየገነባን ነው፡፡ ያ ግንባታ ቢጠናቀቅ ለከብቶች ውሃ፣ ከዚያም አልፎ ለእርሻ ለአካባቢው ሳይሆን ከአካባቢው ባሻገር ልማት ሊያመጣ ይችላል፡፡ ተጀምሯል ፤ በጣም በርካታ ሥራ በየቦታው ስላለ ሪሶርስ ውስንነት ስላለ በቂ አይደለም ሊባል ይችላል ፤ የጀመርነውን ሥራ አጠናክረን ደቡብ ኦሞን ተረጂ ሳይሆን ረጂ፣ ለማኝ ሳይሆን ሰጪ ማድረግ እንፈልጋለን፡፡ በዛው አግባብ እንደሚሠራ ተስፋ አለኝ፡፡

ቦረናም እንደዚሁም ቦረናም በጣም በጣም ሰፊ ቦታ ነው ያለው፡፡ እንደምታውቁት ሰፊ ሜዳ ነው ያለው፡፡ የቦረና ችግር ውሃ ብቻ ነው፡፡ ውሃ ቢሄድ በአንድ ዓመት አልፋ አልፋ ምርት ከፍተኛ ሀብት ሊያመጣ ይችላል፡፡ ለከብቶች ብቻ ሳይሆን፡፡ ያም ታስቦ እየተሠራ ነው ያለው የአፍሪካ ዴቨሎፐመንት ባንክ እያገዘን ውሃ ለመውሰድ ጥረት እየተደረገ ነው፡፡ በእኔ እምነት በሚቀጥሉት ዓመታት እነዚህ አካባቢዎች ከለማኝነት ወደ ረጂነት የሚሄዱበት እድል ሰፊ እንደሆነ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡

ዋናው የእኛ ትኩረት ፎከስ ማድረግ ያለበት አንደኛ ዕዳ መቀነስ፣ምርታማትን መጨመር፣ መሠረተ ልማት ማስፋፋት፣ ሌብነት መቀነስ፣ ቱሪዝም እንዲያድግ፣ ሰርቪስ እንዲያድግ ማድረግ ፕሮጀክት በጥራት መፈጸም ፤ይሄንን ካደረግንና ብዙ ጊዜ በሥራ ካሳለፍን ካሳለፍን አሁን እየገጠመን ያለውን መከራ ልናልፍ እንችላለን የሚል እምነት ነው ያለኝ፡፡

በድምሩ ኢትዮጵያ ውስጥ የሰላም ችግር አለ፣ የግጭት ችግር አለ፣ የፖለቲካ ነጋዴዎች የሚያረግቡት ችግር አለ፡፡ ይሄ እንደተጠበቀ ሆኖ በአፍሪካ ውስጥ ሻል ያለ ዕድገት እያስመዘገበ ያለ፣ ሰፋፊ ኢንቨስትመንት እያደረገ ያለ፤ ተቋማት እየገነባ ያለ፣ ኮንሰልዴት እያደረገ ያለ ሀገርና መንግሥት ነው፡፡ ችግሮች አሉበት፣ ፈተናዎች አሉበት ቅድም እንዳልኩት እንደ ላውንዴሪው ነው፡፡ እየተተኮሰ እየታደሰ እየተጠገነ የሚሄድ መንግሥትና ሀገር ነው፡፡ ችግሮችን በዚህ አይተን ለመፍትሔ ከሰራን ውጤት እንደሚመጣ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡

ትግራይን በሚመለከት በቅርቡ የአሸባሪነት አዋጅ እንዲነሳ አድርጋችኋል፡፡ ለዚያ ከፍተኛ ምስጋና አቀርብላችኋለሁ፡፡ በነበረው ውይይት ጥያቄ የነሱና ነገሩ እንዲመረመር የፈለጉ ሰዎች ነበሩ፡፡ የእነርሱም ሀሳብ መከበር አለበት፣ እነርሱ እንደሰጉት ጉዳዩ የሚያሰጋ ሆኖ አይደለም፤ መፈተሽ ያለበት ጉዳይ ስላልነበረ አይደለም፤ ሰላሙ ይበልጥብናል ብለን ይቅር ብለን የምናደርገው ጉዳይ እንጂ ሁሉም ነገር መቶ በመቶ ተሟልቷል ችግር የለም በሚል አይደለም፡፡ እና ያንን የነበረውን የሀሳብ ልዩነት ሰብሰብ አድርገን እንዴት ነው የትግራይ ሕዝብን ወደተቀረው ወንድም ሕዝቦች የምናመጣው፣ ተጎዳሁ ተበደልኩ የሚለውንስ በልኩ እንዴት አይተን ማገዝ እንችላለን ከእኛ ይቅር ብለን እንዴት ማቀፍ እንችላለን የሚለውን ጉዳይ የተከበረው ምክር ቤት እንዲያይ እፈልጋለሁ፡፡

ቅድም ኢትዮጵያ እንድትበትን አትሥሩ የተባለው ጉዳይ የሚሠራው ለዚህ ጉዳይ ነው፡፡ ኢትዮጵያ እንድትበተን ካልፈለጋችሁ ትግራይን ጎብኙ፡፡ እንድትበትን ካልፈለጋችሁ እዚያ ያለውን ችግር በልኩ ተገንዝበን ለማገዝ ልባችን የሰፋ ይሁን፡፡ ትግራይ አካባቢ ያለው ሰው በአማራ ክልል ችግር ያለ አይመስለውም፤ አማራ ምንም ነገር የተጎዳ አይመስለውም፡፡ በኦሮሚያ ክልል ምንም ችግር ያለ አይመስለውም፤ አድምጠን እኛም ጋ ችግር አለ፤ እኛም ጋ በደል አለ እያልን ይህን በውይይት የምናቅፍበትን መንገድ መፍጠር ያስፈልጋል፡፡

በኦሮሚያ አካባቢ ከአማራ ጋር ያለው አንዳንድ ሽኩቻዎች የኢትዮጵያን ሰላምና ልማት የሚጎዱ ብቻ ሳይሆን ከማንም በፊት ከየትኛውም ብሔር በፊት ኦሮሞንና አማራን ነው የሚጎዱት፡፡ አይጠቅሙም፤ መስከን መርጋት መወያየት ያስፈልጋል፡፡ በስፋት የተዋለድን የተጋባን አብረን የምንኖር ስለሆንን ጉዳቱ ቤት ውስጥ ነው የሚሆነው፤ ይሄ እንዲቀር ብልህ መሆን ያስፈልጋል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ሚዲያዎቻችን በወል በጣም ስለሚሳደቡ፤ እነርሱ ዋሽንግተን ይሳደባሉ ጅማ ላይ ያለ አንድ ዜጋ ይጎዳል፡፡

እንደዚያ እንዳይሆን የአማራ አካባቢ ተወላጆች ምንም ቢሆን ከነድካሙም የኦሮሞ ወንድምነት ይሻላል ብለን ለእሱ እንሥራ፤ በኦሮሞ አካባቢ ያለን ሰዎች የፈለገ ችግር ቢኖር የአማራ ወንድም ይሻላል ብለን እንሥራ፤ የሚያዋጣው እሱ ነው፡፡ መገፋፋቱና ከልክ ያለፈው ውጥረት እኛኑ ከመጉዳት ያለፈ ጥቅም የለውም፡፡ የመጨረሻው መልዕክቴ እነዚህ ኃይሎች ከተደመሩ ከተጋገዙ ለኢትዮጵያ ፍቱን መድኃኒት ይሆናሉ፡፡ ካልተጋገዙ ሁለቱም ይጎዳሉ የሚጠቃቀም የለም፡፡

ይሄን አስበን እንሂድ፤ ሥልጣን በምርጫ እናድርግ፡፡ ውይይት እንመን፤ በሀሳብ እንመን፤ ያለውን ጥላቻና ውጥረት እንቀንስ፤ በዚህ አግባብ የተጠናከረች ኢትዮጵያን ለመፍጠር አበክረን እንስራ፡፡ የተከበረው ምክር ቤት ሦስት ዓመት አላችሁ በዚህ ሦስት ዓመት ውስጥ ጠንክረን ውጤት ለማምጣት እንሥራ ከዚያ በፊት የሚታሰብ ማንኛውም ነገር አይሆንም፤ አመሰግናለሁ!

ስፖርትና መዝናኛ

# የዘመን ጥበብ

## የዓባይን ነገር ጥበብ ሲመሰክር

**ዋለልኝ አየለ**

በዓባይ ጉዳይ ላይ ብዙ ብለናል፤ ከዚህም በላይ ብዙ ማለት አለብን። እንዲያውም በሚፈለገው ልክ አልዘመርንለትም የሚል ወቀሳ ነው የሚደጋገመው እንጂ በዛ የሚል አይደለም። ዓባይ ሕይወት ነዋ!

ግብጾች «ዓባይ የግብጽ ሕይወት ነው!» የሚለውን መፈክር ዓለም አቀፍ አድርገውታል። ከልሂቅ እስከ ደቂቅ ስላስተጋቡት ማለት ነው። ዓባይ ለኢትዮጵያ ሕይወት መሆኑን ግን በሚገባው አልተናገርነውም።

ዓባይ ለኢትዮጵያ ሕይወት መሆኑን ከሚመሰክሩ ነገሮች አንዱ የሕዝብ ሥነ ቃል የጥበብ ውጤቶች ናቸው። ምክንያቱም እነዚህ የጥበብ ውጤቶች ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲወርዱ ሲወራረዱ የመጡ ናቸው። የሕዝቡን ታሪካዊና ነባራዊ ባለቤትነት የሚገልጹ ናቸው። እንዴት የሚለውን ከሥነ ቃል ግጥሞች እናያለን።

ዓባይ ለግብጽ የኃይል ምንጭ ሲሆን ለኢትዮጵያ ደግሞ የጥበብ ምንጭ ጭምር ነው። ዓባይ «ከኢትዮጵያና ከግብጽ ማንን ታውቃለህ?» ተብሎ ቢጠየቅ «ኢትዮጵያን» ማለቱ አይቀርም። ምሁራን አንድ የሚሉት ነገር አለ። ይሄውም፤ ግብጽ ውስጥ ከህፃን እስከ አዋቂ፣ ከአርሶ አደር እስከ ወታደር ያውቁታል የሚል ነው። እንዲያውቁት ደግሞ ስለዓባይ በሰፊው ይሰበካሉ። በሥርዓተ ትምህርታቸው ውስጥ ይካተታል፤ መገናኛ ብዙኃኖቻቸው ይደጋግሙታል፤ አለፍ ሲልም ለፖለቲካ ፍጆታ ይጠቀሙታል። ይህን የሚሉ ምሁራን በተቃራኒው ኢትዮጵያ ውስጥ ግን ትኩረት እንዳልተሰጠው ይናገራሉ። አዎ! እውነት ነው አልተሰጠውም።

ግን፤ እውነት ዓባይ ከግብጽ በላይ ኢትዮጵያ ውስጥ አልተዘመረለትም? ዓባይ ከግብጽ በላይ ኢትዮጵያ ውስጥ ተዘምሮለታል፤ ተነግሮለታል፤ ተዘፍኖለታል። ልዩነቱ ብዙም ምርምር አይጠይቅም፤ ግብጽ ውስጥ በስብከት ሲሆን ኢትዮጵያ ውስጥ ግን በተፈጥሮ ነው። ዓባይ ለግብጽ ህልውና የሆነው በፖለቲከኞች ስብከት ሲሆን ኢትዮጵያ ውስጥ ግን ከህዝቡ ጋር በተፈጠረ ባህልና ማንነት ነው። ዓባይ ለኢትዮጵያ ማንነት ነው።

ዓባይ የኢትዮጵያ ማንነትና ምንነት ለመሆኑ ደግሞ ምስክሮቻችን ሥነ ቃሎች ናቸው። የባህል ጥናትና የሥነ ጽሑፍ ባለሙያዎች እንደሚሉት ደግሞ ሥነ ቃል የአንድ ማህበረሰብ ምንነት ነው። ምክንያቱም ሥነ ቃል በመንግሥት ትዕዛዝ ወይም በአንድ ወገን ጫና የሚፈጠር ሳይሆን ማህበረሰባዊ ሥነ ልቦና የሚገለጽበት ነው። ሕዝብ ብሶቱንና ደስታውን የሚገልጽበት ነው። እነዚህ የስሜት መግለጫ የሆኑ የሥነ ቃል ሀብቶች ደግሞ የሚፈጠሩት ከሚታየው ነባራዊ ሁኔታ ነው። ለዚህም ነው የአንድ ማህበረሰብ ታሪካዊ ታሪክ ሲጠና ትውፊቱ መነሻ የሚሆነው።

እንግዲህ ዓባይ የኢትዮጵያውያን ማንነትና ምንነት ባይሆን ኖሮ ሥነ ቃሎቻችን እንዲህ በዓባይ አይጥለቀለቁም ነበር ማለት ነው። በተረትና ምሳሌዎቻችን ውስጥ ዓባይ አለ፤ የደስታና የኀዘን እንጉርጉሮዎቻችን ውስጥ ዓባይ አለ፣ በባህል ዘፈኖቻችን ውስጥ ዓባይ አለ፣ በስም አወጣጣችን ውስጥ ዓባይ አለ... ዓባይ በብዙ ነገሮቻችን ውስጥ አለ።

ተረትና ምሳሌዎቻችን፣ እንጉርጉሮዎቻችን ሁሉ የሚያሳዩት የዓባይን ግዙፍነት ነው። በሌላ በኩል የዓባይን አስቸጋሪነትና አደገኛነትም የሚያመለክቱ ናቸው። ከግብጽ ጋር ያለን ልዩነትም እዚህ ላይ ይመስላል። ግብጾች የሚዘምሩለት በጠቃሚነቱና በሕይወትነቱ ብቻ ሲሆን ኢትዮጵያ ውስጥ ግን በአስቸጋሪነቱም ተዘምሮለታል። ይሄውም በክረምት ወራት የዓባይ ወዲያ ማዶና የዓባይ ወዲህ ማዶ ሰዎችን ስለማያገናኝ ነው። ያኔ በዘመኑ ድልድይ የሚባል ነገር ስለማይታወቅ በዋና እና በእግር በመሻገር ብቻ ስለነበር ስለአስቸጋሪነቱ ተዘፍኖለታል። አብዛኞቹ ተረትና ምሳሌዎች፣ እንጉርጉሮዎች ግን ስለግዙፍነቱ የሚመሰክሩ ናቸው።

ከተረትና ምሳሌዎቻችን ውስጥ፤ ዓባይን ያላየ ምንጭ ያመሰግናል፣ ዓባይ ማደሪያ የለው ግንድ ይዞ ይዞራል፣ ዓባይ ቢሞላ ተሻገር በሌላ፣ ዓባይ አንተ አየኸኝ ከደረት እኔም አየሁህ ከጉልበት፣ ዓባይና ስንቅ እያደር ይቀላል፣ ዓባይን በጭልፋ፣ የዓባይን ልጅ ውሃ ጠማው፣ የሰው ቤት ዓባዩ... የሚመሳሰሉት ይጠቀሳሉ። አብዛኞቹ ግዙፍነቱን የሚገልጹ ሲሆኑ አንዳንዶቹም ተጓዥነቱንና አስቸጋሪነቱን የሚገልጹ ናቸው። ዓባይን ያላየ ምንጭ ያመሰግናል የሚባለው አንድ ሰው ትንሽ ነገር ሲያደንቅ ነው፤ ከዚህም የበለጠ አለ ለማለት ነው። ለምሳሌ የአንዲት የገጠር ከተማን ሕዝብ ብዛት ለሚያደንቅ ሰው እነ አዲስ አበባን ለመግለጽ «ዓባይን ያላየ ምንጭ ያመሰግናል» ሊባል ይችላል። የዓባይ ግዙፍነት ሌሎች ነገሮችን ለመግለጽ እንደ ማንፀሪያ ያገለግላል ማለት ነው። ዋና ዓላማችን ተረትና ምሳሌዎቹን ማብራራት ስላልሆነ እንደየ ዓውዳቸው እንጠቀማቸዋለን።

አሁን ከተረትና ምሳሌዎች (ምሳሌያዊ ንግግሮች) ወደ ቃል ግጥሞች እንሂድ። የቃል ግጥሞች በጣም ብዙ ናቸው። በተለይም በባህል ዘፈኖች ውስጥ ይደጋገማሉ። የባህል ዘፈኖች ሲባል በካሴት ወይም ሲዲ እና ዲ ቪ ዲ የወጡትን ሳይሆን እረኞችና ገበሬዎች የሚዘፍኑትን ለማለት ነው። ዓባይ ኢትዮጵያ ውስጥም ከእረኛ ጀምሮ እንደሚታወቅ የምናውቀውም በእነዚህ የሥነ ቃል ዘፈኖቹ ነው። ለምሳሌ የፍቅር ዘፈኖችን እንይ።

በድሮው ጊዜ ዓባይን መሻገር የሚቻለው በበጋ ወቅት ውሃው በመጠኑም ቢሆን ሲቀንስ ተጠብቆ ነበር። እንደ ዛሬው ድልድይ የለም፣ መኪና የለም። አንድ ከዓባይ ወዲህ ማዶ ያለ ኮበሌ ከዓባይ ወዲያ ማዶ ያለች ጉብል ካፈቀረ መገናኘቱ ከባድ ነበር። የሚገናኙት የበጋ ወቅት ጠብቀው ነው። የፍቅረኛው ናፍቆት ሲጠናበት በማሽላ ይመስላታል። እንዲህም ሲል ያንጎራጉራል።

**ዓባይ ወዲያ ማዶ ማሽላ ዘርቼ**
**ወፎች ጠረጠሩት መሻገሪያ አጥቼ**

«ወፎች« ተብለው የተገለጹት ፍቅረኛውን የሚነኩበትን ሌሎች ወንዶች ነው። በዚህ ቅኔ ለበስ ግጥም ውስጥ ብሶቱን ይገልጻል። ከዓባይ ወዲያ ማዶ አፍቅሬ ማግኘት አልቻልኩም ማለቱ ነው። ባስ ሲልበት ደግሞ እንዲህ በማለት ፈጣሪን ይማጸናል።

**አንቺ ወዲያ ማዶ እኔ ወዲህ ማዶ**
**አንገናኝም ወይ ተራራው ተንዶ?**

ተራራ ተብሎ የተገለጸው የዓባይ ውሃ ነው። የያኔው አፍቃሪ ፀሎት ሰምሮ እነሆ ዛሬ ተራራው ተንዷል። ከዓባይ ወዲህ ማዶ ያለ አፍቃሪ ከዓባይ ወዲያ ማዶ ያለች ፍቅረኛው እንዲህ ህልም አትሆንበትም። ያ የከለከለው ተራራ በዓባይ ድልድይ ተንዷል። በፈለገው ቀን ሄዶ ፍቅረኛውን ማግኘት ይችላል።

የዓባይ ውሃ ክረምቱን ሙሉ እንዲህ ሰውን ያቆራርጥ ነበር። መገናኘት የሚቻለው በበጋ ወቅት ነው። ፍቅሩ ብሶበት የበጋ ወቅት የሚጠባበቀው አፍቃሪ እንዲህ ሲል ተስፋ በቆረጠ አንጀት ይዘፍናል።

**ዓባይ ጉደል ብለው አለኝ በታህሣሥ**
**የማን ሆድ ይችላል እስከዚያ ድረስ?**

ታህሳስ የበጋ ወቅት የመጀመሪያው ወር ነው። ይሄን የበጋ ወቅት መጠበቅ ያልቻለ አፍቃሪ፣ ያለው አማራጭ በዋና መሻገር ነው። በእርግጥ ይህ የሚሆነው ደግሞ ዋና ለሚችል ሰው ነው። ዋና የሚችለው ደግሞ እንዲህ ሲል ይዘፍናል።

**እስኪ ልሻገረው ዓባይን በዋና**
**የጎጃም ልጅ ወደ ምን እንቀልፍ አለና!**

አፍቃሪው የሸዋ ሰው ሊሆን ይችላል። ወደ ጎጃም ለመሻገር ደግሞ በመሃል ዓባይ አለ። በነገራችን ላይ ዓባይ ውሃው ብቻ አልነበረም አስቸጋሪ። ወደ ወንዙ የሚያስገቡ መንገዶች ሁሉ ዳገትና ገደል ናቸው። በዋና እንኳን ለመሻገር ብዙ አስቸጋሪ መንገዶችን በእግሩ ሄዶ ነው። የወንዝ ዳር መንገዶች እንደሌላው ምቹ አይደሉም። ወደ ወንዙ ሲወርድ ቁልቁለት አለ፤ ከተሻገረ በኋላ ደግሞ አቀበት (ዳገት) አለ። ቁልቁል ሲወርድ እሷን ለማግኘት ነውና ይጨንቀዋል (በዚያ ላይ የውሃው ስጋት አለ) ከተሻገረ በኋላ ደግሞ በችኮላ አቀበቱን ይወጣዋል። ይሄኔ እንዲህ እያለ ይዘፍናል።

**ዓባይ ቁልቁለቱን እምባዬ እያነቀኝ**
**ዓባይ አቀበቱን ላብ እያጠመቀኝ**
**መቅረትስ አልቀርም**
**እስከዚያው ጨነቀኝ።**

የዓባይ ውሃ መሙላት አንዳንዴ ደግሞ ጥሩ አጋጣሚም ይፈጥራል። ይህ የሚሆነው ከዓባይ ወዲያ ማዶ ያለችዋ ተፈቃሪ አፍቃሪዋ ጋ ወዲህ ማዶ እንደመጣች ውሃው ከሞላ ነው። ምክንያቱም አትሄድም። ይህን አጋጣሚ ሲያገኝ

**ዓባይ ሞላ አሉ ሞላ አሉ**
**እንደ ዕድሌ ሁሉ**

እያለ ይዘፍናል። አንዳንዱ ደግሞ እንዲህ በማለት ቀጭን ትዕዛዝ ይሰጣል።

**ዓባይ ቢሞላ ቢሞላ**
**ዞረሽ ነይ በሌላ!**

በእርግጥ እሷን ብቻ ሳይሆን ለራሱም እንዲህ ብሏል።

**ዓባይ ሞላ ብየ ሞላ ብየ**
**አልቀርም ሸግየ**

አንዳንዱ ደግሞ ትንቢት ይገለጥለታል። የዓባይ መሙላት እንዲህ አስቸጋሪ ሆኖ አይቀርም ያለ አፍቃሪ እንዲህ ብሎ ነበር።

**ዓባይም ቢሞላ ቢሞላ**
**አለው አሉ መላ**

የዚህ ትንቢት ፈጣሪ፣ «መላው» ምን እንደሆነ አልነገረንም፤ «አለው አሉ መላ» ብሏል። እነሆ መላው ተገኝቶ ዛሬ የዓባይ መሙላት ፍቅረኞችን መለያየት አልቻለም። ሰውየው የተናገረው ነገር ምናልባትም ድልድይ ሊሰራ እንደሚችል ታይቶት ነበር ብለን እንያዝለት።

የሥነ ቃል ዘፈኖችና ምሳሌያዊ አነጋገሮቻችን ብዙ ጥልቅ ሃሳብ ያላቸው ናቸው። ዓባይ ከኢትዮጵያውያን ጋር ያለውን ባህላዊና ታሪካዊ ትውፊት የሚያሳዩ ናቸው። የዓባይንና የኢትዮጵያን ሕዝብ ሥነ ልቦናዊ ትስስር ፍንትው አድርገው የሚያሳዩ ናቸው።

ዓባይ የጥንት ኢትዮጵያውያን አበው ብቻ አይደለም። ዓባይ ለዚህ ትውልድም ገናና ማንነት ነው። ይሄ ትውልድም ገናና አሻራውን ያሳረፈበት ነው። ይሄ ትውልድም የተጠበበበት ነው። ስለዓባይ ያልዘፈነ የለም፤ ያልተቀኘ የለም፣ ያልገጠመ የለም፣ ያልሳለ የለም፣ ያልተወነ የለም! ዓባይ ለብዙ ከያኒያን የጥበብ ምንጭ ሆኗል። ለዛሬው ዘፋኞችን ብቻ እናያለን። የሁለት ዘፋኞችን ስንኞች መልዕክት እንያቸው። በ2003 ዓ.ም የአባይ ግድብ የመሰረት ድንጋይ ሲጣል ከዜናው እኩል ተሰምቷል። ስለ ግድቡ ለሚሰሩ ፕሮግራሞች ሁሉ ማጀቢያ ነበር። የድምጻዊት ገነት ማስረሻ «ዓባይ ጭስ አልባው ነዳጅ» የተሰኘው ዘፈን አሁን ድረስ የፕሮግራሞች ማጀቢያ ነው። ከዚያ ወዲህ ስለ ግድቡ ብዙዎች ቢዘፍኑም ቀዳሚ በመሆኑ ይመስላል ይደጋገማል፤ በሌላ በኩል ደግሞ ስንኞቹ ጥልቅ መልዕክት አላቸው። እስኪ ጥቂቶችን እንያቸው።

**አደባልቆት ሲሄድ ጥቁር እና ነጩን**
**ግዮን አበሻ ነው ማን ይነካል ምንጩን!**
**ዓባይ አንተ እያለህ ታላቁ ወንዛችን**
**መሳለቂያ አንሆንም በድህነታችን።**

አዎ! ዓባይን የሚያህል ግዙፍ ሀብት ይዘን መሳለቂያ ሆነናል። ለመዝገበ ቃላት የድህነት ትርጉም መፍቻ ሆነናል። ይሄ ሁሉ ሲሆን ከኢትዮጵያ ተነስቶ የኢትዮጵያን ጋራና ሸንተረር አቆራርጦ፣ የኢትዮጵያን አፈር እያደባለቀ የሚሄድ ነው። «አደባልቆት ሲሄድ ጥቁር እና ነጩን» የሚለውን ቅኔ በየራሳችን መተርጎም ነው።

**ዘመን ቢያስታርቀን ከዓባይ ብንስማማ**
**ይዘን ተጠጋነው አካፋና ዶማ**

ዓባይ ለዘመናት ለቀረርቶና ለፉከራ የግጥም ምንጭ ብቻ ሆኖ ኖሯል። እነሆ 2003 ዓ.ም ላይ ግን ታሪክ ተቀየረ። አካፋና ዶማ ይዘን ተጠጋነው።

**ማደሪያ ሳይኖረው ግንድ ይዞ ይዞራል**
**የሚባለው ተረት ከእንግዲህ ይቀራል**
**እንዲህ እንደ ዛሬው መልካም ቀን ሲመጣ**
**ግንድም ይዘህ አትዞር ማደሪያም አታጣ።**

አዎ! ተረት እውን ሆነ። «ዓባይ ማደሪያ የለውም ግንድ ይዞ ይዞራል» የሚለው ተረትና ምሳሌ ራሱ ተረት ሆነ። ዓባይ ማደሪያ አገኘ፤ ሥራው ግንድ ይዞ መዞር ሳይሆን ኃይል ማመንጨት ሆነ።

**ዓባይ እኔና አንተ ሳይሉን ቸር ሆነን**
**ፎከሩብን እንጂ ማን አመሰገነን!**
**በራሳችን ውሃ በረሳችን አፈር**
**ተዘባበቱብን ተመጠጠ ከንፈር!**

ዓባይ ለዘመናት ለኢትዮጵያ ምንም ሳይጠቅማት ግብጽንና ቅኝ ገዥ አገራትን ሲያወዳጅ ኖሯል። ግብጽን አበልጽጓል። ኢትዮጵያ ግን አልተመሰገነችም፤ እንዲያውም መሳለቂያና መዘባበቻ አደረጓት። በራሷ ውሃና አፈር መሳለቂያ ሆነች፤ በሌለችበት እንደፈለጋቸው ይፈራረሙበታል፤ ይወዳጁበታል። አቅም የላትም፣ አትገነባውም የሚል ንቀት መሆኑ ነው።

**ስንት ዘመን ቁጭት ስንት ዘመን ግጭት**
**ስንት ዓመት በጣሳ ስንት ዓመት በወጪት!**
**ፍሰስበትና በሀገርህ ሜዳ**
**የሚቆጣም ካለ ያበጠው ይፈንዳ!**

አሁን ተረቱም ፉከራውም ይበቃል፤ «ዓባይን በጭልፋ፣ ዓባይን በወጪት...» የሚሉ ተረትና ምሳሌዎች ወደ እውን ይቀየሩ። እነሆ ዓባይ ይገደብ እንደማለት ነው፤ «አትገድቡም» የሚል ካለም ኢትዮጵያውያን ያውቁበታል ለማለት ነው።

መቼም የዓባይ ነገር ከተነሳ ከወንዙ እኩል ስመ ገናና የሆነችው ድምጻዊት እጅጋየሁ ሽባባው (ጂጂ) በሁላችንም ልብ ውስጥ ናት። አንድ ለሙዚቃ ምንም ቅርበት የሌለው ሰው «እስኪ የአንድ ዘፋኝ ስም ተናገር» ቢባል «ጂጂ» ማለቱ አይቀርም። ጂጂ ከዓድዋ እና ከዓባይ እኩል ስሟ ይነሳል፤ ምክንያቱም ዓድዋንም ዓባይንም በብዙዎች ልብ ውስጥ እንዲሰርጹ አድርጋለች። መዝፈን ቢሉ ዝም ብሎ መዝፈን ሳይሆን ልብን ሰርስረው በሚገቡ ጥልቅ ስንኞች በመቀኘት ነው።

ጂጂ ለዓባይ የዘፈነችው ሊገደብ ነው ሲባል አይደለም፤ ማንም ባላሰበበት ወቅት ነው። እውነተኛ ጥበብም እንዲህ ነው፤ ቀድሞ ይተነብያል፤ የሌሎችን አይንና ልብ ይከፍታል። ጂጂ ዓባይን እንዲህ ስትለው ኖራለች።

**የማያረጅ ውበት የማያልቅ ቁንጅና**
**የማይደርቅ የማይነጥፍ ከዘመን የፀና**
**ከጥንት ከፅንስ አዳም ገና በፍጥረት**
**የፈሰሰ ውሃ ቀድሞ ከገነት**

ጂጂ የዓባይን ታሪካዊና ጥንታዊነት ነው የነገረችን። ዓባይ የማያረጅ ውበት መሆኑ ደግሞ ቀደም ሲል ያየናቸው የማህበረሰቡን ሥነ ልቦና የሚገልጹ ሥነ ቃሎችም ይነግሩናል። ከሰው ልጅ ፍጥረት ጋር ያለውን ቁርኝትና የሥልጣኔ አስጀማሪነቱን ትነግረናለች። «ግርማ ሞገስ የአገር ፀጋ የአገር ልብስ» እያለች የዓባይና የኢትዮጵያን ታሪካዊና ተፈጥሯዊ አንድነት ትነግረናለች።

**ዓባይ**
**የበረሃ ሲሳይ**
**ብነካው ተነኩ! አንቀጠቀጣቸው**
**መሆንህን ሳላውቅ ስጋና ደማቸው!**

ይሄ እንግዲህ የዘመኑን ወቅታዊ ሁኔታ እንኳን ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ነው። ዓባይ ለግብጻውያን ስጋና ደማቸው ነው፤ ሲነካ ያንቀጠቅጣቸዋል። ለዚህም ነው በመገናኛ ብዙኃኖቻቸው የውሸት ዜና ሳይቀር የሚያሰራጩት። ግብጾች ምንም አይነት ውስጣዊ ችግር ቢያጋጥማቸው ከዓባይ ፕሮፖጋንዳ ዝንፍ አይሉም። እንዲህ አይነቱን እውነታ ነው የጂጂ ስንኞች የሚነግሩን።

**የሚበሉት ውሃ የሚጠጡት ውሃ**
**ዓባይ ስጋሲ ነው በዚያ በበረሃ**

ልብ በሉ እነዚህን ስንኞች! የሚበሉት ውሃ፤ የሚጠጡት ውሃ። እንዲህ ላወቁበት ውሃ የሚጠጣ ብቻ ሳይሆን የሚበላም ነው። ውሃን የምናውቀው እንደሚጠጣ ነው፤ በልማድ ውሃ ይበላል አንልም፤ በሳይንሳዊ ጥበብ ግን ውሃ ይበላል። ልክ እንደ ግብጽ ላወቀበት ማለት ነው። «ውሃ እንዴት ይበላል?» ሳይንሳዊ ማብራሪያ የሚያስፈልገው አይመስለኝም!

**ዓባይ ዓባይ**
**ዓባይ ወንዛወንዙ**
**ብዙ ነው መዘዙ!**

አዎ! የዓባይ ጉዳይ የባለቤቶች ብቻ አልሆነም። ከአውሮፓ እስከ እስያ፣ ከአፍሪካ እስከ አሜሪካ በአንድም ይሁን በሌላ መልኩ እጃቸውን አስገብተውበታል። አገራት ተጣልተውበታል፤ ተወዳጅተውበታል። በዓለም አደባባይ ስሙ የተነሳባቸው አጋጣሚዎች ብቻ ናቸው። ዓባይ ጓዙም መዘዙም ብዙ ነው።

**ዓባይ የወንዝ ውሃ አትሆን እንደሰው!**
**ተራብን ተጠማን ተቸገርን ብለው**
**አንተ ወራጅ ውሃ ቢጠሩህ አትሰማ**
**ምን አስቀምጠሃል ከግብፃች ከተማ?**

**ዓባይ ሰው አይደለም፤** እንዳደረጉት ይሆናል። ከገደቡት ይገደባል። በዚህ የጂጂ ስንኝ ውስጥ እንደ ሰው ታናግረዋለች። መልዕክቱ የሚነግረን ግን እኛም እንደ ግብጾች ማድረግ እንዳለብን ነው።

እጅጋየሁ ሽባባውም ሆነች ሌሎች ከያኒያን ዓባይን በጥበባቸው ገልጸዋል። ከእነዚህ ሁሉ በላይ ደግሞ የእረኞችና የገበሬዎች እንጉርጉሮዎች ቀድመው ዓባይን ተረድተውታል። ከዚህ የምንረዳው ዓባይ ግብጽ ውስጥ ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያ ውስጥም ሕይወት እንደነበር ነው። ከዚህ በኋላ ዓባይ የጥበብ ብቻ ሳይሆን የኃይልም ምንጭ ይሆናል!

ማህበራዊ

# ልዩ ልዩ

## ኦትስቲክ ልጆችን ከብቸኝነት ለማላቀቅ በሕብረት የመትጋት እንቅስቃሴ

**ሰላማዊት ውቤ**

ኦቲዝም የዘላቂ አእምሮ እድገት እክል ነው። ሆኖም ሕብረተሰቡ ስለ ችግሩ ብዙ መረዳት የለውም። የዓለም የኦቲዝም ቀን የተሰየመውና በየዓመቱ በሚያዝያ ወር ወሩን ሙሉ በተለያዩ ዝግጅቶች የሚከበረው በሕብረተሰቡ ዘንድ ስለበሽታው ግንዛቤ እንዲኖር ለማድረግ ነው።

ይሄንኑ አስመልክቶ ባለፈው ማክሰኞ በሀገር ደረጃ በኦቲዝም ዙርያ የሚሰሩ ማዕከላት በጋራ በመሆኑ በስካይ ላይት ሆቴል በጋዜጣዊ መግለጫ የታጀበ አንድ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ አዘጋጅተው ነበር። የዚህ መድረክ አስተባባሪ አቶ ተስፋዬ ገብረማርያም እንደተናገሩት የዘላቂ አእምሮ እድገት እክል የሆነው ኦቲዝም ምልክቶቹ በልጆች ላይ መታየት የሚጀምሩት የልጆቹ ዕድሜ ሦስት ዓመት ከመድረሱ በፊት ሲሆን ከሌሎች ሰዎች ጋር ግንኙነት ለመፍጠርና ለመግባባት መቸገር፤ ለተወሰኑ ነገሮች ብቻ ፍላጎት ማሳየት፤ ተደጋጋሚ ባህርያትን ማሳየት፤ ለድምፅ፤ ለንክኪ፤ ለጣዕም፤ ለሽታ፤ ለብርሃንና ለቀለም የተለየ ስሜት ማሳየት በበሽታው በተጠቁ ልጆች ላይ አብዝቶ መስተዋል የበሽታው ባህርይ ነው።

ሰው ግን እንደ ፈጣሪ ቁጣና እንደ እርግማን ወይም በምድር ላይ እንዳልታየ እንደ ሌላ የከፋ በሽታ ይወስደዋል። ኒያ ፋወንዴሽንና በበሽታው ዙርያ የሚሰሩ ማዕከላት ይሄን አመለካከት ለመስበር ብዙ ሲሰሩ ቆይተዋል። በተለይ ጤና ሚኒስቴርን ጨምሮ መንግሥታዊ የሆኑ ተቋማት በብርቱ ሲደግፏቸው የነበረበት ሁኔታ ነበር። ሆኖም በተለይ የግንዛቤ ችግሩን መቀነስ እንጂ መቅረፍ አልቻሉም። ስለዚህ በማዕከላቱ በተበታተነ መልኩ ሲሠሩ የነበሩ ሥራዎችን ተቀራርቦ መስራት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል። ከዚሁ በመነሳት መድረኩ የኢትዮጵያ ኦቲዝም ሶሳይቲ ማህበር መመስረት የሚያስችልም ምክክር ለማድረግ ታስቦም ነው የተዘጋጀው። የማህበሩ መመስረት ‹‹ማዕከላቱ በየግላቸው ያካበቱትን ልምድ፣ አቅምና ዕውቀትም አስተባብሮ ለመጠቀምና የተሻለ ሥራ ለመሥራት ያግዛል ብለን እናስባለን›› ያሉት አስተባባሪው ችግሮችን እንደሚቀርፍና ጠንካራ ሕብረት



**በኦቲዝም የተያዘ አውቲስቲክ ልጅ**

በመፍጠር፤ ለተጎጂዎቹ ተንከባካቢ ባለሙያ፤ የሕክምና ባለሙያ በማፍራትና ሌሎች ችግሮችን በመቅረፍና ተጨባጭ ለውጥ ለማምጣት እንደሚያግዝም አውስተዋል።

አስተባባሪው የጤና ባለሙያዎች መረጃን ጠቅሰው እንዳሉት ኦቲዝም በኦቲዝም ጥላ ሥር ከሚገኙ በሽታዎች መካከል አንዱ እንደሆነ ሲናገሩ ይደመጣሉ። በአምስቱም የጤና እክሎች የተጠቁ ልጆች የተለያየ ባህርይ የሚያሳዩበት ሁኔታ ቢኖርም አምስቱንም እክሎች የሚያመሳስሏቸው ባህርያት እንዳሉም በዘርፉ ሕክምና የተሰማሩ የጤና ባለሙያዎች ይናገራሉ። ከሚያመሳስሏቸው ባህርያት ሦስት መሰረታዊ እክሎች ይጠቀሳሉም።

በኦቲዝም የተጠቃ ልጅ ያላቸውና በመድረኩ ተሞክሯቸውን ያካፈሉት ወይዘሮ ራሄል አባይነህ መግባባት አለመቻል አንዱ መሆኑን ይናገራሉ። እሳቸው ከተሞክሯቸው ተነስተው እንዳሉት ኦቲስቲክ ልጆች በድምጽም ሆነ በድምጽ አልባ ቋንቋ (በምልክት) ለመግባባት በእጅጉ መቸገራቸው ነው።

ወይዘሮ ራሄል አምስቱ እክሎች ከሚያመሳስሏቸው ሁለተኛው ማህበራዊ ግንኙነት መፍጠር አለመቻል ሲሆን ሦስተኛው በየትኞቹም ድምጾች ታግዘው ማህበራዊ ግንኙነት ለመፍጠር አለመቻል እንደሆነም ያሰምሩበታል። ታዲያ አሁን ላይ የነህሚያ ኦቲዝም ማዕከል መሥራችና ዳይሬክተር የሆኑት ወይዘሮ ራሄል በመድረኩ እንደተናገሩት የወለዱት በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ (ህመም)ውስጥ ያለ ልጅ መሆኑን ሲያውቁ በጣም ደንግጠው ነበር።

ለእኛ እንዳጫወቱንም ልጃቸው ኦቲዝም ያለው መሆኑን ያወቁት በሦስት ዓመት ከስድስት ወር የወለዷቸውን ልጆች ቤት ውስጥ ቁጭ ብለው በመንከባከብ ራሳቸው ካሳደጉ በኋላ ወደ ሥራ መግባት እንዳለባቸው ከባለቤታቸው ጋር ተመካክረው ቆይተው የራሳቸውን ሥራ ለመሥራት ዝግጅት እያደረጉ ባለበት ጊዜ ነበር። በመሆኑም ሌላውን ሥራቸውን ትተው ሥራቸው ዘንድሮ 16ኛ ዓመቱን የያዘውንና ሁለተኛውን በኦቲዝም የተጠቃ ልጃቸውን መንከባከብ ሆነ።

‹‹በበሽታው የተጠቁ ልጆችን መንከባከብና ማሳደግ እጅግ ከባድ ነው›› በሽታው ስለሚያቅበዘብዛቸው አድካሚ ክትትልና ቁጥጥር እንደሚጠይቅም ያወሳሉ። ‹‹ክትትሉ 24 ሰዓት ሙሉ በመሆኑ ሊያሰለችና ተስፋ ሊያስቆርጥ ይችላል። ሆኖም ፈጣሪን ማማረር አይገባም›› ይላሉ። እነሱን የትም ቦታ ይዞ መሄድ እንደማይቻልም ያነሳሉ። ሱፐር ማርኬት እንኳን ይዘዋቸው ቢሄዱ ሁሉንም ዕቃዎች ስለሚነካኩ ያስቸግራል። የገዛ ወላጆቻቸውን እህትና ወንድሞቻቸውን እንዲሁም ቤተሰባቸውንና ማንኛውንም ሰው መለየት አይችሉም። በዚህ የተነሳ እነሱን ከቤት ውጪ ይዞ መውጣት ያስቸግራል። በተለይም ስለማይለዩ እናት ታዝናለች። ስለዚህ ወደየትኛውም ሥፍራ ሲሄዱ ቤት ውስጥ ከሠራተኛ ጋር ትተውት ነበር የሚወጡት። ቀስ በቀስ ግን በተቻለ መጠን እየተቆጣጠሩ ይዘውት በመውጣት ያለማምዱት የነበረበት ሁኔታ ነበር ‹‹ኦቲዝም በሽታ የያዘው ልጅ ባህርይ ወይም በሽታ ከልብ ክብካቤ ክትትልና ሕክምና ካገኘ ይሻሻላል ይቀየራል፤ ይሄን በራሴ ልጅ አይቻለሁ›› ይላሉ። እንዳከሉት አሁን ላይ ልጃቸው ተው ሲሉት መስማት ደረጃ ላይ ደርሷል። አታድርግ የሚሉትን አያደርግም። በተለይ እሳቸውንና አባቱን ወንድምና እህቶቹን መለየት ችሏል። ሥራዎችንም ለመሥራት የሚሞክርበት አለ። ቤተክርስቲያንም ከቤተሰቦቹ ጋር ይሄዳል።

‹‹ከዚህ በፊት ይሄን ሁሉ አያደርግም ነበር›› የሚሉት ወይዘሮ ራሄል ይሄ ትልቅ ለውጥ እንደሆነም ይናገራሉ። ‹‹የራሴን ልጅ ለውጥ ሳይ በ2003 ዓ.ም ለምን የሌሎቹን ልጆችስ ለምን አላግዝም በሚል በልጄ ስም ‹‹ነህሚያ ኦቲዝም ማዕከል››ን መሰረትኩ›› ይላሉ። አሁን የዚህ ድርጅት መሥራችና ዳይሬክተር ሆነው እየሰሩ የሚገኙት ወይዘሮ ራሄል ማዕከሉን ለመመስረት ካነሳሳቸው ዋናው በልጃቸው የተነሳ ሚኒ፟ ዘሚ የኑስ ከመሰረቱት ከጆይ ኦቲዝም ማዕከል ኒያ ፋውንዴሽን ጋር በቅርበት መሥራታቸው ነው። አሁን ላይ በማዕከላቸው 60 በኦቲዝም የተጠቁ አውቲስቲክ ልጆችን እየተንከባከቡ እንደሚገኙም አጫውተውናል። ‹‹በሽታው በአብዛኛው ወንዶችን ነው የሚያጠቃው›› የሚሉት ወይዘሮ ራሄል ሳይንሱ እንደሚለውም ከስምንት ልጆች የሚያጠቃው አንዷት ሴት ልጅን ብቻ እንደሆነ ማመላከቱንና በማዕከሉ ካሉት ከ60ዎቹ ውስጥ የሴቶች ቁጥር ሰባት ብቻ መሆኑንም ነግረውናል። ከኦቲዝም ጋር የሚወለዱ ልጆች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መምጣቱን ደጋግመው ሲያነሱ የሚደመጡት ወይዘሮ ራሄል ከ1 ሺህ 400 በላይ የበሽታው ተጠቂ ልጆች በተጠባባቂነት በማዕከሉ ተይዘው መገኘታቸውንም አክለውልናል።

በዚህ መስክ የሕክምና ባለሙያ፤ ልጆቹን የሚንከባከብ ሰው እጥረት እንዲሁም ከፍተኛ የሰው ኃይል አለመኖሩንና በዚህም በበሽታው የተጠቁ ልጆች ወላጆች በተለይም እናቶች አብዝተው መቸገራቸውን ያነሳሉ። ይሄን ሥራ በመሥራታቸው ችግሩን በእገዛቸው መቅረፍ ለሚችሉ ለሰባት ወንዶች ጨምሮ ለ43 ሰዎች የሥራ ዕድል መክፈት የቻሉበት አጋጣሚ መፈጠሩንም አውግተውናል። ‹‹ሰዎቹ አውቲስቲክ ልጆች በምን መንገድ ከዘላቂ በሽታቸው ቀስ በቀስ እያገገሙ መሻሻል እንዲችሉ በማገዙ ረገድ ትልቅ ልምድና ስልጠና ያላቸው ብቻም ሳይሆን አውቲስቲክ ልጆች ከፍተኛ ፍቅርና ትዕግስት ያለው ሰው እንደመፈለጋቸው ይሄንንም የሚያሟሉ ናቸው›› ብለውናል። እኛም ኦቲዝምን በመረዳት ትዕግስትና ፍቅር ለአውቲስቲክ ልጆች በመስጠት ከበሽታቸው እንዲያገግሙ እናግዛቸው በማለት ጽሑፋችንን ቋጨን።

# ዓለም አቀፍ



## ሩሲያ በያርስ የሚሳይል ሥርዓት ልምምድ መጀመሯን አስታወቀች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ሩሲያ በያርስ አህጉር አቋራጭ ባሊስቲክ ሚሳኤል እና በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ወታደር ልምምድን ጀምራለች ሲል የመከላከያ ሚኒስቴር ገለጸ።

ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲን የቶፖልን ሥርዓት የተካውን የያርስ ሚሳኤል ሥርዓት የሩስያ “የማይበገሩ የጦር መሳሪያዎች” አካል እና የመሬት ላይ የተመሰረተው የኒውክሌር ጦር መሳሪያ ዋና መሰረት እንዲሆን ለማድረግ ዓላማ አድርገዋል።

የመከላከያ ሚኒስቴር በቴሌግራም የመልእክት መላላኪያ አገልግሎት ላይ በሰጠው መግለጫ “በአጠቃላይ ከሦስት ሺህ በላይ ወታደራዊ አባላት እና ወደ 300 የሚጠጉ መሳሪያዎች ልምምዱ ላይ ተሳትፈዋል።

ልምምዱ የስትራቴጂክ ሚሳይል ሃይሎች አጠቃላይ ቁጥጥር የኦምስክ ሚሳኤል አፈጣጠርን ከትእዛዝ እና ከሰራተኞች ልምምድ ጋር ከኖቮሲቢርስክ ሚሳኤል አሰራር ጋር ያርስ ሲስተሞችን ያካትታል።

በልምምድ ወቅት የያርስ የሞባይል ሥርዓቶች በሦስት የሩሲያ ክልሎች ውስጥ እንቅስቃሴዎችን ያካሂዳሉ ብሏል ሚኒስቴሩ።

“እንዲሁም ስትራቴጅካዊ ሚሳኤሎች ከማዕከላዊ ወታደራዊ ዲስትሪክት እና ከኤሮስፔስ ሃይሎች አደረጃጀቶች እና አሃዶች ጋር በመተባበር ዘመናዊ የአየር ላይ አሰሳ ዘዴዎችን ለመምሰል እና ለመከላከል የተወሰኑ እርምጃዎችን ያካሂዳሉ።

12 ሺህ ኪሎ ሜትር የሥራ ማስኬጃ ርቀት እንዳለው የተነገረለት የያርስ ሞባይል አህጉር አቀፍ ባሊስቲክ ሚሳኤል ዘዴዎች ጥቂት የተረጋገጡ ታክቲካዊ እና ቴክኒካል ባህሪያት አሉት።

እንደ ወታደራዊ ጦማሪዎች ገለጻ፣ ሥርዓቶቹ ራሳቸውን ችለው በርካታ ኢላማ የተደረጉ የኒውክሌር ጦርነቶችን መሸከም የሚችሉ እና በጭነት መኪና አጓጓዦች ላይ ሊጫኑ ወይም በሲሎስ ውስጥ ሊሰማሩ ይችላሉ።

ባለፈው ዓመት የካቲት ወር ዩክሬን ላይ ወረራ ከጀመረች በኋላ ሩሲያ በራሷ ወይም በሌሎች ሀገራት እንደ ቻይና ወይም ደቡብ አፍሪካ ያሉ በርካታ ወታደራዊ ልምምዶችን አድርጋለች ሲል የዘገበው አል አይን ኒውስ ነው።

## ትንሿ ሌሶቱ በሰፊ የደቡብ አፍሪካ ግዛቶች ላይ የይገባኛል ጥያቄ ልታቀርብ ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የሌሶቱ ፓርላማ በደቡብ አፍሪካ ስር ገብተውብኛል ያላቸውን ሰፋፊ ግዛቶች እንዲመለሱለት በሚጠይቅ የውሳኔ ሃሳብ ላይ ሊወያይ ነው።

በግዙፏ ደቡብ አፍሪካ ተከባ የምትገኘው የትንሽዬዋ አገር ፓርላማ በግዛት ጥያቄው ላይ ተወያይቶ ውሳኔ ያሳልፋል ተብሎ የሚጠበቀው በትናንትናው ዕለት ነው።

ለፓርላማው የቀረበን የውሳኔ ሃሳብ ሰነድ የጠቀሱ አንድ የተቃዋሚ ፓርቲ የምክር ቤት አባል እንዳሉት፣ ሌሶቱ በዙሪያዋ ያሉ በደቡብ አፍሪካ ስር የሚገኙ በርካታ ግዛቶች ላይ የይገባኛል ጥያቄን አንስታለች።

ሕግ አውጪዎቹ የደቡብ አፍሪካ “ፍሪ ስቴት ግዛትን በሙሉ፣ የሰሜን እና ኢስተርን ኬፕ ግዛቶችን በከፊል፣ ፑማላንጋን በከፊል እንዲሁም የክዋዙሉናታል ግዛትን የተወሰነ ክፍሎችን” የሌሶቱ ግዛት አድርገው እንዲወስኑ ሃሳብ ቀርቧል።

ሌሶቱ ይገባኛል በሚል ከደቡብ አፍሪካ ለመጠየቅ የተነሳችው አካባቢዎች ደቡብ አፍሪካ ካሏት ዘጠኝ ግዛቶች በአምስቱ ላይ ነው።

የውሳኔ ሃሳቡ ሰነድ እንደሚለው ይህ የሌሶቱ የግዛት ይገባኛል ጥያቄው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጠቅላላ ጉባኤ በአውሮፓውያኑ 1962 ያሳለፈው ውሳኔን መሠረት ያደረገ ነው።

በንጉሣዊ አስተዳደር ስር ያለችው ሌሶቱ በደቡብ




አፍሪካ ሙሉ ለሙሉ ተከባ የምትገኝ ትንሽዬ አገር ስትሆን፣ አጠቃላይ እንቅስቃሴዋ ከደቡብ አፍሪካ ጋር የተያያዘ ነው። የሌሶቱ ሕዝብ በተጠቀሱት እና አሁን በደቡብ አፍሪካ ስር በሚገኙት ግዛቶች ውስጥ ይኖሩ እንደነበር በታሪክ ይነገራል ሲል የዘገበው ቢቢሲ ነው።

# ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች ለምግብ

- ዩኒቨርሲቲዎች

# የሚመደበው በጀት እንዲሻሻል ጥናት ተሠርቶ ለገንዘብ ሚኒስቴር ቀርቧል

- ትምህርት ሚኒስቴር

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ፡- ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች ለምግብ የሚመደበው በጀት ዝቅተኛ ነው ሲሉ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ገለጹ፡፡ ትምህርት ሚኒስቴር በበኩሉ በጀቱ እንዲሻሻል ጥናት ተሠርቶ ለገንዘብ ሚኒስቴር መቅረቡን አስታውቋል፡፡

የወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ ፋይናንስና በጀት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ተክሉ መና ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ለተማሪዎች ቀለብ በቀን ለአንድ ተማሪ 15 ብር ቢበጀትም ዩኒቨርሲቲው ግን ለተማሪዎች በቀን በትንሹ 100 ብር ያወጣል ብለዋል፡፡

በአሁኑ ጊዜ ባለው የኑሮ ውድነት የሚመደበው በጀት አነስተኛ ነው ያሉት አቶ ተክሉ ለሌላ ሥራ የሚመደበው በጀት ለተማሪ ምገባ እየዋለ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በዩኒቨርሲቲው በሳምንት ሁለት ቀን ስጋ የሚቀርብ ሲሆን ለተማሪው መጠኑንና ጥራቱን የጠበቀ ምግብ ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡ ነገር ግን ይህን ለማሟላት ከመንግሥት አስፈላጊው ግብአት እየተሟላ አይደለም፡፡

እንደ አቶ ተክሉ ገለጻ በተያዘው በጀት አመት ለተማሪ ምገባ 108 ሚሊዮን ብር ቢበጀትም የተበጀተው በጀት በማለቁ ዩኒቨርሲቲው ለሌላ ሥራ ከተበጀተው ላይ 63 ሚሊዮን ብር እላፊ ተጠቅሟል፡፡

ይህን አስመልክቶም መንግሥት ለሌላ ሥራ የተመደበው በጀት ለቀለብ እየዋለ ሌሎች ሥራዎች እየቆሙ መሆኑን ተረድቶ ወቅታዊ ገበያውን መሠረት ባደረገ መልኩ የዋጋ ማሻሻያ ሊያደርግ ይገባል ብለዋል፡፡

ሌላኛው አስተያየታቸውን የገለጹት የአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶ/ር ዳምጠው ደርዛ በዩኒቨርሲቲው ተማሪ እየተመገበ ያለው በተበጀተለት 15 ብር ሳይሆን በአማካይ 68 ብር ወጪ እየተደረገ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በዚህም ምክንያት ዩኒቨርሲቲው ለሌላ ሥራ የተበጀተውን በጀት አዙሮ ለምገባ እየተጠቀመ ሲሆን ይህም ዩኒቨርሲቲው ሊሠራቸው የሚገቡ ሌሎች ሥራዎች ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ እያሳደረ ነው ብለዋል፡፡

ከዚያ በተጨማሪም አንድ በጀት ለተመደበበት አላማ ሊውል እንደሚገባ የኦዲት ሕጉ ስለሚያዝ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በኦዲት ግኝት ስማቸው እንዲነሳም ያደርጋል ብለዋል፡፡

የትምህርት ሚኒስቴር የአስተዳደርና መሠረተ ልማት መሪ ሥራ አስፈጻሚ ዶ/ር ሰለሞን አብርሀ ዩኒቨርሲቲዎች በቀን ለአንድ ተማሪ 15 ብር ቢበጀትላቸውም ይህ ካለው የኑሮ ውድነት አንጻር በቂ አለመሆኑ ይታወቃል ብለዋል፡፡

ይህንን ለማስተካከልም ትምህርት ሚኒስቴር መመሪያውን የማሻሻል ሥራ እየሠራ ነው ያሉ ሲሆን ይህንን አስመልክቶም ጥናት ተጠንቶ ለገንዘብ ሚኒስቴር መቅረቡን አስረድተዋል፡፡

በጥናቱ ከ2009 ዓ.ም እስከ 2014 ዓ.ም ዩኒቨርሲቲዎች ምን ያህል ወጪ ያወጣሉ የሚለውን 19 ዩኒቨርሲቲዎችን መነሻ በማድረግ ተጠንቶ በአማካይ የምግብ ዋጋ ቀርቧል ብለዋል፡፡

ዶ/ር ሰለሞን ዩኒቨርሲቲዎች ከሥራቸው ጋር ተያያዥነት ያላቸው ቢዝነስ የሚሠሩበት አግባብ በመኖሩ በእንስሳት ልማት፣ በስንዴ ማልማትና በሌሎች ዘርፎች እየሠሩ መሆኑን ጠቅሰው፤ ይህም የምግብና ሌሎች ችግሮችን ለመፍታት እንዳገዛቸው ጠቁመዋል፡፡

## «የዓባይ ግድብ ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

የላቸውም፡፡ በቅኝ ግዛታቸው ልክ የተበታተኑ ሆነው ይታያሉ፡፡ ኢትዮጵያ ቅኝ ያልተገዛች ብቸኛ አገር መሆኗን ተከትሎ ብቻዋን እንድትቆም የማድረግ ሁኔታ ይታያልም ሲሉ ጠቁመዋል፡፡

ግብጽ የውሃ ችግር የለባትም ያሉት መምህሩ፤ በቀይባህርና በሜዲትራኒያን ባህር የተከበበች፣ ከፍተኛ የከርሰ ምድር ውሃ ክምችት ያላት አገር ናት፡፡ የሱዳንም የግብጽም ሕዝብ በተለይም ምሁራን ቆም ብለው ሊያስቡበት ሂደቱንም ሊነቅፉት ይገባል፡፡ አገራቱ ከዚህ ውጪ የሚያደርጉት እንቅስቃሴ ከንቱ ነው ብለዋል፡፡

ለኢትዮጵያ መታዘዝ፣ ለችግሯ መቆርቆር፣ ተፋሰሱ በድርቅ ሲጠቃ ውሃ ሊያንስ ስለሚችል በኢትዮጵያ ለሚያጋጥም ድርቅ ደራሽ መሆን እንደሚገባቸውም አመልክተዋል፡፡

ሁለቱ አገራት የግድቡ ግንባታ ተጠናቅቆ ወዳጅ እስኪሆኑ ኢትዮጵያውያን ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ በእውቀት ላይ በመመስረት መከራከርና ማስረዳት ይጠበቅባቸዋል ያሉት ዶክተር ኢንጂነር ጥላሁን፤ ለግድቡ ግንባታ አስተዋጽኦ ማድረግ ግድቡን ፈጥኖ ማጠናቀቅ፣ የሚያስፈልገውን ተጨማሪ ግድቦችን መገንባት ያስፈልጋል ነው ያሉት፡፡

ሁለቱ አገራት ፖለቲካቸው እየተበላሸ በመምጣቱ ምክንያትም አቅጣጫቸውን አዙረው የሚሞክሩት ነገር ሊኖር ስለሚችልም መንግሥት በንቃት መከታተል አለበት ሲሉም አሳስበዋል፡፡

ኢትዮጵያ ሕዝቡን በማስተባበር በያዘችው አቋም ጠንክራ መቀጠል አለባት ያሉት ዶክተር ኢንጂነር ጥላሁን፤ አሁን በኢትዮጵያ ላይ ጫና የሚያሳድሩ ኃይሎች አንድ ቀን እንቅስቃሴው ትክክል አለመሆኑን ይገነዘባሉ፡፡ የዓባይ ግድብ ሙሉ ለሙሉ ሥራውን ከጀመረ በኋላ ምንም እንደማይጎዳቸው ያረጋግጣሉ፣ በዚያን ጊዜ በጥርጣሬ መተያየቱ ያቆማል ሲሉ ገልጸዋል፡፡

በተለይም የግብጽም ሆነ የሱዳን ሕዝብ ከወታደራዊ አገዛዝ የመውጣት ዕድል ካገኘ በሕዝቦች መካከል መፈቃቀር፣ መፈቃቀድ፣ ድንበር አጥፍቶ የጋራ አገር እስከመመስረት መድረስ እንደሚችሉም ተናግረዋል፡፡

‹‹ይህ የጋራ ሀብት ነው፡፡ ሕዝቦችን ሊያቀራርብ እንጂ ሊያራርቅ አይገባም›› ሲሉም ዶክተር ኢንጂነር ጥላሁን ተናግረዋል፡፡

ለህሊናቸው የቆሙ በርካታ የግብጽ ምሁራን ምንም ተጽእኖ እንደሌለው ቢገልጹም ተቀባይነት እንዳላገኙም ነው የተናገሩት፡፡

ወታደራዊ መንግሥታት አጀንዳ ሲያጡ ሕዝቡን የሚያታልሉት ‹‹ኢትዮጵያ ውሃ ልታሳጣችሁ ነው፣ እዚያ ላይ እየሠራን ነው›› በሚል ሕዝቡን ማታለያ አድርገውታል ሲሉም አብራርተዋል፡፡

ኢትዮጵያ በልማቷ እንድትጠቀምና ገንና እንድትወጣ አይፈለግም፡፡ የደኸየች፣ የቆረቆዘች እና የተበጣጠሰች ሆና እንድትቀጥል ይፈልጋሉ ነው ያሉት ዶክተር ኢንጂነር ጥላሁን፡፡


## Invitation for National Competitive Bid (NCB)
## Bid No (Gada/NCB/05/2015)

Gada Transport and logistics S.C has invited eligble and qualified bidders to procure MDVR (**Mobile Digital Video Recording**) Hardware through National Competitive Bidding (NCB) procedures for Fleet Management compliance.

1. The bidders who has the following eligbility documents can apply for the assignment
   - ♦ Valid business license indicating the stream of the business in which the Bidder is engaged
   - ♦ VAT registration Certificate issued by the tax authority
   - ♦ Valid tax clearance Certificate issued by the tax authority
   - ♦ Being registered in the suppliers list
   - ♦ As a proof of the bidder's financial standing, financial statement certificate by an independent auditor for two years is needed.
2. interested eligble bidders may obtain the bid document and detail specification of the material from the companies address given below from March 28/2023 upto April 18 /2023 time 8:30-5:00PM.
3. All bids must be accompanied by a bid security in the amount of birr 50,000 (fifty thousand) in the form of certified cheque (CPO) issued by a recognized bank or bank guarantee from recognized bank.
4. A complete set of bidding document in English may be purchased by interested bidders up on payment (depositing) of non-refundable fee of birr 100 (one hundred birr). The method of payment will be cash on site.
5. The bidders shall submit each of their bids in to two separate outer envelopes, the first envelope containing the original and copy of the technical proposal envelopes; the second envelope containing the original and copy of the financial proposal envelopes. The bid security shall be contained in the original technical proposal envelope.
6. The application and necessary documents must be delivered to the address below at or before date April 18, /2023 time 8:30-5:00PM in the morning. Late application will be rejected.
7. Technical document will be opened in the presence of the bidders or their legal representatives who choose to attend at the address below on April 18/2023 at 2:30 PM in the afternoon and financial will be opened after the technical evaluation result is notified to all bidders.
8. The Gada Transport and logistics S.C reserves the right to reject any bid and to annual the bidding process and reject all bids at any time prior to contract award without thereby incurring and liability to bidders,

The address refferd to above is: Gada Transport and logestics s.c, Around Sengatera in front of commerce college, Biftu Adugna Business S.C Building, 12th floor Procurement Directorate.

**Phone: 011-558-25-19**

## Gada Transport and Logistics S.C

## BID INVITATION FOR NATIONAL BIDDERS

**Bid Title: Provisional Consultancy Service to Asset Evaluation for International Financial Reporting Standards (IFRS) Implementation**

Under Tourism Training Institute Genet Hotel Enterprise is an antique and historical Hotel found in the center of Addis Ababa Mozambique Street, on the road from Mexico to Kera, and it is a government owned hotel working as model training center to the tourism Institute.

Thus, Genet Hotel Enterprise now invites all interested eligible firm to evaluate Asset evaluation for International Financial Reporting Standards (IFRS).

Interested bidders are required to fulfill the Following.

- Interested bidders can purchase the TOR document from Genet Hotel Enterprise finance department located Addis Ababa Mozambique Street, on the road from Mexico to Kera in front of Kassa Grand Mall with non-refundable fee of ETB 200.00(Two Hundred Birr). The bid will float on newspaper for ten consecutive days from date of this announcement and closing /opening day is on the tenth day at 2:00PM and the bid will be opened at 2:30 PM. If the closing/opening day is non-working day the next day will be considered as opening day.
- Bidders shall submit a bid Bond in the form of CPO amounting to Ethiopian Birr 5,000.00 (Five Thousand Birr). The CPO Shall be prepared by the name of "Genet Hotel Enterprise".
- Bidders who fulfill the Criteria set in the TOR Shall Submit their offer (Technical and Financial Proposals Separately) In wax sealed envelopes marking "Technical and Financial" Proposal to Genet Hotel Finance Department before deadline.
- Bid Document Without renewed Trade license & Tax clearance, CPO, VAT Certificate and TIN certificate will be automatically disqualified from the competition.
- Genet Hotel has reserved the right to fully or partially accept or reject this bid.
- Interested eligible bidders may obtain further information and clarification in the listed down address.

**Address:**

**Genet Hotel Enterprise**

**Kirkos Sub City Woreda 11 House no 884,Mexico Road**

**0911-750219/0911-885563**

**Addis Ababa- Ethiopia**

## Tourism Training Institute

# ስፖርት

## ዓለም አቀፉ የጸረ አበረታች ቅመሞች ኤጀንሲ ኢትዮጵያን አደነቀ

ብርሃን ፈይሳ

ከዓመታት በፊት የስፖርት አበረታች ቅመሞች (ዶፒንግ) ተጠቃሚነት በኢትዮጵያ የመኖሩ ዜና ሲሰማ በስፖርት ቤተሰቡ ዘንድ የፈጠረው ድንጋጤ የሚዘነጋ አይደለም፡፡ በዓለም ሕዝብ ዘንድ በአትሌቲክስ ስፖርት የተከበረች ሀገር በዚህ ጉዳይ ስሟ መነሳቱ የቆረቆራቸው የዘርፉ ባለሙያዎች እንዲሁም መንግሥታዊ አካላት ባደረጉት ርብርብም በአጭር ጊዜ ውስጥ አስደንጋጩ ማዕበል ሊረግብ ችሏል፡፡ በቆራጥነት በተሰራው ስራም የኢትዮጵያ ጸረ አበረታች ቅመሞች ባለሥልጣንን በማቋቋም እና አስፈላጊውን ጥረት በማድረግ በአፍሪካ ደረጃ ዶፒንግን በመዋጋት ምሳሌት የሚሆን ስራ ተከናውኗል፡፡

ዓለም አቀፉ የጸረ አበረታች ቅመሞች ኤጀንሲ ባለሙያዎችም በተለያየ ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት ይህንኑ ሁኔታ አረጋግጠዋል፡፡ ከሰሞኑም የዓለም አቀፉ የጸረ አበረታች ቅመሞች ኤጀንሲ ፕሬዚዳንት ዊቶልድ ባንካ ከልኡካቸው ጋር በኢትዮጵያ የስራ ጉብኝት አድርገዋል፡፡ በአፍሪካ ደረጃ የኤጀንሲው ፕሬዚዳንት መሰል ጉብኝት ሲያደርጉ ይህ የመጀመሪያቸው ሲሆን፤ በቆይታቸውም የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ፣ የኢፌዴሪ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ደመቀ መኮንን እንዲሁም ከኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስትር ቀጄላ መርዳሳ፣ የስፖርት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ አምባሳደር መስፍን ቸርነትን እንዲሁም የመንግሥት ስራ ኃላፊዎችን በማግኘት ውይይት አድርገዋል፡፡

በውይይቱም ፕሬዚዳንቱ «በአፍሪካ ትልቁ ተቋም» በማለት ኢትዮጵያ ዶፒንግን ለመዋጋት እያከናወነች ያለችው መልካም ተግባር ማድነቃቸውን፤ የኢትዮጵያ ጸረ አበረታች ቅመሞች ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር አቶ መኮንን ይደርሳል ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ ገልጸዋል፡፡ ለጉብኝቱ ምክንያት ከሆኑ ጉዳዮች መካከል አንዱ



ዓለም አቀፉ የጸረ አበረታች ቅመሞች ኤጀንሲ ልዑክ ከኢፌዴሪ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ደመቀ መኮንን ጋር ተወያይቷል፤

ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ የውድድር መድረኮች በአትሌቲክስ ስፖርት ተጠቃሽ ሀገር መሆኗ ሲሆን፤ ሌላኛው የሚደረገውን ጠንካራ የጸረ አበረታች ቅመሞች እንቅስቃሴ ይበልጥ ለማሳደግ ነው፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን በአፍሪካም ሆነ በምስራቅ አፍሪካ ቀጣና ባለው እንቅስቃሴ ኢትዮጵያ የደጋፊነት ሚና እንዲኖራትና ይህንንም ማሳደግ እንድትችል ከአፍሪካ ህብረት ኮሚሽን ሊቀመንበር ጋር በመነጋገር አቅጣጫ ማስቀመጣቸውን አቶ መኮንን አስታውሰዋል፡፡

ፕሬዚዳንት ዊቶልድ ባንካን ከመንግሥት ስራ ኃላፊዎች ጋር በየደረጃው ባደረጉት ውይይትም፤ ለእስካሁኑ ስራ ዕውቅና በመስጠት በቀጣይ ሊከናወኑ በሚገባቸው ጉዳዮች ላይ አቅጣጫ ሰጥተዋል፡፡ በዚህም ዶፒንግን ለመዋጋት እየተደረገ ያለውን እንቅስቃሴ ይበልጥ ማጠናከር ተገቢ መሆኑንና በመንግሥት በኩል የሚደረገው ትኩረት ቀጣይነት እንዲኖረው ማድረግ ቀዳሚው ነው፡፡

ሌላው በአፍሪካ ደረጃ ኢትዮጵያ ዶፒንግን ለመከላከል ያላትን ሚና በላቀ ሁኔታ እንድትወጣ የሚያስችል ነው፡፡ በኢትዮጵያ በኩልም የስፖርት አበረታች ቅመሞች መመርመሪያ ቤተ ሙከራ ለመገንባት የተጀመረውን ስራ በኤጀንሲው ድጋፍ እንዲያገኝ ጥያቄ ቀርቧል፡፡ ለቤተ ሙከራው ዕውቅና የሚሰጠውም ሆነ ቴክኒካዊ ድጋፍ የሚያደርገው ዓለም አቀፍ ኤጀንሲው እንደመሆኑ ይህንኑ የሚመለከት ሃሳብ መቅረቡንም ዳይሬክተሩ አብራርተዋል፡፡

ባለሥልጣኑ፤ ኤጀንሲው የሚያወጣቸውን ደንቦችና መመሪያዎች በመተግበር እንዲሁም መረጃዎችን በመለዋወጥ ረገድ ጠንካራ የሚባል ግንኙነትን መፍጠር ችሏል፡፡ ከሀገር ውስጥ የስፖርት ማህበራት እንዲሁም ከሚመለከታቸው አካላት (ከጤና ባለሙያዎችና ፍትህ አካላት) ጋርም በቅንጅት ይሰራል፡፡ በአበረታች ቅመሞች ቁጥጥር ዙሪያ በኢትዮጵያ እየተተገበረ ያለው ስራ ጠንካራ ሲሆን፤ ለዚህም ማሳያው የሕግ ማዕቀፎችን ማዘጋጀትና መተግበር ነው፡፡ ተቋምን ከመገንባት አንጻርም በሰው ኃይልና በአሰራር ማጠናከር፣ ትምህርትና ሥልጠናን በሚመለከትም ባለሥልጣኑ ከሚሰራው ባለፈ በሀገር አቀፍ ደረጃ ከ5ኛ ክፍል አንስቶ በመደበኛ ሥርዓተ ትምህርት እንዲያውቁት በማድረግም ረገድ ዘርፈ ብዙ ስራ ተከናውኗል፡፡ እንደ ጀማሪ ሀገር ጥሩ የሚባል ደረጃ ላይ ያለው ነገር ግን በበቂ ሁኔታ ያልተሰበበት ምርመራና ቁጥጥርን የሚመለከት ነው፡፡ ይኸውም እንደ ኢትዮጵያ ያሉት በርካታ አትሌቶች በመሆናቸው እና ምርመራውም በውጭ ሀገር በመሆኑ ከውጭ ምንዛሬ ጋር በተገናኘ ያለው ውስንነት ባለሥልጣኑን በሚፈለገው ልክ ባያራምደውም መልካም በሚባል ደረጃ ላይ የሚገኝ መሆኑን ዳይሬክተሩ አስረድተዋል።

እንደ ኢትዮጵያ ልዩ ትኩረት የሚሰጠው ለአትሌቲክስ ስፖርት ቢሆንም ሁሉም ስፖርት ከስፖርት አበረታች ንጥረ ነገሮች የጸዱ እንዲሆኑ ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ ሁሉም ዜጋ ሃላፊነት ያለበት በመሆኑ የሚመለከታቸው አካላት በሙሉ ኃላፊነታቸውን ሊወጡ እንደሚገባም ዳሬክተሩ አሳስበዋል። በተለይም የስፖርት ማህበራት፣ የስፖርት ባለሙያዎች እና ስፖርተኞች ከሚያገኙት ጊዜያዊ ጥቅም ይልቅ ሀገራቸውን በማስቀደም መስራት እንዳለባቸውም አክለዋል፡፡


# የጨረታ ማስታወቂያ

## ቁጥር 02/2015

## አዋጭ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኃላፊነቱ የተወሰነ መሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበር

**ማህበሩ**
**የማህበሩ የ2015 በጀት ዓመት**
**ሎት 1 ቋሚ ዕቃዎች /ፈርኒቸሮች/፣**
**ሎት 2. ቋሚ የቢሮ ኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች፣**
**ሎት 3 የጽህፈት መሳሪያዎችን በጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል**
**ስለሆነም ተወዳዳሪዎች/ተጫራቾች፡**

1. በዘርፉ የታደሰ ህጋዊ የንግድ ፈቃድ ያላቸው፣የዘመኑን ግብር የከፈሉ እና ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የድጋፍ ደብዳቤ ማቅረብ የሚችሉ መሆን አለባቸው፡፡
2. በገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ትብብር ሚኒስቴር የተመዘገቡ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ማቅረብ አለባቸው፡፡
3. የተጨማሪ እሴት ታክስ /ቫት/ የምዝገባ ማስረጃ የምስክር ወረቀት ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
4. የጨረታውን ሰነድ የማይመለስ ብር 100/ አንድ መቶ ብር/ በመክፈል አዋሬ፣ ኤድና አዲስ ሆቴል ፊት ለፊት ገባ ብሎ፣ አጋር ሕንጻ፣ 3ኛ ፎቅ፣ ቢሮ ቁጥር 301 በመቅረብ መውሰድ ይችላሉ፡፡
5. የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ብር 10,000.00 /አስር ሺህ ብር/ በባንክ በተረጋገጠ CPO ከጨረታ ሰነዱ ጋር አሽገው ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
6. የሚወዳደሩባቸው እቃዎች ጥራታቸውን የጠበቁ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡
7. ተጫራቾች ለሚያቀርቡት እቃና አገልግሎት ግዢዎች በሙሉ ዋስትና ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
8. ለሚወዳደሩባቸው በሎት 1 እና በሎት 2 የተገለጹትን እቃዎች በተመለከተ ናሙና ማሳየት እንዲሁም በሎት 3 የተገለጹትን እቃዎች በተመለከተ ከእየ አይነቱ አንድ አንድ ናሙና የድርጅታቸውን ማህተም አድርገው የናሙናዎቹን ዝርዝር በሁለት ኮፒ በማድረግ ጨረታው ከሚከፈትበት ዕለት አስቀድሞ በማህበሩ ንብረት ሠራተኛ አስፈርመው ማስረከብና አንዱን ኮፒ መረከብ ይኖርባቸዋል፡፡
9. በሰነዶቻቸው ላይ ስማቸውን፣ ሙሉ አድራሻቸውና ፊርማቸውን አሟልተው ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
10. በተጫራቾች ዋጋ ላይ ተንተርሶ የሚቀርብ ዋጋ ተቀባይነት የለውም፡፡
11 የጨረታ ማስታወቂያው በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከወጣ ዕለት ጀምሮ እስከ 16ኛው ቀን ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ድረስ የጨረታ ሰነዳቸውን ማስገባት የሚችሉ ሲሆን በዚሁ ቀን 4:00 ሰዓት የጨረታ ሳጥኑ ታሽጎ በ4፡15 ተጫራቾች እና ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ጨረታው ይከፈታል፡፡
12. ለአሸናፊ ተወዳዳሪዎች በጨረታው ማሸነፋቸው እንደተገለጸላቸው ቅሬታ ያላቸው ተወዳዳሪዎች ቅሬታቸውን በጽሑፍ ለማህበሩ ስራ አስፈጻሚ በ5 ቀናት ውስጥ ማቅረብ ይችላሉ፡፡ በውድድሩ የቀረበ ቅሬታ ከሌለ አሸናፊ ድርጅቶች በ15 ቀናት ውስጥ በማህበሩ ቀርበው ግዢውን ከሚፈፅመው አካል ጋር ውል ይፈፅማሉ፡፡
13. ማህበሩ የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**ለበለጠ መረጃ፡- በስልክ ቁጥር 011-557-9394 ደውሎ መጠየቅ ይቻላል፡፡**
**አድራሻ፡- አዋሬ፣ ኤድና አዲስ ሆቴል ፊት ለፊት ገባ ብሎ፣**
**አጋር ሕንጻ፣ 3ኛ ፎቅ፣ ቢሮ ቁጥር 301**
**አዋጭ የገ/ቁ/ብ/ኃላ/የተ/መሠ/የህብረት ሥራ ማህበር ዋና ቢሮ**

# አዋጭ የገ/ቁ/ብ/ኃላ/የተ/መሠ/የህብረት ሥራ ማኅበር